የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ።

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

፩ኛ ፡ ቮልዩም ፡ ቍጥር ፡ 1
በጋ ፡ 1956 ፡ ዓ ፡ ም ።

Vol. I No. 1
Summer 1964

በዚህ ፡ እትም ፡

IN THIS ISSUE

የጉዳዩ ፡ መግለጫዎች ፡

ጋብቻ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡
በዊልያም ፡ ቡሐጂያር ፡

የሕጎች ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ ደረጃ ፡ በኢትዮጵያ ።
በጂ ፡ ቸችኖቪች ፡

የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጠምራ ፡ ክስ ፡
በፊሊፕ ፡ ግራቨን ፡

Case Reports

Marriage under the Civil Code of Ethiopia
William Buhagiar

Hierarchy of Laws in Ethiopia
G. Krzeczunowicz

Joinder of Criminal and Civil Proceedings
Philippe Graven

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡

በዓመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥሴላ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሚዘጋጅ ።

(፩ኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡

መጽሔት ፡ ተብሎ ፡ ይጠቀሳል ።)

የቦርዱ ፡ አባሎች ፡

አቶ ፡ በላቸው ፡ አሥራት ፡ ሰብሳቢ ፡	አቶ ፡ ንራአዮ ፡ ኢሣያስ ፡
ዶክተር ፡ ፊሊፕ ፡ ግሬቨን ፡	ዲን ፡ ጃይምስ ፡ ሲ. ኤን. ፖል ፡
አቶ ፡ ነጋ ፡ ተሰማ ፡	ሚስተር ፡ ሮበርት ፡ ኤ. ሰድለር ፡

አ ዘ ጋ ጅ ዎ ች ፡

ሚስተር ፡ ሮበርት ፡ ኤ. ሰድለር ፡	የዝግጅቱ ፡ አመራር ፡ ዋና ፡ ኃላፊ ፡
ሚስተር ፡ ስቲቨን ፡ ሎወንሽተን ፡	የፍርዶች ፡ ዝግጅት ፡ ዋና ፡ ኃላፊ ፡
ሚስተር ፡ ቶማስ ፡ አ. ሮስ ፡	ከፍርድ፡ቤት፡ለሚሰጡ፡መግለጫዎች፡ኃላፊ፡
ሚስተር፡ዳብሊው፡ሉወረንስ፡ቸርች፡	የማሳተሙ ፡ ተቆጣጣሪና ፡ አዘጋጅ ፡
ሚስተር ፡ አዊን ፡ ፒ. ሲልኪ ፡	የሥራው ፡ አስተናባሪ ፡
አቶ ፡ ወንድወሰን ፡ ኃይሉ ፡	የቋንቋ ፡ ረዳት ።

ስለማንኛውም ፡ አስፈላጊ ፡ ጉዳይ ፡ ጽሑፋችሁን ለዋናው ፡ አዘጋጅ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ የፖስታ/ሣጥን ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፸፮ ፡ አዲስ ፡ አበበ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብላችሁ ፡ ጻፉ ።

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

Published twice annually at the Faculty of Law of Haile Sellassie I University
(to be cited as: 1 J. ETH. L.)

EDITORIAL BOARD

Justice Belatchew Asrat, Chairman

Dr Philippe Graven

Ato Negga Tessema

Ato Nirayo Esayas

Dean James C.N. Paul

Mr. Robert A. Sedler

EDITORIAL STAFF

Mr. Robert A. Sedler, Managing Editor for Administration

Mr. Steven Lowenstein, Managing Editor for Court Reports

Mr. Thomas O. Rose, Court Reporting Editor

Mr. W. Lawrence Church, Press Editor

Mr. Owen P. Cylke, Business Manager

Ato Wondwossen Hailu, Language Assistant

Please address correspondence to the Editor, *Journal of Ethiopian Law*, Box 1176, Addis Ababa, Ethiopia.

ኢዮቤልዩ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡
አዲስ ፡ አበባ ፡

በሀገራችን ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ የተደረገውን ፡ እርምጃ ፡ በተጨማሪ ፡ የሚያስረዳ ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ታትሞ ፡ ሲወጣ ፡ በማየታችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ። ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ጀምሮ ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ቅርስና ፡ ባህል ፡ የተመሠረቱት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችንና ፡ ሌሎችም ፡ በዘመኑ ፡ መንግሥታችን ፡ በየጊዜው ፡ ተሰናድተው ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውሉና ፡ የሕግም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በዘመናዊ ፡ መንገድ ፡ ሲሠራበት ፡ በማየታችን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ። ደጋግመን ፡ እንደገለጽነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በምታደርገው ፡ ፈጣን ፡ የዕድገት ፡ እርምጃ ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ አገልግሎት ፡ ስለሚፈልግ ፡ ሕጉ ፡ በደንብ ፡ እንዲሠራበት ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ ለማስተማር ፡ ይህ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተቋቋመ ። የፍርድ ፡ ቤቶቻችን ፡ የሚሰጡትን ፡ ፍርድና ፡ ስለኢትዮጵያም ፡ ሕግ ፡ የሚገልጡትን ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ አስተያየቶች ፡ የሚገልጽ ፡ መጽሔት ፡ መውጣት ፡ ተጨማሪ ፡ እርምጃን ፡ የሚያስገኝ ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ እንተማመናለን ።

ሕግ ፡ በአንድ ፡ አገር ፡ የአንድነት ፡ ኃይል ፡ ነው ። ዘማናዊ ፡ ሕጎችን ፡ በማውጣት ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ከታቀዱት ፡ ዓላማዎች ፡ አንዱ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችን ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ አንድነት ፡ እንዲመሠረት ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። ሕጉ ፡ በትርጉም ፡ ምክንያት ፡ ሲያጠራጥር ፡ ወይም ፡ በቀጥታ ፡ ሕግ ፡ ያልወጣለት ፡ ጉዳይ ፡ ሲገኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሕጉን ፡ መተርጐምና ፡ በሥራም ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚውል ፡ መወሰን ፡ ይገባቸዋል ። እነዚህም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዶች ፡ በሕግ ፡ አስተዳደር ፡ በኩልና ፡ ለሕግ ፡ ዕድገት ፡ ለሚሠሩ ፡ በሙሉ ፡ መታወቅ ፡ አለባቸው ። የፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዶች ፡ ታትመው ፡ መውጣት ፡ ሕጉን ፡ በበለጠ ፡ እርግጠኛና ፡ ግልጽ ፡ ያደርጉታል ። ይህም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ዕድገት ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ።

ሕጎቹ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በከፊል ፡ የውጭ ፡ አገሮችን ፡ ሕጎች ፡ ቢመረኩዙ ፡ በጠቅላላ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ ፍላጐት ፡ ለማርካትና ፡ የዱሮ ፡ የሕግ ፡ ቅርሷን ፡ ለማጠንከር ፡ የወጡ ፡ ናቸው ። ሕጎቹም ፡ ኃይልና ፡ ብርታት ፡ የሚያገኙት ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሕግ ፡ ፍላጐት ፡ ያረኩና ፡ በባህሏ ፡ የተመሠረቱ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቻችንና ፡ ዳኞቻችን ፡ ሕጎችን ፡ ለመተርጐምና ፡ ለማብራራት ፡ በሙሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕጎችን ፡ መመርኮዝ ፡ የለባቸውም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ልምድና ፡ ባህል ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ብሔራዊ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ አስተያየት ፡ በመስጠት ፡ መጐልመስ ፡ ያሻል ፡ በዚህ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ አማካይነት ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ስለአንቀጾች ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉምና ፡ በሥራ ፡ ላይም ፡ እንዴት ፡ እንደሚውሉ ፡ ሐሳባቸውን ፡ ያበረክታሉ ፡ በዚህም ፡ ዓይነት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የማያጋጥሟት ፡ የሕግ ፡ ችግሮች ፡ መፍትሔ ፡ ያገኛሉ ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ። ይህ ፡ መጽሔት ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ የሚደረጉትን ፡ ከፍተኛ ፡ ጥናቶችና ፡ ምርምሮች ፡ እያጠራቀመ ፡ በማውጣት ፡ ለሕግ ፡ ተማሪዎችና ፡ ሠራተኞች ፡ ተጨማሪ ፡ ዕውቀት ፡ የሚያበረክት ፡ ይሆናል ።

ይህ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንና ፡ በውጭ ፡ አገርም ፡ በብዛት ፡ እንባቢ ፡ እንደሚያገኝ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። ሕግ ፡ በዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ዘንድ ፡ ዋና ፡ ማሠልጠኛ ፡ መሣሪያ ፡ ነው ። ይህ ፡ መጽሔት ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ለሚደረገው ፡ ጥናት ፡ በተጨማሪ ስለሚረዳ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሲሆን ፡ በዓለምም ፡ የጥናት ፡ ሸንጐ ፡ ተገቢ ፡ ቦታውን ፡ ያገኛል ።

ስለዚህ ፡ ይህንን ፡ የመጀመሪያውን ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ እንዲወጣ ፡ ስናደርግ ፡ ደስ ፡ እንዳለን ፡ ወደፊትም ፡ እንደዚሁ ፡ በየጊዜው ፡ የሚወጣው ፡ መጽሔት ፡ የምናስበውን ፡ ያህል ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ እንዲሆን ፡ ጽኑ ፡ ምኞታችን ፡ ነው ።

ግንቦት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም.

ቀ. ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ን. ነ.

JUBILEE PALACE
ADDIS ABABA

It is with great satisfaction that We witness the publication of the inaugural issue of the Journal of Ethiopian Law, which marks still another step forward in the legal development of Our country. During Our reign we have been pleased to see the Constitution and the other laws which We have proclaimed, the implementation of those laws and the modernization of the legal system, all of which have proceeded in light of Ethiopia's rich legal heritage beginning from the Fetha Negast. Since, as We have observed, Ethiopia's rapid progress demands the services of a large number of legal experts, a Faculty of Law has been established to educate persons capable of insuring the effective application of the law. We hope that further progress will be achieved by the creation of a law journal containing reports of the decisions of Our courts and commentary upon the law of Ethiopia.

Law is a unifying force in a nation; one of the goals sought to be attained by the enactment of modern codes and other legislation is that the law be uniform throughout the Empire. Where the meaning of provisions of the law is doubtful or a question arises that is not expressly covered by the law, it is necessary that the courts interpret the law and decide upon its application. These judgments of the courts must be known to all engaged in the administration of justice and the study of the law. The publication of court decisions will serve to make the law more certain, and thus will be a valuable contribution to the legal system of Ethiopia.

The Codes, though drawing in part on foreign sources, were drafted to accord with Ethiopia's needs and ancient legal tradition. The foundation of the Codes lies in the feeling of the people as to what is just. This being so, Our courts and

judges cannot rely exclusively on foreign sources in interpreting the Codes. The national character of Ethiopian Law demands that Ethiopian Commentary upon the law be developed. We hope that through the medium of the Law Journal, legal experts, both Ethiopian and foreign, can express their views as to the meaning of the provisions of the Codes and propose solutions to legal problems likely to confront Ethiopia. The Law Journal can serve as the vehicle by which writings explaining the law of Ethiopia can be published and made available.

We hope that this Journal will be widely circulated throughout the Empire and abroad. Law is an instrument for civilizing the peoples of the world. We hope that the publication of this Law Journal will add to the study of Ethiopian Law. And We hope that this Law Journal will find its appropriate place in the international literature of laws.

It is, therefore, with great pleasure that We inaugurate the publication of the Journal of Ethiopian Law. We earnestly hope that future publications of this Law Journal will give the desired fruits.

HAILE SELLASSIE I

ማውጫ ፡

	ገጽ ፡
ስለ ፡ መጽሔቱ ፡ መቋቋም ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ ቃል ፡ .	iv
ለቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ማውጫ ፡	ix
የጉዳይ ፡ መግለጫዎች ፡	3
አንቀጾች ፡	
ጋብቻ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በዊሊያም ፡ ቡሐጂያር ፡	43
የሕንች ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ ደረጃ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በጂ ፡ ቻችኖቪች ፡	103
የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ በፊሊፕ ፡ ግራቨን ፡	119

TABLE OF CONTENTS

	Page
Inaugural Statement by His Imperial Majesty	vi
Table of Cases Reported	x
Case Reports	6
Articles :	
Marriage under the Civil Code of Ethiopia *by William Buhagiar*	73
Hierarchy of Laws in Ethiopia *by G. Krzeczunowicz*	111
Joinder of Criminal and Civil Proceedings *by Philippe Graven*	35

ለቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ማውጫ ፡

የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡

	ገጽ
ከሳሾች ፡ ፋኩንዶና ፡ (ፍራንስስኮ ፡) ትራንዝዮ ፡ (ጊያደኒ) ፡ ተከሳሾች ፡ ፐድሬቶ ፡ (ጁሴፔ) የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቊጥር ፡ ፩፻፲፫/፶፱ ዓ. ም.	3
ከሳሽ ፡ ጌታቸው ፡ ግዛው ፡ መልስ ፡ ሰሚ ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ቊጥር ፡ ፶፰/፶፩ ዓ. ም.	9
ከሳሽ ፡ ወይ/ ወርቅነሽ ፡ በዛብህ ፡ ተከሳሽ ፡ ወይ ፡ ይደነቁ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቊጥር ፡ ፳፻፹፫/፶፰ ዓ. ም.	15
ከሳሽ ፡ አቫኪያን ፡ (ሻኬ) ፡ ተከሳሽ ፡ አቫኪያን ፡ (አርቲን) ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቊጥር ፡ ፩፻፩፻፲፬/፶፰ ዓ. ም.	23

ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡

አቫኪያን ፡ (ሴትራክ) ፡ ስለውርስ ፡ ንብረት ፡ የውርስና ፡ የአስተዳደር ፡ ነገር ፡ ቊጥር ፡ ፻፯ ፶፰ ዓ. ም.	30
ከሳሽ ፡ ማሞ ፡ ይንበርበሩ ፡ ተከሳሽ ፡ ይርጉ ፡ አበበ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ ቊጥር ፡ ፩፻፶፬/፶፰ ዓ. ም.	34

TABLE OF CASES REPORTED

Supreme Imperial Court

Avakian, Chake v. Artin Avakian (Civil Appeal No. 1114/55 E.C.) . . 26

Facondo, Francesconi and Ghiandoni Trenzio v. Pedretto Giuseppe ix
(Civil Appeal No. 413/49 E.C.) 6

Getatchew Gizaw v. The Advocate General (Criminal Appeal
No. 95/51 E.C.) 11

Workinesh Bezabih v. Woz. Yidenekou (Civil Appeal No. 883/55 E.C.) 17

High Court

Avakian, Setrak, In the Matter of the Estate of:
(Probate and Administration Case No. 107/55 E.C.) . . . 32

Mammo Yinberberu v. Yirgu Abebe (Civil Case No. 454/55 E.C.) . . 96

<u>መግለጫዎች ።</u>

የሚከተሉት ፡ ስድስት ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ ጉዳዮች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ። የአማርኛው ፡ ፍርድ ፡ መደበኛ ፡ (ኦፊሻል ፡) ስለሆነ ፡ ከእንግሊዝኛው ፡ ቀድሞ ፡ ይገኛል ። ስለነዚህም ፡ በኢትዮጵያውያንና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ዳኞች ፡ መካከል ፡ ስለተወሰኑት ፡ ጉዳዮች ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ሁለት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየቶች ፡ መጻፋቸውን ፡ ማስተዋል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ አስተያየቶች ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ የተተረጐሙ ፡ አይደሉም ። እያንዳንዱ ፡ ፍርድ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ቢሆንም ፡ በዳኞች ፡ መካከል ፡ ስለሥራ ፡ ነገሩና ፡ ስለመጨረሻው ፡ ውሳኔ ፡ ስምምነት ፡ አለ ። ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ውሳኔዎችን ፡ አትሞ ፡ ማውጣት ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሕግ ፡ አስተዳደር ፡ በኩል ፡ ላሉ ፡ ሁሉ ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ ይደረግበታል ።

REPORTS

The following are six cases decided by the Supreme Imperial and the High Courts of Ethiopia. The Amharic judgment is official and always precedes the English. It is important to note that in those cases heard before mixed benches of both Ethiopian and foreign judges, two separate opinions are written, one in Amharic and one in English. These opinions are not translations of one another, but are independent judgments based upon common agreement among the judges as to the principles and final outcome of each case. It is hoped that the publication of significant decisions will be of great value to those engaged in the administration of justice in Ethiopia.

የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡

ክፍል ፡ ሰ

ከሳሾች ፡ ሚስተር ፡ ፍራንቸስኮ፡ ፋኮንዶና ፡ ሚስተር ፡ ሪያንዶ፡ ትራንዚዮ ፡
ተከሳሽ ፡ ሚስተር ፡ ፔድሬቲ ፡ ጁሴፔ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ 413/49 ዓ ፡ ም ።

የግዴታዎች፡ሕግ-ንግድን፡ስለመወሰን፡
ስለሚደረግ፡ውል-የንብረትን፡ጥቅም ፡
ለመጠበቅ፡ካልሆን፡በቀር፡ፈራሽ፡ነው ፡
ተብሎ፡ስለሚገመት፡ውል-ተገቢነት ፡
የማያስከትለው፡የሕግ፡ጥያቄ።

ሽርክነታቸውን፡ሲያፈርሱ፡በተደረገው፡ውል፡አንቀጽ፡7 መሠረት፡መልስ፡ሰጭ፡ለይግባኝ፡ባዩ፡ለወደፊት፡በድሬዳዋ፡ጋራዥ፡ወይም፡ሌላ፡መሥሪያ፡ቤት፡እንዳያቋቁምና፡ተቀጥሮ፡እንዳይሠራ፡ፈርሟል ።

<u>ፍርድ፤</u> ይህ፡በንግድ፡ሥራ፡ነፃነት፡እንዳያወጣ፡ተብሎ፡የተደረገው፡ውል፡በጊዜ፡ያልተወሰነና፡የይግባኝ፡ባዩን፡ጥቅም፡ለመጠበቅ፡ከሚደረገው፡በላይ፡ስለሆነ፡ፍርስ፡ነው። ይህ፡ፍርድ፡ከተሰጠ፡በኋላ፡መስከረም፡1 ቀን፡1953 የወጣው፡የፍትሐ፡ብሔር፡ሕግ፡አንቀጽ፡1715 ም፡ይህንኑ፡ውሳኔ፡ይደግፋል ።

ሐምሌ ፡ 1 ቀን ፡ 1950 ፡ ዓ ፡ ም ። ዳኞች ፤ በላምበራስ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ የሸዋ ሀነ ፡ (ምክትል ፡ አፈንጉሥ ፡) ዶክተር ፡ ቡሐር ፤ አቶ ፡ መኩሪያ ፡ ዳመና ፡ በሁሉቱም ፡ በኩል ፡ የቀረበውን ፡ ማመልከቻና ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ በ556/48 ቍጥር ፡ መዝገብ ፡ የፈረደውንም ፡ ተመልክተናል ።

ክርክሩም ፡ በድሬዳዋ ፡ በሽርክና ፡ የቆመው ፡ ጋራዥ ፡ ስለመከፋፈሉ ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ነው ። መልስ ፡ ሰጭው ፡ የሚፈልገው ፡ ድርሻው ፡ እንዲከፈለው ፡ ነው ። የሽርክናውም ፡ ስምምነት ፡ መፍረሱ ፡ ተገልጾአል ። በስምምነቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውም ፡ 7ኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ሚስተር ፡ ፔድሬቲ ፡ ወደፊት ፡ በድሬዳዋ ፡ የመኪና ፡ ማደሻ ፡ ወይም ፡ ጋራዥ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ወይም ፡ ተራ ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ሽርክና ፡ ሆነው ፡ እንዳይሠሩና ፡ እንዳያሠሩ ፡ ተዋውለዋል ። በጥጥ ፡ ፋብሪካና ፡ በኢትዮጵያና ፡ በፈረንሳይ ፡ የምድር ፡ ባቡር ፡ ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሆነው ፡ ሊሠሩ ፡ ይችላሉ ።

መልስ ፡ ሰጭው ፡ ውሉን ፡ አፍርሶ ፡ በድሬዳዋ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ የጋራጅ ፡ ሥራ አቋቁሞ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እላይ ፡ የጠቀሰው ፡ ውል ፡ (7ኛው)አንቀጽ ፡ ስለማይጸና ፡ ኪሣራ ፡ ሊከፈል ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ ወሰነ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ይግባኝ ፡ ብለዋል ። ሰባተኛውን ፡ አንቀጽ ፡ የሚመስሉ ፡ ንግድን ፡ የሚወስኑ ፡ ማለት ፡ ይህን ፡ ይህን ፡ እንዳይሠራ ፡ የሚሉ ፡ ውሎች ፡ ተጠቅሰዋል ። ይህን ፡ የመሰሰሉት ፡ ውሎች ፡ የሕዝብ ፡ ተቃራኒዎች ፡ ናቸው ። እንዲሁም ፡ የንግዱን ፡ አከላከልና ፡ አወሳሰን ፡ በለጥቅሙን ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ሳይገኝ ፡ ወይም ፡ ለተከለከለው ፡ ሰው ፡ ጠቃሚ ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ ጠቃሚ ፡ ካልሆነ ፡ ውሉ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ።

የንግድ ፡ አከላከልና ፡ አወሳሰን ፡ ለሁለት ፡ ይከፈላሉ ፡ ይህም ፡ የነርሱ ፡ስምምነት ፡ ነው ። አንደኛው ፡ ስምምነት ፡ ሽርክናው ፡ ወይም ፡ በትምህርት ፡ ምክንያት ፡ የሚሠራው ፡ የአገልግሎቱ ፡ ውል ፡ ከአለቀ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ በአንደኛው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ ነው ። ሁለተኛው ፡ ስምምነት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ንግዱን ፡ በሸጠ ፡ ጊዜ ፡ ሸጬን ፡ ለመፎከከር ፡ ተመሰሳዩን ፡ ንግድ ፡ እንዳያቆም ፡ የሚደረገው ፡ ነው ።

ይህን ፡ የመሰሰሉት ፡ ስምምነቶች ፡ ሕዝብን ፡ የሚጐዱ ፡ ስለሆነ ፡ አይጸኑም ፡ ምክንያቱም ፡ ሰው ፡ በገንዘቡ ፡ እንዳይሠራና ፡ እንዳይጠቀም ፡ በሚጠቀምበት ፡ ጊዜ ፡ እንዳይሠራ ፡ የሚከለክሉ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

አንዳንድ ፡ የንግድ ፡ አወሳሰንና ፡ አከላከል ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ነው ። ሸጬ ፡ እንዳይፎከከረው ፡ ሳይከለከል ፡ የንግዱን ፡ ሥራ ፡ የሚገዛ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የለም ። አንድ ፡ ጌታ ፡ አስተምሮ ፡ የሚያሠራውን ፡ ወይም ፡ ጸሐፊውን ፡ ወይም ፡ ሌሎቹን ፡ አሽከሮች ፡ ቀጥሮ ፡ በእምነት ፡ ቦታ ፡ ለማኖር ፡ አይደፍርም ። ይህንም ፡ የሚያደርገው ፡ አሽከሮቹ ፡ ከርሱ ፡ ወጥተው ፡ የርሱን ፡ ልማድ ፡ ይዘው ፡ አጠገቡ ፡ ሥራ ፡ የጀመሩና ፡ እርሱንም ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ የጣሉት ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ነገሮች ፡ እንዳያደርግ ፡ የገዥና ፡ የጌታን ፡ የበለቤትነት ፡ መብት ፡ ለመጠበቅ ፡ ሕዝባዊው ፡ ሁኔታ ፡ ይከለክለዋል ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የሚከላከልበት ፡ የለም ። በለጥቅሙን ፡ ለማዳን ፡ ከአስፈላጊው ፡ በላይ ፡ የሚደረገው ፡ የንግድ ፡ እግድ ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆነ ፡ ችግርን ፡ የሚፈጥር ፡ ነው ። ይህም ፡ ለማናቸውም ፡ መልክም ፡ አይደለም ። የንግድን ፡ ጥቅም ፡ በመሸጥ ፡ ላይ ፡ ከሚደረጉት ፡ ውሎች ፡ ይልቅ ፡ አንድ ፡ ተቀጣሪ ፡ ወይም ፡ አሽከር ፡ እንዳይፎከከር ፡ በሚደረገው ፡ ውል ፡ የሚቀርበው ፡ ምክንያት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ንግድን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገርን ፡ ሲገዛ ፡ ሸጬ ፡ ያንኑ ፡ የመሰለውን ፡ ሥራ ፡ አጠገቡ ፡ አቋቁሞ ፡ በፉክክር ፡ እንዳያከስረው ፡ ከዚህ ፡ የሚድንበትን ፡ ውል ፡ ሊዋዋል ፡ ይችላል ። ይህን ፡ የመሰለው ፡ ውል ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከአለው ፡ ሊከለከል ፡ አይችልም ።

ያለስምምነት ፡ ገዥው ፡ ሊገዛው ፡ የተዋዋለውን ፡ ለማግኘት ፡ ሻጬም ፡ ሊሸጠው ፡ የተዋዋለውን ፡ ለመስጠት አይችሉም ። ይህን ፡ ያለው ፡ ሎርድ ፡ ፓርከር ፡ እይግባኝ ፡ ፍ/ቤት ፡ በ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (፲፱፻፳፫) በሞረስና ፡ በአኬልቢ ፡ መከከል ፡ ስለነበረው ፡ ክርክር ፡ ነው ። አንድ ፡ ቀጣሪ ፡ ሠራተኛ ፡ ሲቀጠር ፡ የሥራው ፡ ጊዜ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ አቋቁሞ ፡ እንዳይፎከከረው ፡ ከሠራተኛው ፡ ጋር ፡ ቢዋዋል ፡ ይህ ፡ የተደረገው ፡ ፉክክሩን ፡ ለመከልከል ፡ ወይም ፡ ሠራተኛው ፡ ከሚሠራበት ፡ በአገኘው ፡ እውቀት ፡ እንዳይጠቀምበት ፡ ለማድረግ ፡ እንደሆነ ፡ ይህን ፡ የመሰሰለው ፡ ውል ፡ ተደጋፊ ፡ አይሆንም ፡ የቀጣሪው ፡ ወይም ፡ የአሠሪው ፡ ምስጢር ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ግንኙነት ፡ እንዳይታወቅ ፡ መብቱ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ ከአስፈላጊው ፡ በላይ ፡ የወጣ ፡ እንደ

ሆነ ፡ ውሉ ፡ አይፀናም ። ስለዚህ ፡ የንግድን ፡ ሥራ ፡ የሚገዛ ፡ ከሽጩ ፡ ፋክክር ፡ በውል ፡ ለመዳን ፡ ይችላል ። አሠሪ ፡ ወይም ፡ ቀጣሪ ፡ ግን ፡ ሠራተኛው ፡ ሲሠራ ፡ በአገኘው ፡ ዕውቀት ፡ ቢፎካከረው ፡ ማለት ፡ ሥራ ፡ ከፍቶ ፡ በውል ፡ ሊከለክለው ፡ አይችልም ። ምክንያቱም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ መከልከል ፡ የሕዝብ ፡ ተቃራኒ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታ ፡ በመመልከት ፡ ሥራው ፡ ከመቸ ፡ እስከ ፡ መቸ ፡ ተብሎ ፡ የተወሰነበትን ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ እንደዚሁም ፡ በጠቅላላው ፡ የክሱን ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ መመርመር ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። የንግዱን ፡ ሥራ ፡ ለማዳን ፡ የተደረገ ፡ መሆኑን ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ሥራው ፡ የታገደው ፡ ባለጥቅሙ ፡ ነው ። እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ እንዳይሠራ ፡ የታገደበትን ፡ ጊዜና ፡ የመሥሪያውን ፡ ቦታ ፡ ስፋትና ፡ ርዝመት ፡ ለማጣራት ፡ ለተዋዋዩ ፡ አስቸጋሪ ፡ ይሆናል ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደሚመስለው ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ በድሬ ፡ ዳዋ ፡ ከ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በቀሩት ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ኢጣሊያኖች ፡ መካከል ፡ እንዲኖር ፡ ተፈቅዶለታል ።

ይህ ፡ በቦታው ፡ ተወስኖ ፡ ስምምነቱን ፡ ሊያፈርሰው ፡ አይችልም ። ይህ ፡ የተገለጸው ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ ስምምነቱን ፡ ወዶ ፡ በፈረመ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየት ፡ የይግባኝ ፡ ባይዎችን ፡ መብት ፡ ለመጠበቅ ፡ ተብሎ ፡ የተደረገው ፡ እግድ ፡ ከአስፈላጊው ፡ በላይ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በይግባኝ ፡ ባይዎችና ፡ በመልስ ፡ ሰጭዎች ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት ፡ ንግድን ፡ ለመሸጥ ፡ አይደለም ፡ ይህ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከተፎካከረ ፡ መብታቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ ለማገድ ፡ ይቻላል ። ደግሞ እግዱ ፡ በጊዜ ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ፡ ይግባኝ ፡ ባይዎችም ፡ እግዱ ፡ ሥራቸውን ፡ ለማዳን ፡ ከተፈለገው ፡ በላይ ፡ እንዳይወጣ ፡ መደረጉን ፡ አልገለጹም ። ስለዚህ ፡ በስምምነቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ፯ኛው ፡ አንቀጽ ፡ የሥራንና ፡ የንግድን ፡ መብት ፡ የሚከለክል ፡ ስለሆነ ፡ ሊጸና ፡ አይችልም ፤ ይግባኝ ፡ ባይዎችም ፡ በመልስ ፡ ሰጭዎች ፡ በኩል ፡ ፯ኛው ፡ አንቀጽ ፡ በለመጠበቁ ፡ ይህን ፡ ጉዳት ፡ እንዳስከተለባቸው ፡ የሚገልጽ ፡ ማስረጃ ፡ አላቀረቡም ። ስለዚህ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደውን ፡ አጽንተናል ። ይግባኙን ፡ አልተቀበልንም ። ኪሣራ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ይክፈል ፡ ብለናል ፡ እንዲያውቀው ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይጻፍ ፡ በ፩(፲፩)ሺ ፡ ተወሰነ ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Div. B

FRANCESCONI FACONDO & GHIANDONI TRENZIO v. PEDRETTI GIUSEPPE

Civil Appeal No. 413/49

Law of Obligations -- Agreement in restraint of trade -- Presumption of invalidity unless reasonable to protect proprietary interest -- Reasonableness a question of law.

By Clause VII of an agreement dissolving their partnership, respondent promised appellants not to open or sell his labour to any workshop in Dire Dawa in the future.

Held: Since this restriction upon competition is unlimited as to time and does not purport to afford merely reasonable protection to appellants' business interests, it is void. (Art. 1715 of the Civil Code, which went in force Maskaram 1, 1953, after this decision was rendered, calls not the same conclusion.)

Hamle 1, 1950 E.C. (July 8, 1958 G.C.); Justices: Vice Afenegus Haile Mariam Yeshoneh, Dr. W. Buhagiar, Ato Mekuria Damena: -- This appeal arises out of the severence of a partnership which was established for the purpose of running a garage at Dire Dawa.

The respondent in this case wished to be paid out his share, and accordingly an agreement of dissolution of partnership was drawn up. Clause VII of the said agreement reads as follows:

> VII). Mr Pedretti binds himself not to open, in the future, any workshop in Dire Dawa for the repair of machineries and vehicles, or not to be employed in any private workshop as director, or as an ordinary worker or as partner. He can only be employed in Government administrative factories, as the Cotton Factory, or the Franco-Ethiopian Railway Co.

The respondent in breach of his agreement again set up in the garage business in Dire Dawa with another. The High Court held that Clause VII of the agreement was invalid and that no damage could arise. Against this decision the appellants have appealed.

Clauses similar to Clause VII are commonly referred to as contracts in restraint of trade; such contracts are contrary to public policy and invalid unless:

(A) the restraint is reasonably necessary for the protection of the person in whose interest it is imposed;

(B) the restraint is reasonably in the interests of the party restrained; and

(C) the restraint is reasonable in the interests of the public.

For the purposes of this appeal agreements in restraint of trade may be classified in two kinds:

(A) agreements imposing on one of the parties restrictions in the exercise of his calling after the termination of partnership or apprenticeship articles or contracts of service; and

(B) agreements by persons selling the good will of a business not to carry on a similar business so as to compete with the purchaser.

All agreements of this kind are *prima facie* void as being contrary to public policy, for it is contrary to public policy that a person should be restrained from disposing of his labour and his capital freely and to the best advantage, and from conducting his business in the most profitable way. But some restraint may also be justified by public policy. Nobody would buy the good will of a business unless he could prevent the vendor from at once setting up a competing business on his own account. A master would be discouraged from taking apprentices and employing clerks and other servants in positions of confidence if he ran the risk of the servant or apprentice setting up on his own account next door and acquiring the customers of his late master. Hence, public policy allows of contracts which restrain a person from doing these things, *to the extent necessary to protect the proprietary rights of the purchaser or the master, but no more.* Any restraint which is greater than is reasonably necessary to protect the person in whose interest it is imposed is unnecessary hardship and does no good to any one.

The test of reasonableness is considerably stricter in cases of covenants restraining a servant's competition than in those of covenants entered into on the sale of goodwill. On the sale of a business the purchaser is entitled to be protected from the risk that the seller may set up a new business to the detriment of the old one, and covenants designed to prevent such competition are not objectionable if they are reasonably necessary to secure this protection.

"Without such a covenant, a purchaser would not get what he is contracting to buy, nor could the vendor give what he is intending to sell" -- per Lord Parker in Morris v. Axelby (1916) A.C. 688. On the other hand, where an employer takes a covenant from an employee restraining the latter from carrying on a competing business after the termination of the employment,

such a covenant will not be upheld if it is directed only to the prevention of competition, or against the use of the personal skill and knowledge acquired by the employee in the business. It will be void, in other words, if it goes further than is reasonably necessary for the protection of the proprietary rights, such as a trade connection, or the trade secrets of the employer. A purchaser of a business is, therefore, entitled to protect himself from competition *per se*, an employer is not, for it is contrary to public policy that a servant should be restrained from using his own skill and ability in competition with his late master.

Reasonableness is in every case a question for the Court, looking at the nature of the business, the length of time during which the restraint is imposed, the area of the restraint, and all the circumstances of the case. But the onus is on the person for whose benefit the restraint is imposed, to show that it goes no further than is required for the protection of his business. The longer the time of the restriction, the wider its space of operation, the greater will be the difficulty of the covenantee in justifying it.

In the opinion of this Court, the fact that the respondent was granted residence only in Dire Dawa amongst the 500 Italians who remained in Ethiopia after the Restoration in the year 1941 G.C. does not in itself amount to a justification as to render the agreement null and void as being a general restriction in space: this fact was known to the respondent when he signed the agreement which he did willingly. In the opinion of this Court, however, the restriction goes further than is necessary for the protection of the appellants' rights for two reasons:

(A) because the agreement between the appellants and the respondents was not an agreement for the purchase of goodwill so as to entitle them to the protection of their proprietary rights and to protect themselves from competition *per se*, and

(B) because the restriction is unlimited in time and the appellants have not shown that this restriction as to time goes no further than is required for the protection of their business.

For the above reasons we hold that Clause VII of the agreement is null and void as being in restraint of trade. We may also add that the appellants have adduced no evidence to show that the non-observance of Clause VII on the part of the respondent has caused them any loss.

We, therefore, dismiss the appeal and confirm the judgment of the High Court. Appellants to pay respondent Advocate's fee of $100.

የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

ክፍል ፡ ፬

ተከሳሽ ፡ ወታደር ፡ ጌታቸው ፡ ግዛው ። ከሳሽ ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ።

የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ 95/51 ፡ ዓ ፡ ም ።

የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ኃላፊ ፡ አለመሆን ፡ — የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ፵፰ና ፡ ፵፱ — ግልፍተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ። (ማይክፓቲክ) ፡ —

፩ ፡ ግልፍተኛ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ማይክፓቲክ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ቢያነፃፅሩት ፡ ግልፍተኛነቱን ፡ ለመግታት ፡ የማይችል ፡ በመሆኑ ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ቢሠራ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ፵፰ና ፡ ፵፱ ፡ መሠረት ፡ ለሠራው ፡ የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ኃላፊነቱ ፡ የማይቀርለት ፡ ነው ።

የካቲት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዳኞች ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ ታከለ ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡ ዶክተር ፡ ቡሐጀር ፡ ብላታ ፡ በቀለ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ። — ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ወታደር ፡ ጌታቸው ፡ ግዛው ፡ ይግባኙን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀረበበት ፡ ምክንያት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በወንጀል ፡ ፋይል ፡ ቍጥር ፡ ፩/፶፩ ፡ በተከፈተው ፡ ፋይል ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ጺጋዬ ፡ ጌታነህን ፡ ገድሏል ፡ በማለት ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ስለፈረደበት ፡ ነው ። ፩ኛው ፡ ዳኛ ፡ በአነስተኛ ፡ ድምፅ ፡ ተለይተው ፡ በእድሜ ፡ ልክ ፡ እስራት ፡ እንዲታሰር ፡ ሲሉ ፡ ሐሳብ ፡ ሰጥተዋል ።

የነገሩን ፡ አኳኋን ፡ ስንመረምር ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍድ ፡ ቤርት ፡ ከመጣው ፡ የመዝገብ ፡ ትክክል ፡ ግልባጭ ፡ ዋናውንም ፡ መዝገብ ፡ በውስጥ ፡ አስመጥተን ፡ አንብበን ፡ እንደተረዳነው ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተከሳሹ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ በቁጥር ፡ ፫፻፷፱ ፡ እና ፡ በቁጥር ፡ ፳፮ ፡ የተጻፈውን ፡ ሕግ ፡ ተላልፎ ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ ወታደር ፡ ሆኖ ፡ ስለዘብ ፡ ሥራው ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እንዲወጣ ፡ ከበላይ ፡ አለቃው ፡ ታዞ ፡ እንደታዘዘው ፡ ደንበኛ ፡ ድርጅቱን ፡ ሳያደርግ ፡ በዘብ ፡ መሰለፊያው ፡ ሥፍራ ፡ ተገኝቶ ፡ ስለዘቡ ፡ ኃላፊ ፡ የሆነው ፡ ሟቹ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ጺጋዬ ፡ ጌታነህ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ሳትዘጋጅ ፡ መጣህ ፡ ለዘብ ፡ የተሰጠህን ፡ ጫማና ፡ ልብስ ፡ ለምን ፡ አልለበስክም ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቀው ፡ ተከሳሹ ፡ ፈቃደኛ ፡ ሆኖ ፡ ቅጉን ፡ በመመለስ ፡ ፈንታ ፡ ጫማም ፡ መለዮም ፡ የለኝ ፡ አልገባም ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ሟቹ ፡ ዛሬ ፡ ወታደር ፡ ጉድኋልና ፡ መሣሪያ ፡ ከግምጃ ፡ ቤት ፡ አውጣ ፡ ብሎ ፡ አዘት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ከግምጃ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ መሣሪያውን ፡ አውጥቶ ፡ ከዘብ ፡ መሰለፊያው ፡ ቦታ ፡ ቆሞ ፡ ሳለ ፡ ሟቹ ፡ በተሰለፉት ፡ የዘብ ፡ ወታደሮች ፡ ግምባር ፡ ሲሄድ ፡ ከወደኋላው ፡ አንድ ፡ እርምጃ ፡ አልፎ ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ በጥይት ፡ ተኩሶ ፡ በጀርባው ፡ በኩል ፡ እሺንጡ ፡ ላይ ፡ ጥይት ፡ ተኩሶ ፡ መትቶ ፡ ገድሎታል ፡ ተብሎ ፡ ተከሶ ፡ ቀርቦ ፡ ቢጠየቅ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ብሎ ፡ የእምነት ፡ ክደት ፡ ቃሉን ፡ ሰጥቷል ።

በከሳሹ ፡ በሕግ ፡ አስከብረው ፡ በኩል ፡ ምስክሮች ፡ ተቆጥረው ፡ ቀርበው ፡ ቃላቸውን ፡ ሰጥተዋል ። በመሰከከራቸውም ፡ ተከሳሹን ፡ ያሁኑን ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አልደገፉትም ፡ ወንጀሉን ፡ መስራቱን ፡ አረጋግጠው ፡ መስክረውበታል ።

በተከሳሽነቱ ፡ ስለመከላከያው ፡ የተቆጠሩት ፡ ምስክሮች ፡ የሚደገፉበትን ፡ ምክንያት ፡ አልገለጹለትም ፡ ይልቁን ፡ ከሟቹ ፡ ጋር ፡ ጠብ ፡ እንደነበረውና ፡ ቂም ፡ የያዘ ፡ መሆኑን ፡ ለይተው ፡ ገልጸውበታል ። የተከሳሹ ፡ ያሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ጠበቃ ፡ የ[illegible]ማ ፡ ምስክሮች ፡ የመሰከሩትን ፡ ያነጋገራቸውን ፡ ከተረዳው ፡ በኋላ ፡ ምስክሮቹን ፡ አጥብቆ ፡ ከመጠየቅ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ ለመደገፍና ፡ ከተከሰሰበት ፡ ወንጀል እንዲያመልጥ ፡ ማምለጫ ፡ ሰርጥ ፡ መንገድ ፡ በመፈለግ ፡ ተከሳሹ ፡ ያሁኑ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አንጐሉ ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፡ ደግሞም ፡ ድንገት ፡ የሚጥለው ፡ በሽታ ፡ አለበትና ፡ በሐኪም ፡ ይመርመር ፡ ብሎ ፡ ምክንያት ፡ ሰጥቷል ፡ ስለዚሁም ፡ የአንጐልና ፡ የአዕምሮ ፡ ጉድለት ፡ ሐኪም ፡ ተጠርቶ ፡ ቀርቦ ፡ አንጐሉ ፡ ትክክል ፡ መሆኑን ፡ የአንጐል ፡ መናወጽ ፡ ሕመም ፡ የሌለበት ፡ መሆኑን ፡ ገልጾ ፡ ከመሰከረ ፡ በኋላ ፡ ሳይኮፓት ፡ የተባለ ፡ ድንገት ፡ ግልፍ ፡ የሚአደርግ ፡ ጠባይ ፡ አለበት ፡ ይኸውም ፡ ሲናገሩት ፡ ወይም ፡ ሲሰድቡት ፡ ድንገት ፡ የሚአስነሳው ፡ ልምድ ፡ መሆኑን ፡ ጨምሮ ፡ አስረድቷል ።

ግልፍተኛነት ፡ ከአንጐል ፡ መናወጽ ፡ የማይገናኝ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ለሚሠራው ፡ ነገር ፡ ኃላፊ ፡ አይሆንም ፡ የሚአሰኝ ፡ ምክንያት ፡ እንደሌለበት ፡ ሐኪሙ ፡ ገልጾታል ።

ጠበቃው ፡ ሁለተኛ ፡ የሰጠው ፡ ምክንያት ፡ ድንገት ፡ የሚጥለው ፡ በሽታ ፡ አለበት ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ስለዚሁ ፡ ሲከላከል ፡ የተከሳሹን ፡ ያሁን ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ እናትና ፡ ሚስት ፡ አክስት ፡ ምስክር ፡ ቆጥሮ ፡ በመሰከከራቸው ፡ ተከሳሹን ፡ ለመደገፍ ፡ ያደረጉት ፡ ከመሆኑ ፡ በተቀር ፡ ምስክርነታቸውን ፡ ልንቀበለው ፡ አልቻልንም ። ደግሞም ፡ አብረውት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠሩ ፡ የሥራ ፡ ተባባሪዎቹ ፡ የድንገተኛው ፡ በሽታ ፡ ሲጥለው ፡ አላየንም ፡ ብለው ፡ መስክረዋልና ፡ የተከሳሽን ፡ ቅርብ ፡ ዘመዶች ፡ ምስክርነት ፡ አፍርሶታል ። ስለዚሁም ፡ ድንገት ፡ ስለሚጥል ፡ በሽታ ፡ ነገር ፡ ሐኪሙ ፡ የለበትም ሲል ፡ የመሰከረው ፡ ቃል ፡ በቂ ፡ ሆኗል ፡ ስለተከሳሹ ፡ መከላከያ ፡ አዲስ ፡ በወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ደንብ ፡ በቍጥር ፡ ፵፰ ፡ እና ፡ ፵፱ ፡ የተጻፉት ፡ ሕጎች ፡ ተጠቅሰዋል ። እነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ ተከሳሹን ፡ የሚደግፉት ፡ ሳይሆኑ ፡ አዕምሮአቸው ፡ ሳልበሰለ፡ያንጐል ፡ መናወጽ ፡ ሕመም፡ላለባቸው፡የሚአደርጉትን፡ነገር ፡ ሊያውቁ፡ ለማይችሉ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ተከሳሹ ፡ ከግልፍተኛነት ፡ በተቀር ፡ ሌላ ፡ ያንጐል ፡ መናወጽ ፡ ወይም ፡ የአዕምሮ ፡ ጉድለት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ አዋቂው ፡ ሐኪም ፡ አረጋግጦ ፡ ስለመሰከረበት ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ከሟቹ ፡ ጋር ፡ ጠብ ፡ የነበረውና ፡ ቂም ፡ የያዘ ፡ መሆኑን ፡ ምስክሮች ፡ ጨምረው ፡ የመሰከሩበትና ፡ ወንጀሉን ፡ አውቆ ፡ የሠራ ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዳን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፈረደውን ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ አጽንተን ፡ ይግባኙን ፡ አሰናብተናል ። ፍርዱ ፡ የሚፈጸመው ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ካጸኑት ፡ በኋላ፡ ነው ። ስለሐኪሙ ፡ ምርመራ ፡ ሐሳብ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ዶክተር ፡ ቡሐጂያር ፡ በጻፉት ፡ የፍርድ ፡ ግልባጭ ፡ በስፊው ፡ ታትቶ ፡ ይገኛል ። እንዲአውቀው ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይጻፍ ።

(ይህ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፱ና ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፬ ፡ መሠረት ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጸደቀ ። አዘጋጅ—)

SUPREME IMPERIAL COURT

Div. A

Ato GETATCHEW GIZAW v. The ADVOCATE GENERAL

Criminal Appeal No. 95/51 E.C.

Criminal responsibility — Articles 48 and 49 P.C. — Psychopathic personality — Death sentence, Art. 522 P.C.

1. A "constitutional psychopath" who commits an offence due to his inability vis-à-vis normal individuals to control and restrain impulses may not be considered criminally irresponsible under Articles 48 and 49 P.C.

2. Article 48 requires *total and* an absolute inability to regulate conduct according to understanding.

3. An "abnormal or deficient condition" within the meaning of Article 49 must be biologically caused excluding such factors as upbringing and atmosphere of living.

Yekatit 3, 1951 E.C. (February 11, 1959 G.C.); Justices: Afenegus Takelle Wolde Hawariat, Dr. W. Buhagiar, Blatta Bakele Habte Michael: -- This is an appeal against the judgment of the High Court, which found the appellant guilty of homicide in the first degree and by majority sentenced the appellant to death; according to the minority judgment a sentence of rigorous imprisonment for life was considered a more suitable punishment in all the circumstances of the case.

The facts in this case are not contested by the appellant; indeed there can be no doubt whatsoever that the appellant killed Lieutenant Tsigeh Getaneh by shooting him in the back. The only defence in the High Court was, broadly speaking, one of insanity, and expert witnesses were called by the defence to support this plea. The evidence of Dr. Nick A. Capotas, the Medical Director of the Emanuel State Mental Hospital at Addis Ababa, is the relevant and material evidence on the point. The conclusion of this medical expert, who had the appellant under observation, is that the appellant is a "constitutional psychopath". To quote the full final opinion of the expert, the appellant "more especially belongs to the group of the emotionally pathological personalities, characterized by defects in the nature or control of the emotional or

affective function of the personality, impulsive and excitable. The usual amount of stress and strain (physical, psychological, professional, 'military discipline') which, in the average or so-called normal individuals, would not elicit any abnormal reaction, is, for this kind of constitutional psychopathy, too strong, and, owing, either to the increased strength of their instinctual drives or to the inability to appropriately control and restrain them -- may bring about an unusually pronounced tendency to yield to impulses of violence without restraint and thus become dangerous to society,"

The grounds of appeal are substantially --

(a) that the High Court wrongly interpreted the provisions of Articles 48 and 49 in that it confined itself to the consideration and interpretation of the medico-legal phrase "mental disease", an expression which does not appear in those articles;

(b) that the High Court failed to distinguish between abnormalities of the cognition from those of affectivity, a material element which is warranted by both the said Articles 48 and 49;

(c) that the High Court based its decision on the standards of a normal person, which is contrary to Article 51 and also ignored the finding of the expert witness and overlooked the definite finding that the appellant is a "constitutional psychopath".

Now under Article 48 of the Penal Code a person is not responsible for his acts and therefore not punishable if --

(i) at the time of the act he was incapable of understanding the nature or consequences of his act or of regulating his conduct according to such understanding, and

(ii) such state is due to age, illness, abnormal delay in his development or deterioration of his mental faculties

Similarly under Article 49 a person is not liable to the full punishment, because of limited responsibility, if --

(i) at the time of the act, he was not *fully* capable of understanding the nature and consequences thereof or regulating his conduct according to such understanding, and

(ii) such state was due to a derangement of his mind or understanding, or an arrested mental development or an abnormal or deficient condition.

It is correct what the advocate for the appellant pointed out, that is, that neither of these Articles mention "mental diseases"; under these two Articles the irresponsibility or partial responsibility of the offender is based on two

criteria, that is, the psychological criterion affecting the intelligence and the psychological criterion affecting volition. Whether these two criteria form part of the branch of medicine under the general heading of mental diseases or not is too technical a point to settle here; indeed it has no bearing on the final solution of the matter. It may be stated, however, that these two criteria have been introduced in modern legislation as modern medico-legal science has found it necessary to admit the principle of partial responsibility due to certain factors in the human mind and body which produce a state or condition not amounting to insanity, but which form a definite branch of medical psychology. Modern science has made progress in the study of the human mind, its powers and weaknesses, and distinguishes between abnormality of mind, mental responsibility, emotional instability, gross personality disorder, and so forth. The term "psychopath" as used in modern science has not really a definite meaning which indicates exactly the state of mind or of the psycological set-up of a particular person; it is still a vague term and does not indicate a particular state of mind or condition. In this particular case the expert evidence is to the effect that the appellant is more inclined to give way to his instincts than another person who is normally referred to as "normal". He fully understands the nature and consequences of his acts; he is not subject to act on an irresistible impulse; he is simply inclined to use less resistance than another person to do what he knows is wrong even knowing the consequences of his acts. It is also clear that this state or condition is not due to age, or illness, or abnormal delay in his development or deterioration of his mental faculties; the appellant cannot, therefore, rely on absolute irresponsibility under Article 48 both because that Article does not cover the causes of his state or condition and also because he cannot be said to be *absolutely* incapable of controlling his acts or regulating his conduct according to his understanding. Nor is there under Article 49 a derangement of mind or understanding or arrested mental development; and the only matter to be considered is whether there is an abnormal or deficient condition within the meaning of that Article. The medical expert stated that the type of constitutional psychopath to which the appellant belongs is inclined, in certain circumstances, to yield to impulses of violence without restraint, while such circumstances would not elicit any abnormal reaction in the case of the so called "normal" individual. This state or condition may arise out of various causes; thus a person who is morally perverted is more or less incapable of controlling his instincts, but it is universally acknowledged that such a person is not protected by the provisions of Article 48 or 49. Article 49 is not intended to cover a case of weakness of character which, having regard to a normal individual, may be said to be "an abnormal or deficient condition." The cause of the abnormal or deficient condition, within the meaning of Article 49 must be due to some biological factor and not to such factors as upbringing or atmosphere of living.

Neither Article 48 nor Article 49 cover the present case, the appellant must be considered to be fully responsible and the High Court was right in

finding him guilty of intentional homicide in the first degree.

With regard to sentence Article 522 of the Penal Code provides for the sentence of death or the sentence of rigorous imprisonment for life. The facts in this case justify the sentence of death. The appeal is, therefore, dismissed, and the conviction and sentence of the High Court are confirmed.

(Sentence of death confirmed by His Imperial Majesty in accordance with the Revised Constitution of Ethiopia, Art. 50 and the Code of Criminal Procedure, Art. 204 –Ed.)

የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

ክፍል ፡ ፱

ከሳሽ ፡ እነ ፡ ወይዘሮ ፡ ወርቅነሽ ፡ በዛብህ ፤ ተከሳሽ ፡ እመት ፡ ይደነቁ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቊጥር ፡ ፫፻፹፫/፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ።

አባትነትን ፡ ስለማስረዳት ፡ — ስለልጅነት ፡ ማስረጃ ፡ — የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ፯፻፵ — ፯፻፵፩ — ፯፻፵፪ — ፯፻፵፯ ።

ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ሰጭዋ ፡ ከዘጠኝ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የሞተች ሙ ፡ እናቷ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከሞቱት ፡ አባቱ ፡ ናቸውና ፡ ሀብታቸውን ፡ እንካፈላለሁ ፡ ከምትላቸው ፡ ሰው ፡ በዲቃላነት ፡ ወልዳኛለች ፡ በማለት ፡ ልጅነቷን ፡ ምስክር ፡ ቆጥራ ፡ እንድታስረዳ ፡ ፈቅዶ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰለ ሰጠ ፡ ይግባኝ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፤

ፍርዱ ፡ ትእዛዙ ፡ የመልስ ፡ ሰጭዋን ፡ ክስ ፡ የአባትነትን ፡ ማስረጃ ፡ ከሚመለከቱት ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ፯፻፵—፯፻፵፭ና ፡ የልጅነቱ ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ ከሚያመለክቱት ፡ አንቀጾች ፡ ፯፻፵—፯፻፵፯ ፡ ውጭ ፡ በመሆኑ ፡ ይሻራል ።

ሉ ፡ በቀድሞውም ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ቢሆን ፡ መልስ ፡ ሰጭዋ ፡ ልጅነቷን ፡ ለማስረዳት ፡ አልቻለ ችም ፡ ምክንያቱም ፡ አባት ፡ ናቸው ፡ የተባሉት ፡ አልተቀበሉም ፡ ነበር ፡ ወይም ፡ እንዲቀበሉ ፡ አልተፈረደ ባቸውም ፡ ነበር ፡ እንዲሁም ፡ መልስ ፡ ሰጭዋ ፡ በዕድሜ ፡ ከ፵ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ስትሆን ፡ በቤተሰብም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በተባሉት ፡ አባት ፡ ዘንድ ፡ አትታወቅም ፡ ነበር ።

ታህሣሥ ፡ ፯ ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዳኞች ፡ አፈንጉሥ ፡ ቅጣው ፡ ይታጠቁ ፤ ዶክተር ፡ ቡሐ ጃር ፤ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ተክለጊዮርጊስ — በዚህ ፡ ነገር ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ በላምባራስ ፡ ደግፌ ፡ በዛብህ ፡ በ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያለኑዛዜ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለዩ ። ወራ ሾች ፡ እኛ ፡ ስለሆንን ፡ የሟቹ ፡ ወራሾች ፡ ለመሆናችን ፡ በሕግ ፡ ይታወቅልን ፡ ሲሉ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የውርስና ፡ የአስተዳደር ፡ መዝገብ ፡ ቢከፍቱ ፡ መልስ ፡ ሰጭዋ ፡ እናቴ ፡ ወይዘሮ ፡ ማንሴት ፡ ጥጉ ፡ ከሟቹ ፡ ወልዳኛለች ፡ እሷም ፡ ከ፱ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ሞታለች ፤ ስለዚህም ፡ የሟቹ ፡ ዲቃላ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ በማለትና ፡ ልጅ ፡ ለመሆ ኔም ፡ በምስክር ፡ ላስረዳ ፡ ብላ ፡ አመልክታ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቅዶላታል ። ይህን ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ በመቃወም ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ይህን ፡ የትእዛዝ ፡ ይግባኝ ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረቡ ።

<u>የይግባኙም ፡ ምክንያት ፡</u>

እመት ፡ ይደነቁ ፡ ከ፵ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ዕድሜ ፡ ያላት ፡ ስትሆን ፡ ሟቹ ፡ በሕይ ወት ፡ ሳሉ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብላ ፡ ጠይቃ ፡ የማታውቅ ፡ እኛ ፡ የማናውቃት ፡ ሟቹም ፡ ሲሞቱ ፡ ለልቅሶ ፡ እንኳ ፡ ያልመጣች ፡ ነች ፡ እናቴ ፡ እኔን ፡ በወለደች ፡ ጊዜ ፡ ከባል ፡ ጋር ፡ ነበረች ፡ የምትል ፡ ነች ፡ ስለዚህ ፡ የባላምባራስ ፡ ደግፌ ፡ ልጅነቱን ፡ ላስረዳ ፡ ብላ ፡ ምስክር ፡ መቁጠር ፡ አይገባትም ፡ በማለት ፡ ነው ።

ፍርዱ ፡ የሚታየው ፡ በአዲሱ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጸናው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ የማለት ፡ ክርክር ፡ አለ ።

በቀድሞው ፡ ሕግ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የተወለደ ፡ ዲቃላ ፡ ልጅን ፡ እንዲያየው ፡ በቀላሉ ፡ ማጠቅ ፡ አልነበረም ።

አንዲት ፡ ሴት ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ግንኙነት ፡ ከአንተ ፡ ልጅ ፡ ወልጃለሁ ፡ ብላ ፡ አበት ፡ ነው ፡ የምትለውን ፡ ሰው ፡ የከሰሰች ፡ እንደሆነ ፡ ወንዱ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ከሴቷ ፡ ጋራ ፡ መኖሩን ፡ ያመነ ፡ እንደሆነ ፡ ልጅቷ ፡ ከዚሁ ፡ ግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የተፈራች ፡ መሆኗን ፡ እናቷ ፡ የማለች ፡ እንደሆነ ፡ ልጅነቷ ፡ ይታወቅላታል ።

ግንኙነቱን ፡ የካደ ፡ ወይም ፡ ያልተረጋ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህች ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ አለመኖሩን ፡ የማለ ፡ እንደሆነ ፡ ነገሩ ፡ በሱ ፡ መሐላ ፡ ያልቃል ። የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩንም ፡ ልጅቷም ፡ ከዚሁ ፡ ግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የተወለደች ፡ መሆኗን ፡ ሴትዮዋ ፡ በማለች ፡ ብቻ ፡ ልጅን ፡ የሚያስታቅፈው ፡ ልማድ ፡ አልነበረም ።

አባት ፡ በፈቃድ ፡ የመቀበል ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ በግልጽ ፡ በቤተ ፡ ዘመዶቹ ፡ የታወቀ ፡ ለአቀባበሉም ፡ ሥርዓት ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እመት ፡ ይደነቁ ፡ እናቴ ፡ ከባላምባራስ ፡ ደግፌ ፡ ያስተዋወቀችኝ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ብላለች ፡ በዚህ ፡ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በበለጠ ፡ ዕድሜዋ ፡ እንኳን ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ባላምባራስ ፡ ደግፌ ፡ ዘንድ ፡ የምትታወቅ ፡ እንዳልነበረች ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ነው ።

<u>በእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡</u>

የእመት ፡ ይደነቁ ፡ ጥያቄ ፡ ውድቅ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሷን ፡ በሰው ፡ ምስክርነት ፡ ታስረዳ ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሽረን ፡ ይግባኙን ፡ ተቀብለን ፡ ስለሟቹ ፡ ውርስና ፡ ሌላውን ፡ ጉዳይ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዓይቶ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጥበት ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይጻፍላት ፡ ታኅሣሥ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Div. A

Woz. WORKINESH BEZABIH & others v. Woz. YIDENEKOU

Civil Appeal No. 883/55 E.C

Paternal Filiation -- Proof of filiation -- Possession of status -- Articles 740-761, 769-777 Civ. C.

Relationship of Civil Code to prior customary law -- Art. 3348 Civ. C.

Where appellants have appealed from an order of the High Court allowing respondent to call witnesses in order to prove possession of the status of daughter born out of wedlock of alleged mother who died nine years previously and alleged father, recently deceased, from whose estates she wishes to claim --

Held: Order quashed as respondent's suit does not comply with the relevant provisions of the Civil Code.

1. A child must be considered of unknown father unless capable of proving paternity under one of the following rules:

   (a) a child has as his father that person who, at the time of birth or conception, was married to the mother or was living in an irregular union with the mother (Arts. 740 (1), 741-745 Civ. C.),

   (b) where the paternity of a child has not been established under rule (a), then paternity may result from an acknowledgment made in writing in accordance with the provisions of Arts. 746-757 Civ. C.

   (c) where the paternity of a child has not been established under either rule (a) or rule (b), then paternity may result from a judicial declaration which can be made in the case of abduction or rape of the mother in accordance with Arts. 758-761 Civ. C..

2. Filiation is to be proved by records of birth and in default of such records by possession of status (Arts. 769-770 Civ. C.). Mere rumors of filiation do not constitute possession of status; a child must be treated by the alleged parent as his child and seen to be such by relatives, neighbors and surrounding society.

3. An action to claim status when brought by a child must be instituted against the mother (Art. 777 (2) Civ. C.).

4. Although courts may properly entertain suits to prove that paternal filiation has been established according to customary law prior to the coming into force of the Code, they may not hear suits to claim possession of status under customary law after the effective date of the Code as the agglomeration of facts which entitles a person to claim possession of status did not constitute a "legal situation" before enactment of the Code as required by Art. 3348 Civ. C. A "legal situation" is created when a court decides that certain facts entitle a person to the status in question.

Tahsas 7, 1956 E.C. (December 17, 1963 G.C.); Justices: Afenegus Kitaw Yitateku, Dr. W. Buhagiar, Ato Taddesse Tekle Giorgis: -- In this case the appellants claim to be the heirs of Balambaras Degefe Bezabih who died intestate in the year 1954 and instituted proceedings in the High Court to be declared heirs; the respondent claims to be the daughter of the deceased born out of wedlock, her mother being Woizero Maniste Tegegu, who died about nine years ago. The respondent applied to the High Court to prove possession of status as being the daughter of the deceased, and the Court allowed 4 witnesses to be called by the respondent to prove such status. The appellants are now appealing from the order allowing the respondent to call witnesses.

Before dealing with the merits of this appeal, it is important to consider what provisions the new Civil Code of Ethiopia (which came into force on Maskaram 1, 1953) makes as regards maternity and paternity and as regards proof of filiation. In many respects such provisions differ fundamentally from the rules of customary law now repealed by the Code, particularly in matters concerning paternity.

As regards maternity the Civil Code provides in Article 739 that "maternal filiation results from the sole fact of the birth". When it is established as a fact that a child has been born to a particular woman, that woman is the mother of the child; accepting this fact, Roman law had the maxim "mater semper certa est". There may, of course, be cases where the said fact is not clearly established, as when there has been a substitution of the infant at the time of birth, in which case maternal filiation may be contested.

As regards paternal filiation, the Civil Code lays down three rules, one subsidiary to the others, namely --

(a) a child has as his father that person who, at the time of birth or conception, was married to the mother or was living in an irregular union with the mother -- Art. 740 (1) and Arts. 741-745;

(b) where the paternity of a child has not been established under rule (a), then paternity may result from an acknowledgment made in writing in accordance with the provisions of Arts. 746-757, and

(c) where the paternity of a child has not been established under either rule (a) or rule (b), then paternity may result from a judicial declaration which can be made in the case of the abduction or rape of the mother in accordance with the provisions of Arts. 758-761.

Where the paternity of a child has not been established under any of the above-mentioned rules, then there is no remedy for the child to establish paternity, and he must be considered as being of unknown father. The Code makes provision for the case of conflict of paternity (Art. 762 et seq.) which may arise in cases, e.g., of a married woman living also with a man in an

irregular union. But apart from cases of such a conflict, paternity is established strictly in accordance with the three rules above mentioned. Thus in the case of paternity established under rule (a), if the man claims not to be the father of the child, he may bring an action to disown the child under Article 782 et seq.; but the law gives the right only to him (and in the cases mentioned in Art. 793 to his descendants); but if that man elects not to bring the action to disown, then no other person, not even the child and the mother, can bring such action. The law also lays down a perremptory period within which such action may be brought, that is, 180 days. (See Article 792.) So that if the father does not bring the action or does not bring it within the said period of 180 days, then paternity will be as established under rule (a), and it is not permissible to adduce any evidence to show that such paternity does not correspond with the real facts. This and other rules concerning paternity and maternity are in the nature of provisions of public policy (dispositions d'ordre publique).

As regards proof of filiation, the Civil Code contains provisions in Arts. 769-777. The cardinal rule is that filiation is proved by the records of birth, that is, by the registration in the Registers of Civil Status showing who the father and the mother of the child are. The Registers of Civil Status are mentioned in Articles 90 et seq. of the Civil Code; these Registers are records in which particulars of birth, death and marriage of all persons are entered. These Registers have not so far been established, but when established, they will provide conclusive evidence of the particulars entered therein. In default of records of birth, filiation may be proved by possession of status.

In the generality of cases the question of proof of filiation arises in relation to paternity, for as a rule maternity gives no difficulty. It is clear that once the Civil Code has established definite rules regarding paternal filiation, it is not permissible to circumvent those rules and try to prove the existence of a status contrary to the situation arising from those rules. Thus it is not permissible to prove that a child born of a woman at a time she was married to a particular man has the status of a child of another man (except in an action of disowning brought by the alleged father); nor is it permissible to bring an action against a man for a declaration that a child has the possession of status of being a child of that man when that man has not acknowledged the child as his or has not been judicially declared to be the father of the child after a conviction of abduction or rape.

What is meant by possession of status? Possession of status is the judicial aspect of manifestations of outward appearances; the elements of possession of status are normally said to be *nomen* (name), *tractatus* (treatment) and *fama* (notoriety). Article 770 of the Civil Code provides as follows: "A person has the possession of status of a child when he is treated by a man or a woman, by their relatives and by society as being the child of that man or woman". It is to be noted that Article 770 does not include the name as a necessary ingredient for the

possession of status, but, naturally, the fact that a child has constantly carried the name of the alleged parent is a very relevant circumstance. Mere rumours about filiation do not amount to possession of status; it is essential that a child has been treated by the alleged parent as his child and that, in the eyes of the relatives, of the neighbours and of surrounding society, the child is considered as the child of the alleged parent *(fama)*. The law gives importance to these circumstances because when these manifestations are present, it is most likely that the child is truly the child of the alleged parent. Status may be contested as provided in Articles 778–795 of the Civil Code.

(b) In Article 775, the Civil Code lays down by whom an action to claim a status may be instituted; such action may be instituted, (subject to the prior approval of the Court (Art. 773) by (a) the child (or his guardian or heirs), (b) by the mother of the child, and (c) by the father of the child. It would seem that the action by the mother or by the father are actions more in the nature of contestation of status than actions to claim a status. The action, when brought by the child, is to be instituted against the mother (Art. 777). It is never instituted against the alleged father, and, therefore, it is to be held that the action to claim a status cannot be instituted for the purposes of establishing paternity; paternity can be established through an action instituted against the mother when the woman was married, or was living in an irregular union with a man, at the time of birth or conception. It is for this reason that Article 777 (3) lays down that the person to whom paternity of the child will be attributed in case the action is successful must be made a party to the suit

The above is a statement of the law as it stands since the Civil Code came into force on Maskaram 1, 1953. The old customary law which prevailed before the coming into force of the Civil Code took a more liberal view in matters of proof of filiation; there were no definite principles for the establishment of paternity, except the birth of a child from the alleged father, and for the purpose of proving this fact all means of evidence were available. There was no time limit for the institution of a suit, and cases were frequent where a person came to Court, particularly on the death of a person possessing property, with a claim that the claimant was the child of the deceased. Such claims were made many years after the birth of the claimant, sometimes 30, 40, or 50 years later; in some cases the deceased was a lawfully married person, and the claimant would be an adulterine child; in others, the deceased was a single person, and the claimant would be a natural child. There were also cases where the claim was brought during the lifetime of the alleged father with a view to obtaining maintenance for the child. In some cases there were indications, mostly vague, which were alleged to amount to an acknowldgment of the child. The Courts entertained these actions, and evidence of every nature (which in the circumstances could be very dangerous) was allowed to prove the birth (accouchement) from the alleged father. There were also cases where

the claimant alleged that he had been acknowledged by the father in accordance with the customary law prevailing at the time, or that he had been adopted according to custom. In these cases the evidence was directed to prove such acknowledgment or adoption. Cases to prove paternal filiation are still being introduced in Court and the question is: Can these cases be entertained now that the Civil Code is in force which prescribes definite rules about paternal filiation? The claim is normally based on the following legal grounds: It is stated that Article 3348 of the Civil Code holds valid legal situations created prior to the coming into force of the Code, notwithstanding that the Code modifies the conditions on which such situations may be created. The legal situation which is alleged to have been created prior to the coming into force of the Code is the status of being the child of the alleged father, and an action to claim status is instituted under Article 772 et seq. of the Code. As pointed out above these claims arise on the death of some person, allegedly the father, and the claimant appears as an opposer to the petition for probate of a will or for administration of the property of the deceased. The action is not brought against any particular individual, and the mother, against whom the action for possession of status should be instituted, is in many cases dead.

There can be no question that when a legal situation has been created before the coming into force of the Civil Code, that legal situation continues to be valid under the Code, notwithstanding that that legal situation arose out of circumstances or under conditions which the Code no longer recognises. Thus there would be a valid legal situation when a person has been acknowledged as a child of a man in accordance with the formalities of acknowledgment under customary law although those formalities would not, under the Civil Code, be sufficient to constitute acknowledgment. Similarly, if a person has been adopted in accordance with customary law, such adoption would amount to a proper adoption, notwithstanding that the formalities under customary law are different from those required under the Code. Such an adoption would create a legal situation which continues to be valid after the coming into force of the Code. Actions to prove that there is established paternal filiation as a result of such acknowledgment or adoption before the coming into force of the Code are actions which can properly be entertained by the Courts: In such cases, however, the object of the action is not to establish paternal filiation but to show that paternal filiation had been established before the coming into force of the Code

Is the position the same in the case of a person who institutes an action to claim possession of status? The answer is in the negative because it cannot be said that the fact which entitles a person to claim possession of status is a legal situation. The agglomeration of facts which entitles a person to claim possession of status is a factual situation; such factual situation becomes a legal situation when the Courts have decided that those facts entitle the person concerned to be declared the child of a particular person. Possession of status is a new conception in Ethiopian law, and therefore it cannot even be [illegible] to

that those facts gave the right, before Maskaram 1, 1953, to a person to institute a suit for possession of status and that that right should be respected. Nor can it be said that a person who had a right to institute a suit for a declaration of paternity in the way it was done before Maskaram 1, 1953, has still that right to institute that suit, because the principles of ordre publique underlying the positive law as laid down in the Civil Code are contrary to the idea of ordre publique accepted before the Code. For these reasons any suit brought after Maskaram 1, 1953, for establishing paternity must comply with the provisions of the Civil Code.

In the case of this appeal it is not alleged by the respondent that there was an acknowledgment by the deceased that he was her father, or that the deceased had adopted her or that there was anything else which amounts to a "legal situation". The action is directed to prove the accouchement (birth) from the deceased. This is against the principles laid down in the Civil Code, and therefore her action must fail. The Order of the High Court to hear witnesses in support of the respondent's claim is quashed, the appeal is allowed, and the case is referred back to the High Court to proceed on other matters concerning the inheritance of the deceased.

There shall be no order for costs.

የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡
ክፍል ፡ ፮

ከሳሽ ፡ ሚሲስ ፡ ሻኬ ፡ አቫኪያን ፤ ተከሳሽ ፡ ሚስተር ፡ አርቲን ፡ አቫኪያን ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፩፻፲፬/፶፩ ፡ ዓ ም ።

የውርስ ፡ ሕግ — የንብረት ፡ ድርሻ — ምስክሮች —
የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፹፩ ።

ይግባኙ ፡ የቀረበው ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ኑዛዜው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በሌለው ፡ በሁሉም ፡ ነገር ፡ ተገቢና ፡ ትክክለኛ ፡ ቢሆንም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፹፩ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ሦስት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ምስክሮቹ ፡ አራት ፡ ስላልሆኑ ፡ ኑዛዜው ፡ ሊጸድቅ ፡ አይችልም ፡ በማለቱ ፡ ነው ።

ፍርድ ፡ የተሰጠበት ፡ ዓላማና ፡ ፍላጎት ፡ የሚያብራራ ፡ በሳልሆነ ፡ ሦስት ፡ ምስክሮች ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ስለሆነ ፡ ኑዛዜው ፡ መጽደቅ ፡ አለበት ።

ጥቅምት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዳኞች ፡ ሚስተር ፡ ጂ. ዳቢስ ፡ ግራዝማች ፡ ተሰማ ፡ ነገደ ፡ አቶ ፡ ኃይሌ ፡ አማን — በይግባኝ ፡ ባይ ፡ ዋና ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ መካከል ፡ የቀረበው ፡ ክርክር ፡ ስለሟቹ ፡ ስለሚስተር ፡ ሴትራክ ፡ አርቲን ፡ አቫኪያን ፡ ሀብት ፡ ውርስ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ።

ሟቹ ፡ ከመሞታቸው ፡ በፊት ፡ ጥር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሦስት ፡ እማኞች ፡ ፊት ፡ ተናዝዘው ፡ ሟቹና ፡ እማኞቹ ፡ በፈረሙበት ፡ ኑዛዜ ፡ ላይ ፡ ባለቤቱ ፡ ማዳም ፡ ሻኬ ፡ አቫኪያን ፡ ፍጹም ፡ ወራሼ ፡ እንድትሆን ፡ ስለሾምኳት ፡ ማናቸውም ፡ የሚንቀሳቀስም ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረቴንና ፡ እንዲሁም ፡ በኤስ ፡ አ. አቫኪያንና ፡ ኩባንያ ፡ ሲናልኮ ፡ ያሉትን ፡ አክሲዮኖቼንና ፡ መብቶቼን ፡ ሁሉ ፡ እንድትወስድ ፡ እንዲሁም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የሚገኝ ፡ የግል ፡ ሀብቴንና ፡ ንብረቴን ፡ በሙሉ ፡ ወስዳ ፡ እንድትጠቀምበት ፡ በገዛ ፡ ፈቃዴ ፡ ወድጄ ፡ የሰጠኋት ፡ መሆኔንና ፡ በመሰላት ፡ እንድታዝበት ፡ መፍቀዴን ፡ አረጋግጣለሁ ፡ ብለው ፡ ተናዝዘውላቸዋል ።

ይግባኝ ፡ ባይዋም ፡ ይኸው ፡ ኑዛዜ ፡ እንዲጸናላቸውና ፡ በኑዛዜው ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሀብት ፡ ለማስተዳደር ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በውርስና ፡ አስተዳደር ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፸/፶፫ ፡ ጥያቄ ፡ አቅርበዋል ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ጥያቄአቸውን ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ሕዳር ፡ ፳፱/፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በዋለው ፡ ችሎት ፡ አመልካችዋ ፡ ማለት ፡ ያሁንዋ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ለጊዜው ፡ የሟቹ ፡ ባለቤታቸው ፡ የሚስተር ፡ ሴትራክ ፡ አቫኪያንን ፡ ንብረት ፡ እየጠበቁ ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ ፈቃዶ ፡ ለጥያቄአቸው ፡ ተቃዋሚ ፡ እንዳለ ፡ እንዲቀርብ ፡ በጋዜጣ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲወጣ ፡ አዟል ።

በትእዛዙም ፡ መሠረት ፡ ማስታወቂያው ፡ በጋዜጣ ፡ ስለወጣ ፡ የሟቹ ፡ አባት ፡ ያሁኑ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ ሚስተር ፡ አርቲን ፡ አቫኪያን ፡ በነገረፈጃቸው ፡ በሚስተር ፡ ሐማዊ ፡ አማካይነት ፡ ተቃዋሚ ፡ ሆነው ፡ ቀርበው ፡ የሟቹ ፡ ኑዛዜ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱፻፷፩/፪ ፡ እንደሚፈቅደው ፡ በአራት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ያልተደረገ ፡ በመሆኑ ፡ ሊጸና ፡ አይገባውም ፡ ይፈርሳል ፤ ኑዛዜውም ፡ ሲፈርስ ፡ እኔ ፡ የሟቹ ፡ አባት ፡ በመሆኔ ፡ ከሟቹ ፡ ንብረት ፡ ግማሹን ፡ በውርስ ፡ ማግኘት ፡ ይገባኛል ፡ ሲሉ ፡ ተከራክረዋል ።

የመጀመሪያው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ የመልስ ፡ ሰጭውን ፡ መቃወሚያ ፡ ተቀብሎ ፡ የሟቹ ፡ ኑዛዜ ፡ በአራት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ያልተደረገ ፡ በመሆኑ ፡ መጽናት ፡ አይገባውም ፡ ይፈርሳል ፡ ሲል ፡ ስለወሰነ ፤ የስር ፡ አመልካችዋ ፡ ያሁንዋ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ በነገረፈጃቸው ፡ አማካይነት ፡ የሟቹ ፡ ባለቤትም ፡ ኑዛዜ ፡ በአራት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ባይደረግም ፡ አይጸናም ፡ የሚባልበት ፡ ምክንያት ፡ ሊኖር ፡ ስለማይገባ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ኑዛዜው ፡ አይፀናም ፡ ሲል ፡ የሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ተሽሮ ፡ ኑዛዜው ፡ እንዲፀና ፡ ይደረግልኝ ፡ ሲሉ ፡ ይህን ፡ ይግባኝ ፡ አቅርበዋል ።

የመልስ ፡ ሰጭውም ፡ ነገረፈጅ ፡ ለይግባኙ ፡ መልስ ፡ እንዲሰጡ ፡ ተጠርተው ፡ ቀርበው ፡ ባቀረቡት ፡ መልስ ፡ ኑዛዜው ፡ መጽናት ፡ አይገባውም ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ጸንቶ ፡ ይግባኙ ፡ እንዲሰናበት ፡ ይደረግልኝ ፡ ሲሉ ፡ ጠይቀዋል ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድና ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ያቀረቡትን ፡ ክርክር ፡ በሚገባ ፡ መርምረዋል ። መርምሮ ፡ እንደተረዳውም ፤

፩ ሟቹ ፡ ሚስተር ፡ ሴትራክ ፡ አቫክያን ፡ ከመሞታቸው ፡ በፊትና ፡ አሁን ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ከደረጉት ፡ ኑዛዜ ፡ በፊት ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ሰኔ ፡ ፳፩/፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሚስታቸው ፡ ጋር ፡ ባደረጉት ፡ ውል ፡ በአምስተኛ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ በሲኖልክ ፡ ኩባንያ ፡ ከሚገኙ ፡ ጠቅላላ ፡ አክሲዮኖች ፡ ውስጥ ፡ ማለት ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ሁለት ፡ አክሲዮኖች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሃምሣ ፡ ስድስት ፡ አክሲዮኖች ፡ የባለቤታቸው ፡ የማዳም ፡ ሻኬ ፡ አቫኪያን ፡ ንብረት ፡ መሆናቸውን ፡ በማረጋገጥ ፡ በዚሁ ፡ ውል ፡ በ፲ኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ላይም ፡ እሳቸው ፡ ማለት ፡ ሚስተር ፡ አቫኪያን ፡ ቀድመው ፡ ቢሞቱ ፡ በኩባንያው ፡ ውስጥ ፡ ያሉዋቸው ፡ ሃምሣ ፡ አክሲዮኖች ፡ ባለቤታቸው ፡ በውርስ ፡ እንዲወስዱ ፡ ፈቅደው ፡ ኑዛዜ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ተዋውለዋል ። ይኸውም ፡ ውል ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሬጂስትራር ፡ ፊት ፡ የተመረመረና ፡ በኋላም ፡ ለንግድና ፡ እንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ የተላለፈ ፡ ለመሆኑ ፡ የይግባኝ ፡ ባይዋ ፡ ነገረፈጅ ፡ መስከረም ፡ ፳፱/፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቀረቡት ፡ ማመልከቻ ፡ ላይ ፡ አረጋግጠዋል ። የመልስ ፡ ሰጭውም ፡ ነገረፈጅ ፡ የዚህን ፡ ማመልከቻ ፡ ግልባጭ ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ይኸንኑ ፡ ሳይክዱ ፡ ስለቀሩ ፡ እንደተቀበሉት ፡ ይቆጠራል ።

፪ ፡ ሟቹ ፡ ሚስተር ፡ አቫኪያን ፡ አሁን ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ባደረጉትም ፡ ኑዛዜ ፡ ላይ ፡ ያንኑ ፡ በፊት ፡ ለሚስታቸው ፡ የተናዘዙላቸውን ፡ በሲኖልኩ ፡ ኩባንያ ፡ ያላቸውን ፡ አክሲዮንና ፡ ማናቸውም ፡ ንብረታቸው ፡ ሁሉ ፡ ሚስታቸው ፡ በውርስ ፡ እንዲወስዱ ፡ በሦስት ፡ እማኞች ፡ ፊት ፡ አረጋግጠው ፡ ተናዝዘውላቸዋል ፤ በኑዛዜውም ፡ ላይ ፡ ተናዛዡና ፡ እናዛዥዎች ፡ ፈርመውበታል ።

፫ ፡ በሲናልኮ ፡ ኩባንያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ አክሲዮንም ፡ በመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ የአሁንዋ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ሀብት ፡ ለመሆኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ስለሆነ ፡ ሟቹ ፡ ለሚስታቸው ፡ ያወረሱዋቸው ፡ አክሲዮን ፡ በመቶ ፡ ፳፭ ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። የቀረውም ፡ ሀብት ፡ የባልና ፡ ሚስት ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ እንደሆነ ፡ ይታመናል ።

፬ ፡ ሟቹና ፡ ይግባኝ ፡ ባይዋም ፡ ከጋብቻቸው ፡ የተገኙ ፡ ልጆች ፡ እንደሌላቸው ፡ በክርክራቸው ፡ ተገልጿል ። መልስ ፡ ሰጭውም ፡ ያቀረቡት ፡ ክርክር ፡ ከሟቹ ፡ ልጅ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ጧሪ ፡ ልጅና ፡ ሀብት ፡ ስለሌለኝ ፡ ዕድሜ ፡ አለ ፡ ድረስ ፡ በልጄ ፡ ሀብት ፡ መጦር ፡ ይገባኛል ፡ በማለት ፡ ሳይሆን ፡ ስለኑዛዜው ፡ ፎርማሊቲ ፡ ማለት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፹፩/፪ ፡ እንደሚያዘው ፡ በአራት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ አልተደረገምና ፡ መጽናት ፡ አይገባውም ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፭ ፡ መልስ ፡ ሰጭው ፡ የጠቀሱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፹፩/፪ ፡ በግልጽ ፡ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡ በአራት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ካልተደረገ ፡ በቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ቢልም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፱፻፲/፩ ፡ እንደተመለከተው ፡ ጥርጣሬ ፡ በሚፈጥርበት ፡ ጊዜ ፡ በራሱ ፡ በኑዛዜው ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ አካባቢ ፡ ነገሮች ፡ እንደተመለከተው ፡ የተናዛዡ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በተገመተው ፡ መሠረት ፡ ኑዛዜው ፡ መተርጐም ፡ አለበት ፡ ስለሚል ፡ የሕግ ፡ አውጭው ፡ ሃሳብ ፡ የማያጠራጥር ፡ ኑዛዜ ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ መፈለጉን ፡ ስለሚያስረዳ ፡ ይህም ፡ እንዳይሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የነገሩ ፡ አካባቢዎችን ፡ በማመዛዘን ፡ ሕጉን ፡ መተርጐም ፡ እንዳለበት ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

፮ ፡ በዚህም ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሕጉን ፡ መንፈስና ፡ ትርጉም ፡ እንደተረዳው ፡ የነገሩም ፡ አካባቢዎች ፡ መርምሮ ፡ እንደደረሰበት ፡ ሟቹ ፡ ኑዛዜ ፡ በደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ሕጉ ፡ ገና ፡ አዲስ ፡ ስለነበረና ፡ ከኑዛዜአቸውም ፡ በፊት ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ አራት ፡ ወር ፡ ብቻ ፡ ማለት ፡ ከመስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በመሆኑና ፡ ኑዛዜአቸውም ፡ ያደረጉት ፡ በጥር ፡ ፰ ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመሆኑ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፳፻፹፩/፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ አራት ፡ ምስክር ፡ ማስፈለጉን ፡ ባይረዱት ፡ እንጂ ፡ አስቀድመው ፡ በደረጉትም ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ለሚስታቸው ፡ ላሁንዋ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ተናዝዘውላቸው ፡ ስለነበረ ፡ በኋላም ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ይኸንኑ ፡ በማረጋገጥ ፡ ለሚስታቸው ፡ ስለተናዘዙላቸው ፡ ከመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሚስታቸው ፡ ብቻ ፡ ወራሻቸው ፡ እንዲሆኑ ፡ መፍቀዳቸውን ፡ ስለሚያረጋግጥ ፡ ስለኑዛዜው ፡ የሚያጠራጥር ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፱፻፮ ፡ እንደተመለከተውም ፡ የባልና ፡ ሚስት ፡ ጋብቻ ፡ እስከመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ፀንቶ ፡ ከቆዬ ፡ ባል ፡ ለሚስቱ ፡ ያደረገው ፡ ኑዛዜ ፡ መሰረዝ ፡ አይገባውም ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጸው ፡ ምክንያት ፡ የሟቹ ፡ ኑዛዜ ፡ በአራት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ባይደረግም ፡ የሚጸና ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ ሽረን ፡ ይግባኝ ፡ ባይዋ ፡ በኑዛዜውም ፡ መሠረት ፡ የሟቹ ፡ ባለቤታቸው ፡ የሚስተር ፡ ሴትራክ ፡ አርቲን ፡ አቫኪያን ፡ ሀብት ፡ መውረስ ፡ ይገባቸዋል ፡ ብለናል ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያውቀው ፡ የዚህ ፡ ፍርድ ፡ ግልባጭ ፡ እንዲላክለት ፡ ጨምረን ፡ አዘናል ።

SUPREME IMPERIAL COURT

Div. 6

Mrs. CHAKE AVAKIAN v. Mr. ARTIN AVAKIAN

Civil Appeal No. 1114/55 E. C.

Law of Successions -- Form of will -- Witnesses -- Art. 881 Civ. C.

On appeal from judgment of the High Court denying petition for probate of a will on the basis that, although valid in other respects, there were only three attesting witnesses, while Art 881 Civ. C. requires four such witnesses.

Held: petition should be allowed as three witnesses are sufficient to validate a will when the intention of the testator is clear beyond doubt.

1. The real aim of the legislators goes to the true intent of the testator and not to the form of the will.

Tekemt 13, 1956 E. C. (October 24, 1963 G. C.); Justices: Mr. G. Debbas, Grazmatch Tessemma Negede, Ato Haile Aman: – This is an appeal against the judgment of the High Court (lst Commercial Division) dated 23.7.55 in Probate and Administration File No. 107/55, whereby the appellant lost her petition for probate of the will of her husband appointing her as his sole heiress by universal title. The High Court declared the will invalid for lack of form only, although it commented and admitted that the husband wanted his wife, the present appellant, to be his sole heiress.

The whole appeal, interesting as it is, is about the validity of a will. The late Setrak Avakian was the appellant's husband and died in Addis Ababa on 2nd November, 1962 G. C. His widow petitioned the High Court for probate of the will of her husband, made by him on 16th January, 1961, G. C., appointing her as his sole legatee by universal title. The findings of the High Court regarding the contents of the will are not disputed by either party. The contents of the will are typewritten on both original versions in Amharic and English. The date of the signing by the deceased is filled in

in handwriting on both versions. Both versions bear the signature of the deceased and three persons have affixed their signatures, witnessing the signing in their presence by the deceased after the will had been read over. One of the witnesses to the will was given custody of the original Amharic and English versions. So far there is no dispute by either party.

When the widow petitioned the High Court for probate of the will of her late husband, the only opposer was her father-in-law i.e., the present respondent! Certainly, there was no opening for him, except to attack the form of the will. According to Article 881 of the Civil Code, four witnesses are necessary for a public will, while two witnesses would be sufficient, under Article 882 of the Code, provided one of them is a public officer acting in the discharge of his duties. In this very case, only three witnesses affixed their signatures to witness the signing of the will by the testator and the reading out of it. The question that now arises is whether or not those three witnesses are sufficient to validate the will.

In order to decide on such very delicate cases, a court should not be blinded by the question of form; it should go a little further and find out the presumed intention of the testator, from surrounding circumstances, especially in cases of doubt or uncertainty. Not only one article of the Code should bind a court, but the whole situation should be looked upon generally. It is more the intention of the testator than the form of the will that is the real aim of the legislator.

To start with, this will is a typewritten will both in Amharic and in English. Article 885 of the Civil Code which deals with type written wills, provides that such wills shall be of no effect unless they bear on each of their leaves a handwritten indication of such fact. This very will complies with this Article 885, because it consists of one single leaf in Amharic and one single leaf in English, which are both signed by the testator and the three witnesses and testify to the fact that it is a will. Consequently there is no argument against this will under Article 885 of the Civil Code.

Coming now to Article 881 of the Civil Code, which provides for four witnesses, as opposed to Article 882, which provides for two witnesses, provided one of them is a public officer, and looking at the will, subject-matter of this appeal, we have to go far beyond the Articles referred to by both parties and try to find out the real intention of the testator, in view of the doubt that arises.

The real intention of the deceased testator is whether or not he died "unwilling" to appoint his wife as his sole heiress. There is no argument that the testator died sincerely believing that his sole heiress would be his wife, i.e., the appellant. From his commercial activities during his lifetime, it transpires

from the Memorandum of Association (Article 17 thereof) that a private limited company SINALCO had been formed between him and his wife, i. e., the appellant. Article 17 provides "Nor shall the company be dissolved in case of the death of a member. In the latter event, it is hereby irrevocably stipulated that the shares held by Setrak Avakian shall devolve upon Mrs. Chake Avakian (this appellant); and vice versa.' "Furthermore, this lady appellant holds in that private limited company 75% of the shares (*vide* Article 5 of the Memorandum of Association), while her deceased husband was holding only 25% of the shares. From the contents of Article 17 of the Memorandum of Association, it is already clear that the intention of the testator long before his death and before he wrote his will, was to assign the ownership of all his shares in that company to his wife: which fact clarifies his intention in the will that she shall be his sole heiress.

Our argument regarding the presumed intention of the deceased testator does not stop here but is reinforced by the comments in the judgment of the High Court. Among other comments, the High Court commented "It results that there is no validly given will. This may seem a strange, and in the circumstances, unsatisfactory result, since there can be no serious, doubt about the deceased's intention to appoint his wife as his legatee by universal title, and that he may have died in the belief that she would succeed to all his properties. But the rules relating to the form of wills have been given in order to ensure that effect is given only to the indubitable intention of the testator . . . " From these words, and particularly the last sentence of the High Court comment, the indubitable intention of the testator was to appoint his wife Chake Avakian as his sole heiress. The existence of the present will, coupled with the argument of the High Court regarding the intention of the testator, and coupled also with the contents of Article 17 of the Memorandum of Association of SINALCO, lead us to believe that the indubitable intention of the testator was definitely to appoint his appellant widow as his sole legatee by universal title, to succeed to all his properties. It is consequently useless to continue discussing the intention of the testator.

Another article which eventually helps the appeal is Article 906 of the Civil Code. The testator died when they were still legally married as husband and wife. Their marriage was dissolved only through the death of the husband; and consequently any testamentary provision made by the testator, the late Setrak Avakian in favour of his spouse, Mrs. Chake Avakian, is still strong and valid.

In such cases when the court of first instance knows that the presumed intention of the deceased is to let his wife succeed to all his properties, it should not blind itself with the question of form, especially when the form has all been complied with. An absence of one witness, when three are present and reliable, is of no importance.

Under the circumstances, and in view of the foregoing explanation, we hereby allow this appeal and quash the judgment of the High Court and declare the will of the late Setrak Avakian appointing his wife Mrs. Chake Avakian as his sole heiress, as valid and executory and appoint Mrs. Chake Avakian as sole liquidator of the estate of her late husband.

Each party shall bear its own costs. Given and delivered in open court this 13th day of Tekemt, 1956, in the presence of both parties.

ከፍተኛ፡ ፍርድ፡ ቤት፡

አዲስ፡ አበባ፡ አንደኛ፡ የንግድ፡ ክፍል፡ ችሎት ።

ጉዳዩ፡ ስለ፡ ሌትራክ፡ አቫኪያን፡ ንብረት ።

የውርስና፡ የአስተዳደር፡ ነገር፡ ቍጥር፡ ፩፻፯/፶፭ ዓ፡ ም ።

የውርሶች፡ሕግ — የኑዛዜ፡ፎርም — በጋ
ልጽ፡ወይም፡በተናዛዡ፡የጅ፡ጽሑፍ፡ስለሚ
ደረጉ፡ኑዛዜዎች፡አስፈላጊ፡ነገሮች —
የፍትሐ፡ብሔር፡ሕግ፡አንቀጾች፡ 881 ና 885 ።

ሙሉ፡ኑዛዜ፡እንዲጸድቅ፡ለማመልከት፡ቢቀ፡ብ፡ተቃዋሚ፡ወገኖች፡ወይም፡በተናዛዡ፡የጅ፡ጽሑፍ፡የሚደረገው፡ውል፡የሚ ያስፈልጉትን፡ነገሮች፡ሙሉ፡በሙሉ፡ያሟላ፡ነው፡ሲሉ፡ተቃወሙ ።

ፍርድ፤ ኑዛዜው፡የፍትሐ፡ብሔር፡ሕግ፡አንቀጽ፡፰፻፹፩፡በሚያዘው፡መሠረት፡በአራት፡ምስክሮች፡ፊት፡ካልደረገ፡በቀር፡ምስክሮች፡ፊት፡ካልሆነ፡በስተቀር፡ፈራሽ፡ይሆናል ።

ሀ፡ ወይም፡የተደረገበት፡ኑዛዜ፡በፍትሐ፡ብሔር፡ሕግ፡አንቀጽ፡፰፻፹፭፡መሠረት፡በተናዛዡ፡የጅ፡ጽሑፍ፡የሚደረጉ፡ኑዛዜዎች፡የሚያዙትን፡አስፈላጊ፡ነገሮች፡አልያዘም፤ምክንያቱም፡ተናዛዡ፡የጅ፡ጽሑፍ፡ኑዛዜ፡ለመሆኑ፡በኑዛዜው፡ላይ፡ ስለአላመለከተ፡ነው።

ለ፡ ለኑዛዜዎች፡ቀሚ፡የሆኑ፡አስፈላጊ፡ነገሮች፡መቀቀሚያቸው፡አርግጠኛ፡ለመሆን፡ለተናዛዡ፡ፍላጎት፡ወይም፡ዓላማ፡ብቻ፡ የሕግን፡ማረጋገጫ፡ለመስጠት፡ነው ።

መጋቢት፡ ፳፫፡ ቀን፡ ፲፱፻፶፭፡ ዓ፡ ም ። ዳኞች፡ ሚስተር፡ ኤስ፡ ስቲቨንሰን፡ ሻምበል፡ ኢያሱ፡ ገብረ፡ ሐዋርያት ፤ አቶ፡ ጌራ፡ ወርቅ፡ አጐናፍር — በዚህ፡ ነገር፡ አመልካችዋ፡ ሻኬ፡ አቫኪያን፡ ሕዳር፡ ፱፡ ቀን፡ ፲፱፻፶፬፡ ዓ፡ ም፡ እ. ኤ. አ. የሞተው፡ ሌትራክ፡ አቫኪያን፡ ባለቤቴ፡ ስለሆነ፡ ከመሞቱ፡ በፊት፡ ኑዛዜ፡ ስለተወ፡ በዚህ፡ ኑዛዜ፡ መሠረት፡ እኔው፡ አመልካችዋ፡ ብቻ፡ በኑዛዜው፡ ወራሽ፡ ስለሆንኩ፡ ኑዛዜው፡ እንዲጸድቅልኝ፡ ሲሉ፡ አመልክተዋል ። ከማመልከቻቸው፡ ጋር፡ በአማርኛና፡ በእንግሊዝኛ፡ የተደረገው፡ የሟች፡ ኑዛዜ፡ ጭምር፡ አቅርበዋል ።(አመልካችዋ፡ ስለ፡ ኑዛዜው፡ ውሳኔ፡ እስከ ሰጥ፡ ድረስ፡ ንብረቱን፡ እንድታስተዳድርና፡ እንድታጣራ፡ ትእዛዝ፡ ተሰጥቷት፡ ነበር ፡)

ስለ፡ ውርሱ፡ በጋዜጣ፡ ታውጆ፤ ተቃዋሚ፡ እንዳለ፡ እንዲቀርብ፡ ተደርጎ፡ ስለነበረ፡ የሟቹ፡ አባት፡ የሆኑት፡ አርቲን፡ አቫኪያን፡ የተባሉት፡ የሟቹ፡ አባት፡ የኑዛዜው፡ ፎርም፡ አጻጻፍ፡ ሕግን፡ ያልተመለከተ፡ ነው፡ በማለት፡ ኑዛዜው፡ ፈራሽ፡ እንዲሆን፡ ተቃውመው፡ ቀርበዋል ።

የቀረበው ፡ ኑዛዜ ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ሆኖ ፡ በጽሕፈት ፡ መኪና ፡ የተጻፈ ፡ ነው ፤ በኑዛዜው ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ምስክሮችና ፡ ሟቹም ፡ ብቻ ፡ የፈረመበት ፡ ነው ።

ተቃዋሚው ፡ ዋና ፡ መቃወምያቸው ፡ ስለ ፡ ኑዛዜው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሣይሆን ፡ ስለ ፡ ኑዛዜው ፡ ፎርም ፡ አጻጻፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ከሟቹ ፡ ጋር ፡ ሌሎች ፡ አራት ፡ ምስክሮች ፡ ስላልፈረሙበት ፡ ፈራሽ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፹፩ ፡ (፪ ፡) መሠረት ፡ በግልጽ የሚደረግ ፡ ኑዛዜ ፡ በተናዛዡና ፡ በሌሎች ፡ በአራት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ተጽፎ ፡ የተነበበ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ይላል ፤ እንደዚሁም ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፹፪ ፡ (፪ ፡ መሠረት ፡ ይኸው ፡ ኑዛዜ ፡ በዳኛ ፡ ወይም ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ባላቸው ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፊት ፡ ያልተፈረመ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቶዋል ።

ያመልከች ፡ ጠበቃ ፡ በመኪና ፡ የተጻፈ ፡ ኑዛዜ ፡ ስለሆነ ፡ ሟቹ ፡ ከፈረሙበት ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ ፎርማሊቲ ፡ ማምጣት ፡ አይገባውም ፡ በማለት ፡ ተከራክረዋል ፤ እንዲሁም ፡ ሆኖ ፡ ኑዛዜው ፡ በመኪና ፡ የተጻፈ ፡ ቢሆንም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቍጥር ፡ ፰፻፹፩ ፡ (፪ ፡) መሠረት ፡ ተናዛዡ ፡ ኑዛዜውን ፡ በመኪና ፡ በጻፈ ፡ ጊዜ ፡ ተናዛዡ ፡ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ቅጠል ፡ በእጅ ፡ ጽሕፈት ፡ መግለጽ ፡ ስላለበት ፡ የቀረበውን ፡ ኑዛዜ ፡ ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ ያልተከተለ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተገለጸው ፡ ሁኔታ ፡ መሠረት ፡ አመልካች ፡ ያቀረቡት ፡ ኑዛዜ ፡ ሕጉ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ ሕጋዊ ፡ ፎርም ፡ ያልተከተለ ፡ ስለሆነና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ በአራት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ያልተፈረመ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በዳኛ ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ በውል ፡ አዋዋይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ፊት ፡ ያልተፈረመ ፡ ስለሆነና ፡ ጽሑፉም ፡ የመኪና ፡ ኑዛዜ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ተናዛዡ ፡ ሁኔታውን ፡ በእጅ ፡ ጽሕፈቱ ፡ ያልገለጸ ፡ በመሆኑ ፡ በነዚህ ፡ ውል ፡ ምክንያቶች ፡ ኑዛዜው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ወስነን ፡ ያመልካች ፡ ጥያቄ ፡ አሰናብተናል ፤ አመልካችዋ ፡ የንብረቱ ፡ አጣሪና ፡ አስተዳዳሪ ፡ እንድትሆን ፡ ሕዳር ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሰጠነውን ፡ ትእዛዝ ፡ አንስተናል ፤ የማጣራቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቢነሳም ፡ ቅሉ ፡ የትእዛዙ ፡ መነሣት ፡ የአመልካች ፡ የበልና ፡ የሚስት ፡ ሀብት ፡ መብታቸውን ፡ የሚነካ ፡ አይደለም ፡ ብለን ፡ ወስነናል ።

(ፍርዱ ፡ በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተገለበጠ ፡ ከላይ ፡ የተሰጠ ሐሣብ ፡ ተመልከት ፤ አዘጋጅ)

HIGH COURT

Addis Ababa, Comm. Ct. No 1

In the Matter of the Estate of: SETRAK AVAKIAN

Probate and Administration Case No. 107/55

Law of Successions -- Form of will -- Requirements for public or holographic will -- Arts. 881 and 885 Civ. C.

On the petition for probate, opposer claimed the nullity of will for its failure to comply with formal requirements for a valid public will or holographic will.

Held: Petition denied, the will having been signed in the presence of three witnesses only where Art. 881 Civ. C. requires four for a lawful public will.

1. The contested will does not meet the formal requisites of a holographic will as specified in Art. 885 Civ. C., because it does not indicate itself as such.

2. Formal requirements for wills have been established to ensure lawful effect is given only to testator's indubitable intention.

Megabit 23, 1955 E. C. (April 1, 1963 G. C.); Judges: Mr. S. Stephenson, Captain Yassou Gebre Hawriat, Ato Guerra Work Agonafer --

Setrak Avakian, a resident of Addis Ababa, died on 2nd November 1962 (G. C.). His widow Chaké Avakian has petitioned the Court for probate of a will made by the deceased on the 16th January 1961 (G. C.) appointing her, the petitioner, as his legatee by universal title.

The father of the deceased, Artin Avakian, has filed in Court his declaration of opposition to the will, in that he claims that it is of no effect by the reason of not fulfilling the requirements of law as to form. The opposition was filed in response to the citation published by order of Court in daily newspapers.

Since the will was made after the entry into force of the Civil Code the issue in respect to its validity is governed by the Code.

The will was made in an English and in an Amharic version, both contained on a single sheet of paper. The contents of the will are in both original

versions typewritten. The date of their signing by the deceased are in both versions filled in in handwriting. Both versions bear the signature of the deceased. Three persons have affixed their signatures to the will in witness of its signing in their presence by the deceased after its having been read over. One of the witnesses to the will was also given custody of originals; there is no dispute as to this fact.

The first question which arises is whether or not the will can have effect as a public will according to Article 881 of the Civil Code. The answer must be that it cannot, because it was read prior to signing by the deceased in the presence of only three witnesses, while the law demands four witnesses. It is to be mentioned that none of the witnesses is such a public officer as mentioned in Article 882 of the Code, so that the will could have effect with only one other witness besides him.

Still the will could have effect if it had been given in the forms required for a valid holograph will. Both original versions are typewritten and signed by the deceased. It would seem however, that they were not typed by the testator himself. But even if the deceased actually typed either both or one of the versions himself, the requirements as to form would not have been satisfied, because none of them bears a handwritten indication of such fact. *Vide* Article 885 of the Code.

It results that there is no validly given will. This may seem a strange, and in the circumstances unsatisfactory result, since there can be no serious doubt about the deceased's intention to appoint his wife as his legatee by universal title, and that he may have died in the belief that she would succeed to all his properties. But the rules relating to the form of wills have been given in order to ensure that effect is given only to the indubitable intention of the testator to designate another or other successors to his estate than those who would otherwise have been his rightful heirs at law. Such rules must be strict, and the Court cannot, even in circumstances as the present ones, or in any circumstances, ignore them or allow any latitude in their observance

It is of course understood that the widow's right to her lawful share of properties acquired by her in common with the deceased during their marriage is not affected by this decision.

The appointment of the petitioner as liquidator by order of Court given on 21. 7. 55 is repealed, provided that the repeal of that order must not be taken to mean that the petitioner is thereby deprived of rights as regards her share to properties acquired in common and her continual administration in that respect.

(Judgment reversed by Supreme Imperial Court, see opinion, *supra*-ed.)

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሁለተኛው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ችሎት ።

ከሳሽ ፡ አቶ ፡ ማሞ ፡ ይንበርበሩ ፡ ተከሳሽ ፡ አቶ ፡ ይርጉ ፡ አበበ ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ቍጥር ፡ ፬፻፶፬/፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ።

በአሠሪና ፡ በሠራተኛ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡— የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ድንጋጌ ፡ ቍጥር ፡ ፵፱/፶፬ ፡— የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ፪ሺ፭፻፳፮ ፡— ፪ሺ፭፻፲፪ ።

፩ ፡ በአሠሪና ፡ በሠራተኛ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ በደንብ ፡ እንዲከሄድ ፡ ሥራ ፡ በደንብ ፡ እንዲከናወን ፡ አለመግባባት ፡ ሲፈጠር ፡ ጉዳዩ ፡ በፍጥነት ፡ እንዲወሰንና ፡ እንደዚሁም ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ሲገኙ ፡ የሚከሄዱበት ፡ የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ድንጋጌ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሠራተኛ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ ከሥራ ፡ ተሠናበትኩ ፡ በማለት ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ አይዘጋበትም ።

፪ ፡ የሠራተኛው ፡ ጥፋት ፡ አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ከሥራ ፡ በማሰናበት ፡ ካሣ ፡ እንዳይከፍል ፡ ምክንያት ፡ ሊሆነው ፡ ይችላል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፭፻፶፭ ።

መስከረም ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዳኞች ፡ አቶ ፡ በላቸው ፡ አሥራት ፡ አቶ ፡ ወልደመሔ ፡ ይህደጐ ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ጌታሁን — የአዲስ ፡ አበባ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ለመልስ ፡ ሰጭ ፡ የሥራ ፡ መፈለጊያ ፡ ገንዘብ ፡ $900.00 እንዲከፍሉ ፡ ስለፈረደ ፡ ይህ ፡ ይግባኝ ፡ ቀርቧል ። በይግባኙም ፡ ክርክር ፡ ጊዜ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ በቍጥር ፡ ፵፱/፶፬ ፡ የወጣው ፡ ድንጋጌ ፡ ተጠቅሷል ።

የተባለው ፡ ድንጋጌ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ በአሠሪና ፡ በሠራተኞች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ መመልከት ፡ የሚገባው ፡ በድንጋጌው ፡ የተቋቋመው ፡ ቦርድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አይደሉም ፡ የማለት ፡ ነገር ፡ በየጊዜው ፡ ይሰማል ፡ አንዳንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ እንዲሁ ፡ ያለውን ፡ ጉዳይ ፡ አንቀበልም ፡ ማለታቸው ፡ አልቀረም ።

በእኛ ፡ አስተያየት ፡ ግን ፡ የተባለው ፡ ድንጋጌ ፡ በጠቅላለው ፡ መንገድ ፡ በአሠሪና ፡ በሠራተኞቹ ፡ መካከል ፡ የሚገኘውን ፡ ወይም ፡ የሚነሳውን ፡ ጠቅላላ ፡ ችግር ፡ ወይም ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከታል ፡ እንጂ ፡ በአንድ ፡ ቀጣሪና ፡ በአንድ ፡ ተቀጣሪ ፡ መካከል ፡ በቅጥር ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ የሚነሳውን ፡ የሕግ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ክርክር ፡ አይመለከትም ። በአሠሪዎችና ፡ በሠራተኞች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ በደንብ ፡ እንዲመራ ፡ ሥራ ፡ እንዳይበደል ፡ ኢኮኖሚም ፡ እንዳይጐዳ ፡ በአሠሪዎችና ፡ በሠራተኞች ፡ መካከል ፡ አለመግባባት ፡ ሲፈጠር ፡ ጉዳዩ ፡ ሳይዘገይ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያገኝበትን ፡ ዘዴ ፡ ድንጋጌው ፡ ያውጃል ፡ እንጂ ፡ በቅጥር ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ ተቀጣሪው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚጠይቀውን ፡ ካሣ ፡ አይነካም ፡ ስለዚህ ፡ የተጠቀሰው ፡ ድንጋጌ ፡ በአሠሪዎችና ፡ በሠራተኞች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ጠቅላላውን ፡ ነገር ፡ የሚመለከት ፡ በመሆኑ ፡ ይህ ፡ የያዝነው ፡ ጉዳይ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዳይመረመር ፡ አያደርግም ፡ ዓላማውም ፡ አይደለም ።

እንግዲህ ፣ ወደ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ በመመለስ ፣ የቅጥር ፣ ውል ፣ ለተወሰነ ወይም ፣ ላልተወሰነ ፣ ጊዜ ፣ ነው ። ውሉም ፣ በማስታወቂያ ፣ ወይም ፣ ከለማስታወቂያ ፣ ሊቋረጥ ፣ ወይም ፣ ላይታደስ ፣ ይችላል ። እንደዚህ ፣ በሚደረግበት ፣ ጊዜ ፣ ተጐዳሁ ፣ የሚለው ፣ ወገን ፣ ካሣ ፣ ለመጠየቅ ፣ ይችላል ። ካሣ ፣ እንዲከፍል ፣ የተጠየቀውም ፣ ወገን ፣ ምክንያት ፣ አለኝ ፣ በማለት ፣ ለመከላከል ፣ ይችላል ። ካሣ ፣ የተጠየቀው ፣ የካሣ ፣ ጠያቂውን ፣ ጥፋት ፣ ለመመልከት ፣ የፈለገ ፣ እንደሆነም ፣ የተባለው ፣ ጥፋት ፣ ምክንያት ፣ ሊሆን ፣ ይችላል ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ ከቍጥር ፣ ፩ሺ፰፻፰ ፣ እስከ ፣ ፩ሺ፰፻፲፰ ፣ ድረስ ፣ ተዘርዝሯል ።

የአዲስ ፣ አበባ ፣ አውራጃ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ መልስ ፣ ሰጭው ፣ ከሥራ ፣ የተሰናበቱት ፣ በጥፋታቸው ፣ ምክንያት ፣ ነው ፣ ሲሉ ፣ ይግባኝ ፣ ባዩ ፣ ያመለከቱትን ፣ የተጠቀሱት ፣ ሦጥሮች ፣ በሚያዘው ፣ መሠረት ፣ በሚገባ ፣ ልብ ፣ ሳይል ፣ ለመልስ ፣ ሰጭው ፣ የፈረደ ፣ ሆኖ ፣ አግኝተነዋል ። ስለዚህም ፣ ነገሩን ፣ እንደገና ፣ ከላይ ፣ በተገኘው ፣ ዓይነት ፣ አይቶ ፣ እንዲወስን ፣ ፍርዱን ፣ ሽረን ፣ ልከንለታል ። ባለጉዳዮቹም ፣ የየራሳቸውን ፣ ኪሣራ ፣ ይቻሉ ፣ ብለናል ።

HIGH COURT

Addis Ababa, Civ. Ct. No. 2

Ato MAMMO YINBERBERU v. Ato YIRGU ABEBE

Civil Case No. 454/55 E. C

Labour relations -- Labour Relations Decree 49/54 E. C. (49/62 G. C.) -- Arts. 2567-2593 Civ. C.

1. The Labour Relations Decree extending *inter alia*, to guidance of the relationship between employer and employee, progress of work, advancement, and expeditious settlement of misunderstandings does not restrict an employee's right to claim compensation for wrongful dismissal under the Civil Code.

2. Fault of the employee may constitute good cause relieving the employer of his duty to compensate for dismissal. Art. 2575 Civ. C.

Maskaram 20, 1956 E. C. (October 1, 1963 G. C.); Judges: Ato Belatchew Asrat, Ato Wolde Mussie Yihdego, Ato Mekonnen Getahun: - -

This appeal was brought from judgment of the Addis Ababa Awraja Court allowing respondent $ 900 in order to find employment. The decision was based upon the Labour Relations Decree 49/54.

It has often been stated after the enactment of the above-mentioned Decree that the Board established therein and not the courts is the proper institution to hear cases between employer and employee. Some courts have refused jurisdiction in such cases.

In our opinion, the Labour Relations Decree was enacted to deal with general difficulties arising between employer and employee. The scope of the Decree extends to such areas as the following: guidance of the relationship between employer and employee, progress of work, advancement, and the expeditious settlement of misunderstandings. The Decree does not restrict the employee's right to claim compensation for wrongful dismissal in a contract of hire under the provisions of the Civil Code. The present case is, therefore, properly before us.

Under the Civil Code a contract of hire may be for a limited or unlimited period and may be terminated or not renewed without notice. In such a case,

however, the injured party may claim compensation. The employer is permitted to defend himself by establishing good cause, including fault in the employee, which justifies the termination of the contract.

In our opinion the Addis Ababa Awraja Court has not paid sufficient attention as required by the Civil Code to the appellant's allegations that respondent was dismissed due to his own fault. The judgment of the Awraja Court is therefore reversed, and the case is remanded for further proceedings not inconsistent with this opinion.

The parties will bear their own costs.

— መግቢያ ። —

የሕግ ፡ ቋንቋ ፡ በየትም ፡ አገር ፡ ቢኾን ፡ የተለየ ፡ የራሱ ፡ ዘይቤ ፡ አለው ። የኤውሮፓውያኖች ፡ የመዠመሪያ ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ የተወጠነው ፡ በሮማውያን ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በልሳነ ፡ ላቲን ፡ ስለነበረ ፡ እስካኹን ፡ ድረስ ፡ የማናቸውንም ፡ የኤውሮፓ ፡ ሕግ ፡ በላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ሲጠቃቀስ ፡ ይታያል ። ይልቁንም ፡ አንዳንድ ፡ የሕግ ፡ ሁኔታዎች ፡ የሚጠቀሱት ፡ በላቲን ፡ ነው ። የኛም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ከወሰኑት ፡ የሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በግእዝ ፡ ልሳን ፡ የተጻፈ ፡ ነበረ ። ስለዚህ ፡ በአማርኛው ፡ ያጣነውን ፡ ወይም ፡ የማያጠግበንን ፡ በግእዝ ፡ ብንተካው ፡ ነውር ፡ አይደለም ። ለሁሉም ፡ የሚያስፈልገው ፡ ልማድ ፡ ስለሆነ ፡ ከለመድ ነው ፡ አገልግሎቱ ፡ ያጠግበናል ።

ያብዛኛው ፡ ቃላት ፡ ትርጓሜ ፡ (ፍች ፡) የተለቀሙት ፡ ከሊቁ ፡ ከኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ «መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ ፡» ነው ።

— ፍች —

፩ ፡ በፍትሐብሔርሕጉ ፡ «ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ጉድ ፡» የቀባለው ፡ ከተፈለገው ፡ አገልግሎት ፡ የወጣና ፡ የሰፋ ፡ ነው ። ማስረጃው ፡ «ግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡» ከሆነ ፡ ከጋለሞታ ፡ ወይም ፡ ከሽርሙጣ ፡ ጋራ ፡ የሚደረገው ፡ የግንኙነት ፡ ጉድ ፡ ሁሉ ፡ የጋብቻ ፡ መልክ ፡ ሊኖርበት ፡ ነው ። ማስረጃው ፡ ወይም ፡ መቋጠሪያው ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነቱ ፡ ባይሆን ፡ የግብረቱ ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ ፈሊጥ ፡ ወይም ፡ ሁኔታ ፡ በሆነ ፡ «ውጭን ቅጥ ፡ ጥምረት ፡ (ዕምረት ፡)» ወይም ፡ «ጎብረት ፡» ብንለው ከእንግሊዝኛው ፡ «ኢሬጉላር ፡ ዩኒዮን ፡» መጠጋታችን ፡ እና ፡ ከ «ጎብረቱ ፡» ወበይ ፡ ወይም ፡ ባሕርይ ፡ መቅረባችን ፡ ነው ። «ሀገል ፡ ዕምረት ፡ ማስቱም ፡ ባሰኤዩ ። ነገር ፡ ግን ፡ «የወይ ፡ ለምይ ፡ ግብነት ፡ ጎብረት ፡» ወይም ፡ «የወይ ፡ ግብነት ፡ ጎብረት ፡» የልማድ ፡ መልክ ፡ በበሰግ ፡ ይሰጠዋል ። በዚያም ፡ በላይ ፡ ጎብረቱ ፡ የሚያበከትላቸው ፡ ጉዳቶች ፡ ያጠሩና ፡ የተወሰኑ ፡ መሆናቸውን ፡ ያመለክታል ።

፪ ፡ «በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡» የተባለውን ፡ «ጥንድ ፡ ጋብቻ ፡» ወይም ፡ «ጎብረት ፡» ማለቱ ፡ የተሻለ ፡ ነው ። በእውነቱ ፡ ሁለቱም ፡ ቢሆኑ ፡ የእንግሊዝኛውን ፡ «ቢጋሚ ፡» አያጠግቡም ። የእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ የሚያጠይቀው ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለት ፡ ሴቶች ፡ ወይም ፡ ወንዶች ፡ ጋራ ፡ በጋብቻ ፡ ውል ፡ መታሰርን ፡ ነው ። በላቲን ፡ «ቢ» ማለት ፡ ሁለት ፡ በግሪክ ፡ «ጋሞስ ፡» ማለት ፡ «የጋብቻ ፡» ሲያዋድዷቸው ፡ «የጋብቻ ፡ ጥንድነት ፡» ይሆናል ።

፫ ፡ «ዕክለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡» የተባለው ፡ በለሚረገዝምና ፡ በለማያጠግብ ፡ «ኢእኩል ፡» ወይም ፡ ባማርኛ ፡ «ያለእኩል ፡» ቢባል ፡ የተሻለና ፡ እጥር ፡ ይሆናል ። «እኩል ፡» ማለት ፡ መመጣጠን ፡ ልክ ፡ መሆን ፡ ነው ፡ «ኢ» እሉታ ፡ ነው ።

፬፡ «በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ሰው፡» የተባለው ፡ የተፈለገውን ፡ የሰው ፡ አቋቋምን ፡ አይነግርም ፡ «ኢአኪልም፡» አበረኛም ፡ ወንጀለኛም ፡ . . በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ የሰውየውን ፡ ያእምሮ ፡ ሁኔታ ፡ ስለማያመለክት ፡ መወሰኑን ፡ ብቻ ፡ ማመልከቱ ፡ በቂ ፡ ስለሚሆን ፡ «እክብ» ቢባል ፡ ማስረፊያ ፡ ነው ፡ «ሰቅብ፡» ማለቱ ፡ ደግሞ ፡ መጠበቁን ፡ በበለጥ ፡ ያሳያል ፡ የተሻለ ፡ ነው ። «ውቁን፡»ም ፡ ያስኬዳል ።

፭፡ «የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች፡» የተባለው ፡ በጣም ፡ የተንረፈረፈ ፡ ነው ፤ «ሽምግልና፡» ቢል ፡ ዳኝነትም ፡ እንዳለበት ፡ ያስማል ። እንዲሁም ፡ ከቤተዘመድ ፡ ይልቅ ፡ «ቤተሰብ፡» በባለትዳሮቹ ፡ የሚተዳደረውን ፡ በመከለል ፡ ይወሰናል ። ስለዚህ ፡ «የቤተሰብ ፡ ገላጋዮች፡» ማለቱ ፡ ተፈላጊውን ፡ ያጠግባል ።

፮፡ «ተጋቢ፡አግቢ፡ተጋቢዎች፡አግቢዎች፡» የተባለው፡በንጠላ፡ሲሆን ፤ «በበር፡መሳይ፡» ለጥንዱ ፡ ቢሆን ፡ «ሰበሮች ፡ መሳዮች፡» በበለጥ ፡ ኅብረቱን ፡ ያጐላል ፤ የተለመደም ፡ ነው ።

፯፡ «የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት፡» የተባለው ፡ ካለመለመዱም ፡ በላይ ፡ በጣም ፡ የሚያዋልል ፡ ነው ፡ የሥጋ ፡ ግብር ፡ ወሰኑ ፡ ሰፊ ፡ ነውና ። «ሩካቤሥጋ» ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቢቃውንት ፡ ዘንድ ፡ የታወቀና ፡ የተለመደ ፡ ነው ።

፰፡ «ባሏ ፡ የሞተባት ፡ የብቸኝነት ፡ ኑሮ ፡ ጊዜ፡» የተባለው ፡ ከመራዘሙም ፡ በላይ ፡ ተፈላጊውን ፡ አያሰማም ። ስለዚህ ፡ ባሏ ፡ ለሞተባት ፡ «መበለት፡» ለተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ «የመበለት ፡ ጊዜ/ዕድሜ፡» ይሻላል ።

፱፡ «ለቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ጥቅም ፡ ወጭ፡» የተባለውን ፡ «ለቤተሰቡ ፡ ጣጣ ፡ ወይም፡ ችግር ፡ ዕዳ ፡ ወይም ፡ ወጪ፡» እንዳንዴም ፡ በሚያስኬድበት ፡ «ለቤተሰቡ ፡ ጥቅም» ማለቱ ፡ የተሻለ ፡ ነው ።

፲፡ «የገንዘብ ፡ ሰነዶች፡» የተባለው ፡ አጥጋቢ ፡ አይደለም ። «ቦንድ፡» አንዱ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ (ኩባንያ ፡ ወይም ፡ መንግሥት፡) ለሌላው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ወራሹ ፡ ለመክፈል ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ የሚገልጥ ፡ ማስረጃ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ። «ሴኩሪቲ፡» አንዱ ፡ ለሌላው ፡ ገንዘብ ፡ ሲያበድር ፡ የሚቀበለው ፡ የዋስትና ፡ ሀብት ፡ የምስክር ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ። «ሼር፡» ቦንድ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ለንግዱ ፡ መንቀሳቀሻ ፡ ሰውየው ፡ የከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ የሚያስረዳ ፡ የድርሻው ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ። «የማገቻ፡ሰነድ፡» ለ «ቦንድ፡» «የዋስትና ፡ ሰነድ፡» ለ «ሴኩሪቲ፡» «የአጣ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት፡» ለ «ሼር፡» መጻፉ ፡ ይሻላል ። በተረፈም ፡ እንዳለው ፡ «ቦንድ ፡ ሴኩሪቲ ፡ እና ፡ አክሲዮን፡» ማለቱ ፡ ማለፊያ ፡ ነው ።

፲፩፡ ቅጣት፡» ወይም ፡ «ድንጋጌዎች፡» የተባለው ፡ ተስማሚነቱ ፡ መጠነኛ ፡ ነው ሆኖም ፡ በላይ ፡ ጥቂት ፡ ያዘንቃል ፡ የእንግሊዝኛው ፡ «እገዛ ፡ ሳንክሽን ፡ ቱ ፡ ዘ ፡ ኮንዲሺን ፡ ኦቭ ፡ ማሪየጅ፡» የሚለው ፡ በጭሩ ፡ የጋብቻ ፡ ግዴታ ፡ በመጣሱ ፡ መማጠኛ፡» ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ «ሳንክሽን፡» የተባለው ፡ «የምጥንቃ ፡ ሕግ፡» ወይም ፡ «ምጽዋት/ማዕቀብ ፡ ድንጋጌ፡» ያልነው ፡ እንደሆን ፡ «በምጥንቃ ፡ ጋብቻ ፡ ሲፈርስ ፡ . ብሎ ፡ ለመተርጐት ፡ ያማረ ፡ ይሆናል ።

፲፪ ፡ » » » «ዐብደ ፡ ቤት ፡ ሲዘጋበት፡» የተባለው ፡ ለዕብዶች ፡ ስፈር ፡ ወይም ፡ እየታከሙ ፡ ለሚጠበቁበት ፡ «አሳይሉም፡» ነው ። የግእዙ ፡ «መምሕፃን ፡» መግጠኛ ፡ መሸሻ ፡ መጠጊያ ፡ የሙጥኝ ፡ መባያ ፡ ገዳም ፡ ማለት ፡ ስለሆነ ፡ እንዲለመድ ፡ ቢደረግ ፡ ማለፊያ ፡ ነው ።

፲፫ ፡ » » » "ና" የሚለው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚያዛንቅ ፡ "እና" እያልን ፡ ብንለየው ፡ ጥሩ ፡ ነው ።

፲፬ ፡ » » » «ዋና ፡ መሳሳት» የተባለው ፡ ለእንግሊዝኛው ፡ "ኤሬር ፡ ኦቭ ፡ ሰብስታንስ" ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የእንግሊዝኛው ፡ የስሕተቱን ፡ ዐይነትና ፡ መልክ ፡ ሲያመለክተን ፡ ዐማርኛው ፡ አይገልጽልንም ። ጽርእውያን ፡ (ግሪኮች) «ወስያ»፤ ላቲናውያን ፡ «ሱብስታንቲያ»፤ እንግሊዛውያን ፡ «ሰብስታንስ» የሚሉትን ፡ «ግእዝ ፡ «ሕላዌ» ይለዋል ። ይህንኑ ፡ ቃል ፡ ሲፈታም ፡ ሆላዊ ፡ አስተጋባኢ፡ ባሕርይ ፤ ጠቅላይ ፡ ስም ፤ አኗኗር ፤ ኑሮ ፤ መኖር ፡ መሆን ፡ ይለዋል ። ደግሞም ፡ «መሳሳት» እንደ ፡ «መተሳሰፍ» ክፋትን ፡ ሳያመለክት ፡ አይቀርም ። ስለዚህ ፡ «የሕላዌ ፡ ዝንጋታ» ማለቱ ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነው ።

፲፭ ፡ » » » «የጉማ ፡ ልማድ» የተባለው ፡ ፍችው ፡ ትንሽ ፡ ዕጦር ፡ ስለሚል ፡ «የነገድ፡ ልማድ» ይሻላል ። «ጉማ» መልክንና ፡ መነሻ ፡ ዘርን ፡ የሚለይ ፡ ቅጽል ፡ ነው ፤ «ነገድ» ግን ፡ ወገንና ፡ መጠንን ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ።

፲፮ ፡ » » » «ፈቃድ» የተባለው ፡ ያዛንቃል ። «ፈቃድ»፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከአንዱ ፡ ለሌላ ፡ የሚሰጥ ፡ ሥልጣን ፡ ቀመስ ፡ ሁኔታ ፡ ነው ፤ የእንግሊዝኛው ፡ «ኮንሴንት» ግን ፡ ከፍላጎት ፡ ከመውደድ ፡ ከመሻት ፡ የሚፈልቅ ፡ መስማማት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ለአንዱ ፡ በሚሰጥበት ፡ አጋጣሚ ፡ «ምረቃ»፤ ራሱ ፡ ባለጉዳዩ ፡ በሚያደርግበት ፡ ጊዜ ፡ «ፈቃደኝነት» ቢባል ፡ ይሻላል ።

የዝርዝር ፡ ቃላት ፡ ፍች ፤

ሱታፌ ፤ መተባበር ፤ ማኅበርነት ፤ የማኅበር ፡ ተካፋይነት ፤ ሸርክነት ፤ ባልንጀራነት ፤ ጓደኝነት ።

ማስተንተን ፤ በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ አትኩሮ ፡ ማሰብ ፤ ማውጣትና ፡ ማውረድ ፤ በሐሳብ ፡ ውቅያኖስ ፡ ጠልቆ ፡ ገብቶ ፡ መመራመር ፤ ሐሳቡን ፡ ዘርግቶ ፡ በራስ ፡ መተቸትና ፡ በየመልኩ ፡ ማደራጀት ።

ህልው ፤ ያለ ፡ የኖረ ፡ የነበረ ፤ የሚኖር ፡ ነባር ፡ ቀዋሚ ፡ ከቶ ፡ የማይካድ ፡ እውነት ፤ እንግዲህ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ «ፋክት» የሚለውን ፡ «ህልው»፤ «እስቴት ፡ ኦቭ ፡ ፋክት» የሚለውን ፡ «ህልው ፡ ሁኔታ» ለማለት ፡ ይቻላል ።

መታደግ ፤ ማዳን ፤ መቤዠት ፤ መተው ፤ መዳን ።

ባሕርይ ፤ ፍጥረት ፡ በማይ ፡ ከነገሱ ፡ መሬት ፡ ከነልብሱ ፤ የነገር ፡ ሁሉ ፡ ሥር ፡ መሠረቱ ፤ የጠባይ ፡ መውጫ ። ጽርእውያን ፡ «ፊሲስ»፤ ላቲናውያን ፡ «ናቱራ» የሚሉትን ፡ ግዕዝ ፡ «ባሕርይ» ይለዋል ። ያገራችን ፡ ሊቃውንት ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የተወለደን ፡ ልጅ ፡ ከወላጆቹ ፡ የኑሮ ፡ አቋም ፡ ከብርና ፡ ደረጃ ፡ የወጣ ፤ በባሕርይው ፡ ብቻ ፡ ከወላጁ ፡ የተሳሰረ ፡ መሆኑን ፡ ሲያጠይቁ ፡ (ሲያስረዱ) «የባሕርይ ፡ ልጅ» ይሉታል ።

እንኪያስ ፤ እንግዲያስ ፡ ነው ፤ ለማለዋወጥ ፡ እንዲመች ፡ በማለት ፡ ነው ። እሊህም ፡ «የነዚህ» የሚለው ፡ ቃል ፡ ለውጥ ፡ ነው ።

ማፈጣጠም ፤ ጋብቻን ፡ መሾም ፤ ጋብቻ ፡ መናገር ፤ ጋብቻ ፡ ማወጅ ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በሀገረሰቡ ፡ የተለመዱ ፡ ናቸው ።

ኢ ፤ አሉታ ፤ አል ፤ አ ፤ እንዳ ፤ ላ ፡ ባ ፤ ያል ፤ የማ ፤ እያሰኘ ፡ ከቃል ፡ ፊት ፡ እየገባ ፡ የሚያፈርስ ።

ትውራጅ ፤ የሚያወርድ ፤ «አውራጅ ፡ ዘመድ» እንዲሉ ። «ወራጅ ፡ ዘመድ» የግርጌ ፡ ዘመድ ፡ ማለት ፡ ነው ። ወላጅ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ትርጓሚው ፡ እንደተረዳው ፡ ከአባትና ፡ ከእናት ፡ ሊያልፍ ፡ አይገባውም ፤ «ተወላጅ» የሚለውም ፡ በጣም ፡ የተዘረጋና ፡ ስፊ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የራስጌ ፡ የቅርብ ፡ ዘመድን ፡ «አውራጅ፤» የግርጌ ፡ የቅርብ ፡ ዘመድን ፡ «ወራጅ» ማለቱ ፡ የተሻለና ፡ ባገራችን ፡ የተለመደ ፡ ነው ።

ሰብአዊነት ፤ የሰውን ፡ የባሕርይ ፡ አባሎቹን ፡ የመያዝ ፡ ሁኔታ ፤ « ሰውነት » ግን ፡ የሰውን ፡ አቋም ፡ ማዕርግ ፡ ጠባይና ፡ ግብሩን ፡ የሚያመለክት ፡ ሁኔታ ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ አማርኛው ፡ አገላብጦና ፡ ለውጦ ፡ «ሰብአዊ ፡ መብት ፤ ሰብአዊ ፡ ምግባር ፤ . . .» እያለ ፡ ይጠቀምባቸዋል ። ስለዚህ ፡ «ሰውነት» ሲንል ፡ የባሕርይ ፡ አፈጣጠሩን ፡ ሁኔታ ፡ በማመልከት ፤ «ሰብአዊነት» ስንል ፡ ግብሩንና ፡ ጠባዩን ፡ በማለት ፡ መወሰን ፡ ይሻላል ።

ማከብ ፤ መሰብሰብና ፡ መወሰን ፡ ማጠር ፤ አንድላይ ፡ ቆልሎ ፡ ማከማቸት ፤ የተዝረፈረፈ ፡ ነገርን ፡ ወይም ፡ የተትረፈረፈን ፡ ዕቃ ፡ ሰብስቦ ፡ አድርጎ ፡ ማስቀመጥ ፡ መያዝ ፡ መጠበቅ ፤ መወሰን ፡ ነው ። «እከብ» ከዚህ ፡ ነው ፡ የወጣው ፤ በጤናና ፡ በነጻነት ፡ መሆን ፡ ያትረፈርፋል ፤ ሕመም ፡ ግን ፡ ይልቁንም ፡ የአእምሮ ፡ ይወስናል ።

ወግ ፤ ልማድ ፡ ሥርዓት ፤ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ የቈየ ፡ የነገድ ፡ ልማድ፡ «ወግና ፡ ልማድ» እንዲሉ ።

ነገድ ፤ ወገን ፤ ያንድ ፡ አባት ፡ ዘር ፤ ልጅ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፤ ዘመድ ፡ ተወላጅ ፡ እንደ ፡ ንህብና ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ገንዘብ ፡ እየበዛ ፡ እየተራባ ፡ እውፉ ፡ እያበጀ ፡ የሚሄድ ፡ ነው ።

መዘነቅ ፤ ያለቅጥና ፡ ያለሥርዓት ፡ መደባለቅ ፡ መግርንቅ ፤ መዘባረቅ ።

መመለል ፤ ፈሊጥ ፡ መንደፍ ፤ ለእምነት ፡ የሚሆን ፡ መንገድ ፡ የውሬድንብሩን ፡ መላ ፡ መጣል ፤ ማስብ ።

መፋሰስ ፤ ከፍርድ ፡ ፊት ፡ ለዳኝነት ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ ጉዳያቸውን ፡ አብራርተው፡ መዘርጋት ፤ የምስክር ፡ ቃልን ፡ ማስማትና ፡ ለመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ መዘርጋት ፡ ማቅረብ ።

መበለት፤

ይህ ፡ ቃል ፡ «በልቶ ፡ በልቶት» ከሚለው ፡ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ የወጣ ፡ ትር ጕሙም ፡ መበለት ፡ መለየት ፡ መነጠል ፡ ሥጋን ፡ በየብልቱ ፡ ማውጣት ፡ ማደኽየት ፡ ድኻ ፡ ብቸኛ ፡ ማድረግ ፡ ብቻ ፡ ማስቀረት ፡ ነው ። ሊቁ ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ ሲያፍታቱት ፡ «በጋማች ፡ ሥጋን ፡ ከሥጋ ፡ እንዲለይ ፡ ሞት ፡ ከባሏ ፡ የለያት፡የነጠላት ፤ ድኻ ፡ ብቸኛ ፡ ሴት» ይላሉ ። እንግዲህ፡ መበለትን ፡ መነኵሲት ፡ ማድረጉ ፡ የዘመን ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የመዝገበ ፡ ቃላት ፡ አዋጅ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ባሏ ፡ የሞተባትን ፡ «መበለት» ማለቱ ፡ ተገቢ ፡ ነው ።

«ጽሑፍ ፡ ነጋሪ»፤

በእንግሊዝኛው ፡ «ኖታሪ» ለሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ። «አስታዋሽ» ወይም ፡ «አገናዛቢ» ብንለውም ፡ ያጠግባል ። «ኖታሪ» ማለት ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ በሚ ቀበሉት ፡ መልክ ፡ «ውልን ፡ የሚያዋውል ፡ የሚመዘግብና ፡ የሚያኖር» ማለት ፡ ነው ። የእንግሊዝኛው ፡ ቃልም ፡ የወጣው ፡ «ኖት» (ማስታወስ ፡ ወይም ፡ መገንዘብ) ከሚለው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ «ለማ ዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው» እያሉ ፡ ከማራዘሙ ፤ ወይም ፡ በእንግሊ ዝኛው ፡ . . . «እን ፡ እክት ፡ ኦቭ ፡ ኖታሪ» የሚለውን ፡ «በፍርድ ፡ ፊት ፡ ግልጽ ፡ ጽሑፍ» ከማለቱ ፡ «የጽሑፍ ፡ ነጋሪ ፡ ማስታወሻ/መገንዘቢያ»፡ ወይም ፡ በደፈናው ፡ «መገንዛዘቢያ» ማለቱ ፡ የተሻለና ፡ በቀላሉ ፡ የሚስ መድ ፡ ነው ።

ይኋል ፤

ማለት ፡ መናገር ፤ ይላል ፡ ነው ። ልዩነቱ ፡ ጾታ ፡ አለመለየቱ ፡ ነው ፤ ለምሳሌ፡ የእንግሊዝኛውን ፡ «ሲነምበር . . . » (ይህንና ፡ ያንን፡ ቊ . . . ተመልከት) ብሎ ፡ መተርጐሙ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ተገቢው ፡ «ቊ . . . ይመለከቷል» ነው ። ይህ ፡ ላድራጊው ፡ ሆነ ፡ ለተቀባዩ ፡ የሚውል ፡ አጠቃላይ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ «<u>ይገነዘቧል ፡ ይተረጐሟል ፡ ይሠሯል ፡ ያደርጓል ፡ ይወ ስዷል ፡ ይደነግጓል ፡ . .</u> .» የተለመዱ ፡ የሊቃውንት ፡ ዘይቤ ፡ ናቸው ።

በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የጋብቻ ፡ አቋም ።

ከዊልያም ፡ ቡሐጂየር ፡
የኢትዮጵያ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡
ፕሬዚዳንት ።

በውእነቱ ፡ በክርስቲያኗ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እንደነበረው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ጋብቻ ፡ ያንድ ፡ ላንድ ፡ ኅብረት ፡ ነው ፡ ማንኛውንም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎችን ፡ ሳይጨምር ፡ አንዱ ፡ ወንድና ፡ አንዲ ፡ ሴት ፡ በነዛኛቸው ፡ የሚጋቡበት ፡ የፈቃድ ፡ ሱታፌ ፡ ነው ። ሕጉ ፡ ሦስት ፡ የጋብቻ ፡ ዐይነቶችን ፡ —(1)ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ (2) የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ (3)የልማድ ፡ ጋብቻን ፡ ያስተነትናል ። ጋብቻ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከሴህ ፡ ሥርዓቶች ፡ በማናቸውም ፡ አንዱ ፡ ዓይነት ፡ ሥርዓት ፡ ሊከናወን ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በባልዩውና ፡ በሚስቲቱ ፡ መካከል ፡ በሚመለከተው ፡ የግል ፡ ዝምድና ፡ (ግንኙነት ፡) ሆነ ፡ ወይም ፡ ሀብታቸውን ፡ በሚመለከተው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ጋብቻው ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ በሦስቱም ፡ የጋብቻ ፡ መልኮች ፡ ያው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውጤትን ፡ ነው ፡ በልማድ ፡ ጋብቻም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ስለምን ፡ ቢሉ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጋብቻው ፡ የተከናወነው ፡ የባልየውን ፡ ወይም ፡ የሚስቲቱን ፡ የወግና ፡ ልምድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተከትሎም ፡ ቢሆን ፡ ቅሉ ፡ የጋብቻው ፡ ውጤቶች ፡ የሚዳኙት ፡ ጋብቻው ፡ በተከናወነበት ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ በሕጉ ፡ (ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡)ድንጋጌዎች ፡ እንዲሆን ፡ ሲባል ፡ ነው ፡ ይላል ።

ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ማለት ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዝግብት ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ የሚፈጣጠሙት ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ ማለት ፡ በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ ባንዱ ፡ ሃይማኖት ፡ ያፈጸጸም ፡ ሥርዓቶች ፡ መሠረት ፡ የሚሾመው ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። (እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሃይማኖት ፡ ቢሸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይም ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ያፈቀደው ፡ የሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።) የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ የሚባለው ፡ በነበሮቹ ፡ ነገድ ፡ ወይም ፡ ከዓበሮቹ ፡ ባንዱ ፡ ነገድ ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡ ኑዋሪ ፡ የሆነውን ፡ ጥምረት ፡ ሲያቋቁሙ ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ በደመወዝ ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ የታወቀ ፡ አይደለም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ቆየት ፡ ብለን ፡ እንደምናየው ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ ፈንታ ፡ ወዶገብ ፡ ኅብረት ፡ የተባለውን ፡ በተወሰነ ፡ አኳኋን ፡ በፍርድ ፡ የታወቀውን ፡ ባንድ ፡ ወንድና ፡ ባንድ ፡ ሴት ፡ መካከል ፡ ያለን ፡ ሀልው ፡ ሁኔታን ፡ ሕጉ ፡ ይተካል ።

፩፤ ለማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ የሚያገለግሉ ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ።

ግዴታዎች ፤

ከላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዓቶች ፡ በማናቸውም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማንኛውም ፡ ጋብቻ ፡ ከመከናወኑ ፡ በፊት ፡ ሊፈጸሙ ፡ የሚገባቸው ፡ አንዳንድ ፡ ግዴታዎች ፡ አሉ ። እሊህም ፡ እንደሚከተለው ፤ ዕድሜ ፤ የሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ጥንድ ፡ ጋብቻ ፡ እና ፡ ለማግባት ፡ ፈቃደኝነት ፡ ናቸው።

፩፡ ዕድሜ ፤–በዕድሜው ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ያልደፈነ ፡ ወንድና ፡ በዕድሜዋ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ያልሞላት ፡ ሴት ፡ ጋብቻን ፡ ሊያደርጉ ፡ አይችሉም። ከዚህ ፡ ግዴታ ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፡ ሊታደግ ፡ የሚችል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወይም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ሲል ፡ የሾመው ፡ ሰው ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ እንደ ዚህ ፡ ያለው ፡ ታዳጊነት ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ በታች ፡ ለመቀነስ ፡ አይፈቀድም ፡ ይኸውም ፡ በታዳጊነቱ ፡ መሠረት ፡ ከሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ላላነሰ ፡ ወንድና ፡ ከሥራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ላላነሰች ፡ ሴት ፡ ጋብቻ ፡ ሊሾም ፡ ይቻላል ፡ ማለት ፡ ነው ። (ቍጥር ፡ ፭፻፹፩ ።)

፪፤ የሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፤– እሊህ ፡ የጋብቻ ፡ አደናቃፊዎች ፡ ናቸው ፡ በሥጋ ፡ በተዘማመዱና ፡ በጋብቻ ፡ በተዘማመዱ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ ክልክል ፡ ነው ። (ቍጥር ፡ ፭፻፹፪ ፡ እና ፡ ፭፻፹፫ ።) እንዲሁም ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ በይታወቅላቸውም ፡ ቅሉ ፡ ዕርግጠኛ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅነት ፡ መተሳሰሪያቸው ፡ በይፋ ፡ በታወቀላቸው ፡ የሥጋ ፡ ዘመዳሞች ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዘመዳሞች ፡ መሆን ፡ በሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ እንዳይሾም ፡ ቍጥር ፡ ፭፻፹፬ ፡ ይከለክላል ። የሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ውስጠ ፡ ምስጢሩ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፶ ፡ እና ፡ በተከታታዮቹ ፡ ቍጥሮች ፡ ላይ ፡ ተተርጉሟል ።

፫፤ ጥንድ ፡ ጋብቻ ፡ ፤–ለማጋባት ፡ ከአቀዱት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ በቀደመ ፡ ጋብቻ ፡ የተቀየደ ፡ ከሆነ ፡ የቀድሞው ፡ ጋብቻ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ በነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ ሊሾም ፡ አይቻልም ።(ቍጥር ፡ ፭፻፹፭ ።)

፬፡ ፈቃደኛነት ፤—እንደ ፡ ሌላው ፡ ውል ፡ ሁሉ ፡ ጋብቻም ፡ ነባር ፡ ዋጋ ፡ እንዲኖረው ፡ መሳይ ፡ ወገኖቹ ፡ ተፈቃቅደው ፡ እንዲስማሙ ፡ ያስፈልጋል ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ፈቃደኛነትም ፡ ነጻ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፤ ይኸም ፡ በኃይል ፡ አስገዳጅነት ፡ ያላስተፋት ፡ ፈቃድ ፡ እና ፡ በማናቸውም ፡ የሕላዌ ፡ ዝንጋታ ፡ ያልተበከለ ፡ ፈቃድ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። የጋብቻ ፡ በዓል ፡ በሚከናወንበት ፡ ጊዜ ፡ ዓበሮቹ ፡ ራሳቸው ፡ መፈቃቀዳቸውን ፡ እንዲያስታውቁ ፡ ይገባል ። ፈቃደኝነታቸውን ፡ ለማስታወቅ ፡ መሳዮቹ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሊወክሉ ፡ አይችሉም ፤ ይኸም ፡ ጋብቻ ፡ በእንደራሴ ፡ አይፈቀድም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖር ፡ ጠቅላይ ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ከዚህ ፡ መታደጊያ ፡ የሚሆን ፡ ፈቃድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ፡ (ቍጥር ፡ ፭፻፹፯ ።) ኢአክል ፡ (ያለ ፡ አክል ፡) ሰው ፡ በሚያገባበት ፡ ጊዜ ፡ የራሱ ፡ የኢአክሉና ፡ ቤተ ፡ ዘመዱን ፡ የወከለው ፡ ሰው ፡ እንደራሴ ፡ ፈቃደኝነት ፡ ያስፈልጋል ። በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ሰውን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ የራሱ ፡ ፈቃደኝነት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለዚሁ ፡ ሲል ፡ በሚሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ መደገፍ ፡ ይገባዋል ፡ (ቍጥር ፡ ፭፻፺፩ ፡ እና ፡ ፫፻፴፱ ።)

በኃይል ፡ አስገዳጅነት ፡ የተገኘ ፡ ፈቃደኝነት ፡ ንጹሕ ፡ (ጥሩ- ነጻ ፡) ፈቃድ ፡ ስላልሆነ ፡ አንዳችም ፡ ዓይነት ፡ ፈቃደኝነት ፡ አይደለም ። ፈቃደኝነትን ፡ የሚያበላሽ ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ የኃይል ፡ ተግባር ፡ አይደለም ፤ በቊጥር ፡ ፭፻፹፱ ፡ (፪ ፡) መሠረት ፡ ፈቃደኝነት ፡ የሚጐድፈው ፡ ራሱን ፡ ወይም ፡ ራሷን ፡ ወይም ፡ ከወራጅ ፡ ዘመዶቹ ፡ ወይም ፡ ከአውራጅ ፡ ዘመዶቹ ፡ አንዱን ፡ ከባድ ፡ ከሆነ ፡ ጉዳትና ፡ ዛቻ ፡ ለማዳን ፡ ሲል ፡ በመጨነቅና ፡ በመገደድ ፡ የተፋው ፡ ፈቃደኝነት ፡ ሲሆን ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ስቃይም ፡ የማይዳሰስ ፡ ረቂቅ ፡ የመንፈስ ፡ ወይም ፡ የሚዳሰስ ፡ ግዙፍ ፡ (የሚጨበጥ-ሥጋዊ ፡) ሊሆን ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ጉዳት ፡ በጊዜ ፡ ርዝማኔ ፡ ሊያልፉት ፡ ወይም ፡ በማዘግየት ፡ ሊገፉት ፡ የማይቻል ፡ ከባድ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። ፍዳው ፡ ያልከበደ ፡ ወይም ፡ የማያሰጋ ፡ ሲሆን ፤ ፈቃደኝነትን ፡ ያስገኘው ፡ ኃይል ፡ ፈቃድን ፡ አያበላሽውም ። አውራጅ ፡ ዘመዶችን ፡ ወይም ፡ ማንኛውን ፡ ሌላ ፡ ሰውን ፡ በማክበርና ፡ በማፈር ፡ የገቡበት ፡ የፈቃደኝነት ፡ ቃል ፡ የጐደፈ ፡ አይደለም ፤ ይኸም ፡ አውራጅ ፡ ዘመድን ፡ (ለምሳሌ ፡ አባትን ፤ ወንድ ፡ አያትን ፤ ሴት ፡ አያትን ፤) ወይም ፡ ማንኛውንም ፡ አውራ ፡ ዘመድ ፡ ባይሆን ፡ እንኳን ፡ <u>ዘመድ ፡ አካል ፡ ተብሎ ፡ የሚቆጠር ፡</u> ሌላ ፡ ሰውን ፡ በማክበር ፡ የገቡበት ፡ ፈቃድ ፡ የተጓደለ ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ (ቊጥር ፡ ፭፻፹፱ ፡ (፫) ።)

<u>ከህላዌ ፡ ዝንጋታ ።</u> የተነሣ ፡ ፈቃደኝነት ፡ የሚበላሸው ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ (መሳዩን ፡) ነክ ፡ ስለሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ ሳያውቅ ፡ መስሎት ፡ ተሳስቶ ፡ ቃል ፡ የገባበት ፡ ፈቃደኝነት ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ቊጥር ፡ ፭፻፺፩ ፡ ህላዌ ፡ ዝንጋታ ፡ ተብለው ፡ ፈቃደኝነትን ፡ ለማበላሸት ፡ በቂ ፡ የሚሆኑ ፡ የተወሰኑ ፡ ምክንያቶች ፡ ዝርዝርን ፡ ይሰጣል ። እሊህም ፡ እንደሚከተሉት ፤ –

ሀ/ የመሳዩን ፡ አካል ፡ መዘንጋት ፡ (መሳት ፤) ወይም ፡

ለ/ የአበሩን ፡ ሃይማኖት ፡ መዘንጋት ፤ ወይም ፡

ሐ/ የመሳዩን ፡ ጤንነት ፡ ወይም ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ችሎታ ፡ መዘንጋት ፡ ናቸው ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ዝንጋታውን ፡ በ<u>ሚያገቡት ፡ ሰው ፡ አካላዊ ፡ ባሕርይ ፡</u> በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ ይወስናል ፤ ማለት ፡ መሳሳቱ ፡ በአበሩ ፡ <u>ባሕርያዊ ፡ አካል ፡ አቋም ፡</u> እንደሆነ ፡ አጉልቶ ፡ ይገልጣል ። ሕጉ ፡ የተገለገለባቸው ፡ ቃሎች ፡ በሌላ ፡ ሕጐች ፡ ዘንድ ፡ ከተነሡት ፡ አሻሚ ፡ ብዙ ፡ ክርክሮች ፡ ይገላግላሉ ። ለምሳሌ ፡ በፈረንሳይ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ (ቊጥር ፡ ፩፻፹ ፡ (፪) ፡) እና ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓውያን ፡ አቆጣጠር ፡ በ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢጣሊያን ፡ አገር ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ (ቊጥር ፡ ፩፻፳፪ ፡) ይ ፡ የሠፈሩት ፡ ቃሎች ፡ ‹እውሬር ፡ ሱር ፡ ላ ፡ ፐርሰን ›› (በሰብአዊነቱ ፡ ላይ ፡ መሳሳት ፡) እና ፡ « ኤሮሬ ፡ ኒላ ፡ ፔርሶና ፡ » (በሰብአዊነቱ ፡ ላይ ፡ መሳሳት ፡) ነበሩ ። አከራካሪው ፡ ጉዳይ ፡ ሰብአዊነት ፡ ሲል ፡ ስለ ፡ አበሩ ፡ አካላዊ ፡ ባሕርይ ፡ ሲያጣይቅ ፡ ብቻ ፡ ነውን ? ወይስ ፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ አበሩ ፡ ተፈላጊ ፡ የመለያ ፡ ጠባዮችን ፡ ጭምር ፤ (ለምሳሌ ፡ የምትገባውን ፡ ሚስት ፡ ድንግላይነትን ፡ የመሰለ ፡ ወይም ፡ አበሩ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ተወንጅሎ ፡ መቀጣቱን ፡) የሚለው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ግን ፡ የስሕተቱ ፡ መጠን ፡ ያከበው ፡ በአበሩ ፡ <u>አካላዊ – ባሕርይ ፡</u> ላይ ፡ መሳሳትን ፡ ነው ። ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ ከፖ

ቷዬ ፡ የተሰጠንን ፡ ትችት ፡ እናውሳ ፤ ለምሳሌ ፡ ማሪን ፡ ለማግባት ፡ ቊርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረግኩና ፡ ከማሪ ፡ ጋሬ ፡ የተፈጣጠምኩ ፡ መስሎኝ ፡ ራሷን ፡ የማሪ ፡ አምሳያ ፡ አድርጋ ፡ ለማለፍ ፡ ለምትችለው ፡ ለገሮን ፡ የመሐላ ፡ ቃሌን ፡ ገባሁላት ፡ » የሚል ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ አበሩ ፡ በሕዝብ ፡ ማኅበር ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ የደረጃ ፡ አቋም ፡ (ሰሲያል ፡) ወይም ፡ ስለ ፡ አበሩ ፡ የገንዘብ ፡ ሀብት ፡ አቅም ፡ መሳሳት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አበሩ ፡ ልዩ ፡ ግብሮች ፡ (ጠባዮች ፡) ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ስሕተት ፡ ፈቃደኝነትን ፡ ሊያበላሽ ፡ አይችልም ።

<u>ስለመሳዩ ፡ ሃይማኖት ፡ መዘንጋት</u> ፡ ፈቃደኝነትን ፡ ሊያጓድል ፡ የሚችለው ፡ የመሳዩ ፡ ሃይማኖት ፡ ከተሳሳተው ፡ አበር ፡ ሃይማኖት ፡ የተለየ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እነሆ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖት ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ሊያገባት ፡ ያቀዳት ፡ ሴትዮ ፡ በእርግጡ ፡ በሱው ፡ ሃይማኖት ፡ ያለች ፡ ሳለ ፡ የግሪክ ፡ አርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖት ፡ ልጅ ፡ ነች ፡ ብሎ ፡ ቢያስብ ፡ ፈቃድን ፡ ሊያጕድፍ ፡ የሚችል ፡ የህላዌ ፡ ዝንጋታ ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለጤንነት ፡ ሁኔታ ፡ መሳሳት ፡ የሚባለው ፡ አበሩ ፡ ጤነኛ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሲታመን ፡ ሳለ ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ የያዘው ፡ ሆኖ ፡ በሚገኘው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የታከበ ፡ ነው ። ደግሞም ፡ የጋብቻን ፡ ጣዕም ፡ በምሉ ፡ ለማርካት ፡ የሚያገባው ፡ ሰው ፡ ስለሌላው ፡ አበር ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋን ፡ ተግባር ፡ ለማከናወን ፡ ተፈላጊ ፡ ስለሆኑት ፡ አባሎች ፡ አቅም ፡ በተሳሳተ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃደኛነቱ ፡ ለመጓደሉ ፡ በቂ ፡ ስሕተት ፡ አለማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ መሳዩ ፡ ያባለ ፡ ዘር ፡ ደዌ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ከንደዚህ ፡ ያለው ፡ ደዌ ፡ የተነሳ ፡ አበሩ ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ፡ተግባርን፡ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ ባባለዘር፡ ደዌ ፡ ይሠቃይ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ የመሆኑ ፡ ሀልው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድን ፡ ለማበላሸት ፡ የሚበቃ ፡ የህላዌ ፡ መሳሳት ፡ ሆኖ ፡ አይገመትም ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ቊጥር ፡ ፭፻፺፩ ፡ መሠረት ፡ ፈቃድኝነትን ፡ ለማጉደፍ ፡ በቂ ፡ የህላዌ ፡ ስሕተቶች ፡ ሆነው ፡ የማይቆጠሩት ፡ ሌላውን ፡ ዐበር ፡ በሚመለከቱት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተፈጸሙት ፡ ስሕተቶች ፡ ከበድ ፡ ያልሆነን ፡ የፍቺ ፡ ምክንያትን ፡ ሊያስከትሉ ፡ ይችላሉ ፤ ለምሳሌ ፡ አንዱ ፡ መሳይ ፡ ስለሌላው ፡ አበር ፡ በመልክም ፡ ጤንነት ፡ መኖር ፡ እምነቱ ፡ ማስረጃ ፡ እያለው ፡ ባባለ ፡ ዘር ፡ ደዌ ፡ ተበክሎ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ያንዳንድን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ ሀገርን ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡ ተከትለን ፡ ባልየው ፡ ሚስቲቱን ፡ ከነሕጓ ፡ ነች ፡ ብሎ ፡ አምኖ ፡ ሳለ ፡ የጋብቻው ፡ ዕለት ፡ ይኸው ፡ ሕጓ ፡ ባይገኝ ፡ ለፍቺ ፡ መነሾ ፡ በቂ ፡ ምክንያትን ፡ ያቀርባል ፡ ብሎ ፡ ለማመን፡ ይቻላል ፡ እንጂ ፤ ጋብቻው ፡ የፈረሰበት ፡ (ዋጋ ፡ አልባ፡የሆነበት ፡)ምክንያት ፡ ከህላዌ፡ ስሕተቶች ፡ የተነሣ ፡ ፈቃደኝነቱ ፡ በመጓደሉ ፡ ነው ፡ አያሰኝም ።

<u>ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ መቃወሚያ ፡ ማቅረብ ።</u>

የቊጥር ፡ ፭፻፰ ፡ ድንጋጌዎችንና ፡ ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ የጋብቻ ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ከመከናወኑ ፡ በፊት ፡ ስለሚፈጽሙት ፡ ግዴታዎች ፡ በመመልከት ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ጋብቻን ፡ ለማገድ ፡ መቃወማቸውን ፡ ሕጉ ፡ ይቀበላል ። በቊጥር ፡ ፭፻፺፪ ፡ መሠረት ፡ እንደዚህ ፡ የመሰለውን፡ማገጃ ፡ ምክንያት ፡ ሊያቀርቡ፡የሚችሉት ፡ ሰዎች ፡ በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱት ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ እነርሱም ፡—

ሀ/ ከሚጣመሩት ፣ ያንዱ ፣ ቤተ፣ዘመድ ፣ እንደራሴ ፣ (ይኸውም ፣ በቁጥር ፣ ፮፻፺፪ ፣ የተጠራውን ፣ ሰው ፣ ወይም ፣ የኢአኪሉ ፣ ጠባቂ ፣ ሞግዚትን ፣ ማለት ፣ ነው ፣) ለጋብቻው ፣ ከሚፈለገው ፣ ዕድሜ ፣ ደረጃ ፣ ባለመድረሱ ፣ ምክንያት ፣ ወይም ፣ የሥጋ ፣ ወይም ፣ የጋቢ ፣ ዝምድና ፣ በመኖሩ ፣ ምክንያት ፣ ወይም ፣ የቤተ ፣ ዘመዱ ፣ እንደራሴ ፣ ጋብቻውን ፣ ካለመፍቀዱ ፣ የተነሣ ፣ እንደዚህ ፣ ያለውን ፣ መቃወሚያ ፣ ለማቅረብ ፣ ይችላል ። አበሩ ፣ ከዚህ ፣ ቀደም ፣ ያገባ ፣ ሲሆን ፣ ማገጃ ፣ ምክንያትን ፣ ሊያቀርብ ፣ የሚችለው ፣ አቃቤ ፣ ሕግ ፣ ነው ። (ቁጥር ፣ ፮፻፺፭ ፣ (፪) ፤

ለ/ ለምሳሌ ፣ ያህል ፣ ከሚጣመሩት ፣ ሰዎች ፣ መካከል ፣ አንዱ ፣ ከዚህ ፣ ቀደም ፣ በተደረገ ፣ የጋብቻ ፣ ውል ፣ የተቀየደ ፣ ሆኖ ፣ ሲገኝ ፣ አቃቤ ፣ ሕግ ፣ ማገጃ ፣ መቃወሚያን ፣ ለማቅረብ ፣ ይችላል ።

ማገጃ ፣ ለማቅረብ ፣ ልዩ ፣ መልክና ፣ ሥርዓት ፣ እንዲደረግለት ፣ ሕጉ ፣ አልወሰነም ፣ የጋብቻው ፣ በዓል ፣ እስከሚከናወንበት ፣ ሰዓት ፣ ድረስ ፣ ባለው ፣ በማናቸውም ፣ ጊዜ ፣ ማገጃ ፣ ምክንያቱ ፣ ሊቀርብ ፣ ይችላል ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፺፮ ፣) ። ከአበሮቹ ፣ ውስጥ ፣ አንዱ ፣ መቃወሚያው ፣ እንዲቀር ፣ ለመጠየቅ ፣ ይችላል ፤ ግን ፣ እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ጥያቄ ፣ ሳይፈቀድለት ፣ ቢቀር ፣ ይግባኙ ፣ ከፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ፊት ፣ ይዘረጋል ፣ ማለት ፣ ነው ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ በጋብቻው ፣ መቃወሚያ ፣ የቀረበበት ፣ ሰው ፣ ዕድሜ ፣ ከሃያ ፣ ዓመት ፣ በታች ፣ የሆነ ፣ ሲሆንና ፣ ማገጃው ፣ የቀረበውም ፣ ወደፊት ፣ ከሚአብሩት ፣ አንዱ ፣ ወይም ፣ ሁለተኛው ፣ አባት ፣ ወይም ፣ እናት ፣ የመነጨ ፣ ሲሆን ፣ ለእንደዚህ ፣ ያለው ፣ መቃወሚያ ፣ የይግባኝ ፣ አቤቱታ ፣ ሊኖረው ፣ አይችልም ። ይግባኙን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ሰምቶ ፣ ማገጃው ፣ እንዲሻር ፣ ከበየነ ፣ በኋላ ፣ በእንደዚህ ፣ ያሉት ፣ አበሮች ፣ መካከል ፣ የጋብቻው ፣ በዓል ፣ እንዳይፈጸም ፣ እንደገና ፣ ማገጃ ፣ ሰበብ ፣ ለማቅረብ ፣ የተፈቀደ ፣ አይደለም ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፺፯ ።)

በቁጥር ፣ ፯፻፳፫ ፣ በተመለከቱት ፣ ማናቸውም ፣ ምክንያቶች ፣ የተነሣ ፣ የጋብቻ ፣ ዘመኑዋ ፣ ከፍጻሜ ፣ የደረሰባት ፣ ሴት ፣ (ይኸውም ፣ በባሏ ፣ ሞት ፣ ምክንያት ፣ ወይም ፣ በፍቺ ፣ ወይም ፣ ከጋብቻ ፣ ግዴታዎች ፣ አንዱ ፣ በመጣሱ ፣ ምክንያት ፣ ጋብቻው ፣ የፈረሰበት ፣) የመጀመሪያው ፣ ጋብቻ ፣ ከተደመደመበት ፣ ጊዜ ፣ እንሥቶ ፣ አንድ ፣ መቶ ፣ ሰማንያ ፣ ቀኖች ፣ እስኪያልፉ ፣ ድረስ ፣ አዲስ ፣ ጋብቻ ፣ ለመዋዋል ፣ አትችልም ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ ፩፻፹ ፣ ቀኖቹ ፣ ከማለቃቸው ፣ በፊት ፣ ባለው ፣ በማናቸው ፣ ጊዜ ፣ ልጅ ፣ የወለደች ፣ እንደሆነ ፣ ይህ ፣ የንደገና ፣ ማግባት ፣ ክልከላ ፣ አይጸናባትም ። በወዶገብነት ፣ ኅብረት ፣ ካንድ ፣ ወንድ ፣ ጋር ፣ በኖረች ፣ ሴትም ፣ ላይ ፣ ይኸው ፣ ክልከላ ፣ ይረጋባታል ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፺፰) ። በዚህ ፣ አንቀጽ ፣ የተመለከተው ፣ የመከልከል ፣ ተግባር ፣ አባትነትን ፣ በሚመለከቱ ፣ ጉዳዮች ፣ ከማናቸውም ፣ መዛነቅ ፣ ለመራቅ ፣ ሲባል ፣ ነው ፤ በፊተኛው ፣ ጋብቻ ፣ የተጸነሰ ፣ ሕፃን ፣ በማሕጸን ፣ መኖሩን ፣ ለመረዳት ፣ የ፩፻፹ ፣ ቀን ፣ ዕድሜ ፣ በቂ ፣ ነው ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ያገባች ፣ ሴትን ፣ የመበለትነት ፣ ጊዜዋን ፣ ከመጠበቅ ፣ ሊታደጋት ፣ ይችላል ። እንደዚህ ፣ ያለውን ፣ ታዳጊነት ፣ ለመስጠት ፣ የሚቻለውም ፣ ለምሳሌ ፣ ሴትየዋ ፣ ልጆችን ፣ ለመውለድ ፣ አለመቻሏን ፣ ለማረጋገጥ ፣ በሚቻልበት ፣ አባትነትን ፣ ስለሚመለከቱት ፣ ማናቸውም ፣ አጠራጣሪ ፣ ጉዳዮች ፣ ምንም ፣ ሥጋት ፣ በሌለ ፣ ጊዜ ፣ ነው ።

፬ ! የልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ብጋቻዎች ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ ሥርዓቶች ።

<u>ብሔራዊ፡ጋብቻ</u> ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከወላጆቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከአውራጅ ፡ ዘመዶቹ ፡ አንዱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ጋብቻው ፡ ከሚከበርበት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ለስድስት ፡ ወር ፡ መኖሪያውን ፡ በቋቋመበት ፡ ሰፍራ ፡ ላይ ፡ በቀበሌው ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ የሚፈጣጠሙት ፡ ጋብቻ ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፭፻፺፯) ። ጋብቻው ፡ የሚደረግበት ፡ ዕለት ፡ በሚአብሩትና ፡ በሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ መካከል ፡ በስምምነት ፡ ይቆረጣል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፰) ። የወደፊት ፡ አበሮቹና ፡ አራት ፡ (ማለት ፡ ለያንዳንዱ ፡ አበር ፡ ሁለት) ፡ ምስክሮች ፡ በሉበት ፡ ጋብቻው ፡ በይፋ ፡ ይነገራል ፤ እነዚህ ፡ ምስክሮችም ፡ ለወደፊቱ ፡ አበሮች ፡ ሊዛመዱ ፡ ወይም ፡ ላይዛመዱ ፡ ይችላሉ ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፫) ። የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ጋብቻውን ፡ ከመሾሙ ፡ በፊት ፡ የወደፊት ፡ አበሮቹና ፡ ምስክሮቻቸው ፡ በሚያውቁት ፡ መጠን ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚያስከለክል ፡ አንዳችም ፡ እንቅፋት ፡ (ለምሳሌ ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡) አለመኖሩን ፡ ገልጠው ፡ የመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ ይሰጣሉ ። መሐላ ፡ ከገቡም ፡ በኋላ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ከሁለቱም ፡ አበሮች ፡ አንድ ፡ በንድ ፡ በተራ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ለመሆን ፡ መፈለጋቸውን ፡ የሚያረጋግጡበትን ፡ ቃል ፡ ይቀበላል ። ማረጋገጫ ፡ ቃሉን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ በሕግ ፡ ስም ፡ ሁለቱንም ፡ አበሮች ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ብሎ ፡ ይለፍፋል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፬) ።

ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ሊተሳሰሩ ፡ ሲያቅዱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የታቀደው ፡ ጋብቻ ፡ ከሚከበርበት ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ አስቀድመው ፡ ስለዕቅዳቸው ፡ ለሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ፡ (ቍጥር ፡ ፭፻፺፱) ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙን ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚያደናቅፍ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚያግድ ፡ ምክንያት ፡ መኖሩን ፡ ራሱ ፡ ለማመኑ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ያለው ፡ እንደሆነ ፡ ጋብቻውን ፡ ከመሾም ፡ መታገዱ ፡ ግዴታው ፡ ነው ፤ ጋብቻቸውን ፡ በመሾሙ ፡ ያገዱትን ፡ ምክንያቶችም ፡ ወደፊት ፡ ለሚአብሩት ፡ መሳዮች ፡ ያስታውቃል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፪) ። የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ጋብቻውን ፡ ስላገደባቸው ፡ በሁለቱ ፡ አበሮች ፡ ማነኛውም ፡ አንዱ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይግባኝ ፡ ሊል ፡ ይችላል ፤ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ክልከላው ፡ ትክክለኛ ፡ አለመሆኑን ፡ የደረሰበት ፡ እንደሆነ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ጋብቻቸውን ፡ እንዲሾም ፡ ይገደዳል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ በበየነ ፡ ጊዜ ፡ ሹሙ ፡ በማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ምክንያት ፡ አሳቦ ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ ሊከለክል ፡ አይችልም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፭) ።

የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ የሚከበረው ፡ የበለ ፡ ጉዳይ ፡ ወገኖቹ ፡ ሃይማኖት ፡ ከደነበው ፡ ሥርዓቶች ፡ ጋራ ፡ በሚስማማ ፡ መልክ ፡ ነው ። የሃይማኖት ፡ ጋብቻዎች ፡ እንደሌላው ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ ሁሉ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በሁሉ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ የውል ፡ የጋራ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚጻኙ ፡ ናቸው ፤ እንዲሁም ፡ ጋብቻው ፡ የተነገረበት ፡ ሃይማኖት ፡ ላዘዛቸው ፡ ግዴታዎችም ፡ ተጠያቂ ፡ ናቸው ።

<u>ለልማድ ፡ ጋብቻ</u> ፡ የሚሆኑት ፡ ሥርዓቶች ፡ ዕቅድ ፡ አበሮቹ ፡ የሚኖሩበት ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ አንዱ ፡ በሚኖርበት ፡ ነገድ ፡ ደንቦች ፡ የታዘዙት ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ ቢሆን ፡ በሕጉ ፡ የሠፈሩትን ፡ ግዴታዎች ፡ የነገዱ ፡ ልማድ ፡ ቢቀበለው ፡ ባይ

ቀበለውም ፣ ለሁሉ ፣ የጋብቻ ፣ ዓይነቶች ፣ የተደነገጉት ፣ የወል ፣ የጋራ ፣ ግዴታዎች ፣ በሙሉ ፣ እንዲጠበቁ ፣ ይገባል ።

የሕዝብ ፣ የክብር ፣ አቋም ፣ ማስታወሻዎች ፣ (ማለት ፣ የተወለዱትን ፣ የተጋቡትንና ፣ የሞቱትን ፣ መመዝገቢያ ፣) በተቋቋመ ፣ ጊዜ ፣ ጋብቻን ፣ የሚያፈጣጥመው ፣ ሰው ፣ ጋብቻውን ፣ በማስታወሻ ፣ እንዲመዘግበው ፣ ይገደዳል ፣ እንዲሁም ፣ ማስታወሻው ፣ በሕዝብ ፣ የክብር ፣ አቋም ፣ ማስታወሻ ፣ መዝገቦች ፣ ይመዘገባል ። እንግዲህ ፣ ለጋብቻው ፣ ማስረጃ ፣ ምስክር ፣ ሊሆን ፣ የሚችለው ፣ ከእንደዚህ ፣ ያሉት ፣ ማስታወሻ ፣ መዛግብት ፣ የተወጣጣ ፣ ቅጅን ፣ ሲያቀርቡ ፣ ነው ።

፫፤ ለሁሉ ፣ የጋብቻ ፣ ዓይነቶች ፣ ግዴታዎች ፣ ስለማስከበር ፣ የተወሰኑ ፣ ድንጋጌዎች ፣ ወይም ፣ ምጽዋነ ፣ ግዴታዎች ፣ የሆኑ ፣ ሕጎች ፣

የጋብቻዎችን ፣ ግዴታዎች ፣ ከወሰነ ፣ በኋላ ፣ እሊሁ ፣ ግዴታዎች ፣ ባይጠበቁ ፣ የሚያስከትሉትን ፣ ቅጣቶች ፣ የሚወስኑ ፣ ድንጋጌዎችን ፣ ሕጉ ፣ ያግጋል ። እሊህ ፣ ድንጋጌዎችም ፣ የሚመለከቱት—

ሀ. በዕድሜ ፣ የሥጋ ፣ ዝምድናንና ፣ የጋብቻ ፣ ዝምድናን ፣ ባለ ፣ የቀድሞ ፣ ጋብቻ ፣ ውል ፣ መቀየድ ፣ ያለ ፣ እክል ፣ ወይም ፣ በፍርድ ፣ የተወሰነ ፣ ሰው ፣ ለማግባት ፣ አስፈላጊው ፣ ሥልጣን ፣ የሌለው ፣ ባሏ ፣ በሞተባት ፣ የመበለትነት ፣ ጊዜ ፣ ምክንያት ፣ የተነሣ ፣ ዕንቅፋት ፣ እያለ ፣ የተዋዋሉትን ፣ ጋብቻ ፣ ጉዳዮችን ፣ እና ፣

ለ/ በኃይል ፣ አስገዳጅነት ፣ ወይም ፣ በህላዌ ፣ ዝንጋታ ፣ ፈቃደኝነት ፣ ተጓድሎ ፣ ሳለ ፣ የተዋዋሉትን ፣ ጋብቻ ፣ ጉዳዮች ፣ ነው ።

"ሀ"ን ፣ ስለሚመለከቱት ፣ ጉዳዮች ፣ በሕግ ፣ የታገጉት ፣ ድንጋጌዎች ፣ የሚከተሉትን ፣ ይከታል—

(፩፤) ጋብቻውን ፣ የሾመው ፣ የሕዝብ ፣ የክብር ፣ አቋም ፣ መዛግብት ፣ ሹሙ ፣ ወይም ፣ ሌላ ፣ ባለሥልጣን ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕጉ ፣ መሠረት ፣ እንዲቀጣና ፣ ጥምሮቹ ፣ ራሣቸው ፣ ምስክሮቹና ፣ የጋብቻን ፣ በዓል ፣ ለመሾም ፣ ተከፋይ ፣ የሆኑትን ፣ ሌሎች ፣ ሰዎች ፣ እንዲቀጡ ፣ እና ፣

(፪፤) ጋብቻው ፣ እንዲፈርስ ፣ (ዋጋ ፣ አልባ ፣ እንዲሆን ፣) ነው ።

"ለ"ን ፣ ስለሚመለከቱት ፣ ጉዳዮች ፣ ጋብቻው ፣ እንዲፈርስ ፣ (ዋጋ ፣ አልባ ፣ እንዲሆን ፣) ያግጋል ።

<u>በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በቅጣት ፡ ላይ ፡ መውደቅ።</u>

የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዝግብት ፡ ሹሙ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ ለጋብቻው ፡

ሀ/ በዕድሜ ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፯ ፡)

ለ/ በጋብቻ ፡ ወይም ፡ በሥጋ ፡ ዝምድና ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፲ ፡)

ሐ/ ቀድሞ ፡ የነበረበት ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ እስከሁን ፡ በማለቱ ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፲፩ ፡)

መ/ ለማግባት ፡ አስፈላጊውን ፡ ሥልጣን ፡ በጣ ፡ ኢ.አኪ.ል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፲፬ ፡)

ሠ/ ለማግባት ፡ ፈቃደኝነቱ ፡ በኃይል ፡ አስገዳጅነት ፡ የተገኘ ፡ በመሆኑ ፡ ከመኅደሉ ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፲፮ ፡ (፪) ፡) ምክንያት ፡ እንቅፋት ፡ መኖሩን ፡ ሲያውቅ ፡ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ሲገባው ፡ (ማለት ፡ ንቁ ፡ የሕዝብ ፡ አገልጋይ ፡ ሊያደርገው ፡ የሚገባውን ፡ የመጠያየቅ ፡ ተግባር ፡ ካከናወነ ፡ በኋላ ፡) ጋብቻን ፡ አፈጣጥሞ ፡ ቢገኝ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ቅጣት ፡ ያገኘዋል ።

ደግሞም ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ በጋብቻው ፡ ላይ ፡ የቀረበን ፡ መቃወሚያ ፡ ቍጥር ፡ ፮፻፲፱ ፡ ወይም ፡ ባሏ ፡ ሞቶበት ፡ የመበለትነት ፡ ጊዜን ፡ ባለመፈጸሟ ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፳ ፡) እንቅፋት ፡ እያለ ፡ ጋብቻውን ፡ የለፈፈ ፡ ሹሙን ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣኑን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስበታል ። ሹሙ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣኑ ፡ እንዲያውቅ ፡ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይገባው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ስለሚለው ፡ ሁለት ፡ ምሳሌዎች ፡ ሹሙ ፡ ፈልጎ ፡ ቢደርስበት ፡ ባይደርስበት ፡ የሹሙ ፡ ፈንታ ፡ እንጂ ፡ ሕጉ ፡ የሚቸገርበት ፡ ጉዳይ ፡ እንዳላደረገው ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ፡ ምክንያቱም ፡ ስለጋብቻው ፡ ተገቢ ፡ መቃወሚያ ፡ ቀርቦ ፡ ኑሮ ፡ እንደሆነ ፡ እንደዚሁ ፡ ያለው ፡ መቃወሚያ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የታወቀ ፡ በግልጽ ፡ የሚቀርብ ፡ ነው ። ስለባሏ ፡ የሞተባት ፡ የመበለትነት ፡ ጊዜም ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋምን ፡ መመዝገቢያ ፡ ማስታወሻዎችን ፡ የመሰሉ ፡ መዛግብቶች ፡ ከተቋቋሙ ፡ ከማስታወሻዎቹ ፡ ጋራ ፡ የማስተያየትን ፡ ተግባር ፡ የሚመለከት ፡ ነው።

እንዲሁም ፡ ከላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ የጋብቻ ፡ አጋጅ ፡ እንቅፋቶች ፡ ማናቸውም ፡ አንዱ ፡ እያለ ፡ ጋብቻ ፡ ታውጆ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ በአበሮቹ ፡ ራሳቸው ፡ ጋብቻውን ፡ በመረቁ ፡ ሰዎችና ፡ በጋብቻው ፡ ምስክሮች ፡ በነበሩት ፡ ላይ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስባቸዋል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከሚጋቡት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ከሚፈለገው ፡ ዕድሜ ፡ በታች ፡ በሆነበት ፡ ጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ቅጣት ፡ የሚደርስበት ፡ በዚያው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፯ ፡ (፪) ፡) ። ከሚጋቡት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ኢ.አኪ.ል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ያለ ፡ በመሆኑና ፡ አስፈላጊው ፡ የማግቢያ ፡ ሥልጣን ፡ ፈቃድ ፡ በሌለበት ፡ ጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ተቀጭው ፡ ሌላው ፡ የጋብቻው ፡ ወገን ፡ ነው ፡ (ጥር ፡ ፮፻፲፬ ፡ (፪) ።) በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፮፻፲፭ ፡ እና ፡ ፬፻፲፪ ፡ በተከታታዮቹም ፡ በሕግ ፡ የተከለከለን ፡ ጋብቻ ፡ ያወጀ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚቀጣበት ፡ ድንጋጌ ፡ ሲኖር ፡ አበሮቹ ፡ ጋብቻ ፡ ፈቅደው ፡ የመረቁ ፡ ሰዎችና ፡ ምስክሮቹ ፡ የሚቀጡበት ፡ ድንጋጌ ፡

አለመመደቡን ፣ መገንዘብ ፣ ያሻል ። ዋጋ ፣ በሌለው ፣ ጋብቻ ፣ ውል ፣ እንደተያዘ ፣ የመዝ መሪያው ፣ ኅብረት ፣ ከመፍረሱ ፣ ወይም ፣ ውድቅ ፣ ከመሆኑ ፣ በፊት ፣ ሥራዬ ፣ ብሎ ፣ አልሞ ፣ ሌላ ፣ ጋብቻ ፣ የተዋዋለ ፣ አበር ፣ ያለ ፣ ጥርጥር ፣ ጥንድ ፣ ጋብቻ ፣ ስለፈጸመ ፣ ቅጣት ፣ እንዲያገኘው ፣ ተደርጓል ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፲፮ ፣ ወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ።) ደግ ሞም ፣ ለጋብቻው ፣ ፈቃደኝነትን ፣ ለማግኘት ፣ ሌላ ፣ ሰውን ፣ በኃይል ፣ ያስገደደ ፣ ሰው ም ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕጉ ፣ ቍጥር ፣ ፮፻፲፮ ፣ ይቀጣል ። (እንዲሁም ፣ ወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ቍጥር ፣ ፰፻፳፫ ፣ ይመለከቷል ።)

<u>ስለጋብቻው ፣ መፍረስ ፣ ዋጋ ፣ አልጋ ፣ መሆን ፣ የቅጣት ፣ ድንጋጌዎች ፣ (ማዕቀበ ፣) የምጥንታ / (ምጽዋን ፣ ድንጋጌዎች ፣ ማለቱ ፣ በተሻለ)</u>

ጋብቻው ፣ የሚፈርስበትን ፣ (ዋጋ ፣ አልባ ፣ የሚሆንበትን) የሚከተው ፣ ሌላው ፣ ሕግ ፣ ውጤትን ፣ የሚያገኘው ፣ በሚከተሉት ፣ መንገዶች ፣ ነው ።

ሀ/ ከሁሉ ፣ አስቀድሞ ፣ ከዚህ ፣ ግርጌ ፣ ጥያቄን ፣ ሊያቀርቡ ፣ ይገባቸዋል ፣ ተብ ሎ ፣ በተጠቀሱት ፣ ሰዎች ፣ ጥያቄው ፣ ቀርቦለት ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ካላዘዘ ፣ በስተቀር ፣ ጋብቻው ፣ አይፈርስም ። (ጋብቻው ፣ እንዲፈርስ ፣ ለፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ያመለከቷል ፣ እን ጂ ፣ ለቤተ ፣ ዘመድ ፣ ገላጋዮች ፣ አለመሆኑን ፣ ይገነዘቧል ። የቤተ ፣ ዘመድ ፣ የሽምግ ልና ፣ ዳኞች ፣ የሚያዩት ፣ የፍቺን ፣ ጥያቄዎች ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በጋብቻ ፣ ግዴታዎች ፣ መጣስ ፣ በማዕቀብ ፣ ሕግ ፣ ምጥንታ ፣ የሚፈርሰውን ፣ ጋብቻ ፣ አይደለም)።

ለ/ ከተዋዋይ ፣ ወገኖቹ ፣ አንዱ ፣ ከሚፈለገው ፣ ዕድሜ ፣ በታች ፣ ከመሆኑ ፣ የተ ነሣ ፣ ወይም ፣ የሥጋ ፣ ዝምድና ፣ ወይም ፣ የጋብቻ ፣ ዝምድና ፣ መተሳሰሪያ ፣ ከመኖሩ ፣ የተነሣ ፣ ጋብቻው ፣ እንዲፈርስ ፣ በማነኛው ፣ ጉዳዩ ፣ ነው ፣ ባይ ፣ ሰው ፣ ወይም ፣ በዐ ቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ለፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ጥያቄ ፣ ሊቀርብ ፣ ይችላል ። እንዲህ ፣ ያለው ፣ አቤቱታ ፣ በተሰማ ፣ ጊዜም ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ጋብቻው ፣ ይፈርስ ፣ ዘንድ ፣ እንዲፈቅድ ፣ ይገባዋል ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ ፍርሻው በጋብቻው ፣ ጊዜ ፣ ከሚፈለግበት ፣ ዕድሜ ፣ በታች ፣ ኑሮ ፣ አሁን ፣ ከሚፈለገው ፣ ዕድሜ ፣ በደረሰው ፣ መሰይ ፣ ላይ ፣ አይጸናም ። (ቍጥር ፣ ፮፻፱)።

ሐ/ ከጥንድ ፣ ጋብቻ ፣ የተነሣ ፣ ጋብቻው ፣ ፍርስ ፣ እንዲሆን ፣ በጥንዱ ፣ ጋብቻ ፣ ከአበሩት ፣ ውስጥ ፣ አንዱ ፣ ወይም ፣ ዐቃቤ ፣ ሕጉ ፣ ጥያቄ ፣ ለማቅረብ ፣ ይችላል ። ግን ፣ ሁለተኛው ፣ ጋብቻው ፣ በሚነገርበት ፣ ጊዜ ፣ የቀድሞው ፣ ጋብቻው ፣ አበር ፣ በሕይወ ት ፣ መኖሩ ፣ በፍጹም ፣ ካልተረጋገጠ ፣ በቀር ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ጋብቻው ፣ ፍርስ ፣ እንዲ ሆን ፣ አይበይንም ። (ቍጥር ፣ ፮፻፲፪) ። የቀድሞው ፣ ጋብቻው ፣ አበር ፣ እንደሞተ ፣ መታ ወቁ ፣ ሲመሠረት ፣ ዕጥፍ ፣ ድርብ ፣ ጋብቻ ፣ የነበረው ፣ ወዲያውኑ ፣ ባለ ፣ ዋጋ ፣ ይሆ ናል ። እንዲሁም ፣ ከጥንዱ ፣ (ከተደረበበት ፣) ጋብቻ ፣ የተነሣ ፣ ፍርስ ፣ ይሆን ፣ ዘንድ ፣ ጥያቄ ፣ ለማቅረብ ፣ አይቻልም ።

መ/ ያለአክል ፣ ወይም ፣ በፍርድ ፣ የተወሰነ ፣ ሰው ፣ (ዕክቡ) እንዲያገባ ፣ ሥል ጣን ፣ ከማጣቱ ፣ የተነሣ ፣ ጋብቻ ፣ ፍርስ ፣ እንዲሆን ፣ ያለአክሉ ፣ ራሱ ፣ ወይም ፣ ዕክቡ ፣ (በፍርድ ፣ የተወሰነው ፣ ሰው) ራሱ ፣ ወይም ፣ ኢአኪሉ ፣ ጋብቻ ፣ ሊመርቅ ፣ ሊፈቅድ ፣ የሚገባው ፣ ሰው ።

ሁ/ ወይም ፡ የመበለትነት ፡ ዕድሜ ፡ ካለመጠበቁ ፡ ብቻ ፡ የተነሣ ፡ (ቁጥር ፯፻፷(፫)፥ ወይም ፡ ተደርጎ ፡ ለነበረው ፡ መቃወሚያ ፡ ምንም ፡ ግምት ፡ አልተሰጠውም ፡ ከማለት ፡ ብቻ ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻው ፡ ፈራሽ ፡ እንዲሆን ፡ ጥያቄ ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ፤ እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ የዝምድና ፡ መተሳሰሪያ ፡ በእውነቱ ፡ ሳይኖር ፡ በወደፊቱ ፡ ሙሰዮች ፡ መከከል ፡ ዝምድና ፡ አለ ፡ ከማለት ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይሾም ፡ መቃወሚያ ፡ ቀርቦ ፡ ኑሮ ፡ እንደሆነ ፡ እንግዲህ ፡ ለማገጃ ፡ ምክንያቱ ፡ ምንም ፡ ግምት ፡ ሳይሰጠው ፡ በመቅረቱ ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ በቂ ፡ መነሻ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእውነቱ ፡ የዝምድና ፡ መተሳሰሪያ ፡ ካለ ፡ እንግዲያስ ፡ ለመፍረሱ ፡ አይነተኛ ፡ መነሻ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆነው ፡ ይህ ፡ መተሳሰሪያ ፡ ነው ።

ለጋብቻው ፡ በኀይል ፡ አስገዳጅነት ፡ የተተፋ ፡ ወይም ፡ በሕላዊ ፡ መሳሳት ፡ የተገኘ ፡ የደፈረሰ ፡ ፈቃደኝነት ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ እንዲፈርስለት ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ አስገዳጅ ፡ ኃይል ፡ ወይም ፡ መሳሳቱ ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ አቤቱታም ፡ ያስገደደው ፡ ኃይል ፡ ከተቋረጠበት ፡ ወይም ፡ ስሕተቱን ፡ ከተረዳበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ በስድስት ፡ ወሮች ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። በማናቸውም ፡ መንገድ ፡ ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚደረገው ፡ ጥያቄ ፡ ጋብቻው ፡ ከተከበረበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ፤ (ቁጥር ፡ ፮፻፲፯ ፡ እና ፡ ፮፻፲፰) ።

<u>ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የጋብቾች ፡ ዓይነቶች ፡ የሚያገለግሉ ፡ ልዩ ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፤</u>

<u>(«የምጥንታ ፡ ሕጎች ፡/ ድንጋጌዎች ፡» ምባልከፋ ፡)</u>

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የታተቱት ፡ የቅጣት ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለሁሉም ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ የሚሆኑትን ፡ የወል ፡ ግዴታዎች ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ በተለይ ፡ የተመደቡ ፡ ሌሎች ፡ የምጥንታ ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አሉ ። የብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ልዩ ፡ የቅጣት ፡ ሕጐች ፡ የሚመለከቱት ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ የመዛግብት ፡ ሹሙንና ፡ ተጣማሪዎቹንና ፡ ምስክሮቹንም ፡ ነው ፤ በምንም ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆን ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋብቻውን ፡ የሚያፈርስ ፡ ውጤትን ፡ አይወልዱም ። በዚያው ፡ ሥፍራ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ የመኖሩ ፡ ጊዜ ፡ ግዴታ ፡ ሳይከበር ፡ ጋብቻን ፡ ያወጀ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹም ፡ <u>እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ አለመጠበቁን ፡ እያወቀ ፤ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ ሲገባው ፤)</u> በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚቀጣ ፡ ነው ፤ ደግሞም ፡ ተጣማሮቹና ፡ ምስክሮቹ ፡ ቅጣት ፡ ይገባቸዋል ። የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ጋብቻውን ፡ በሚያስከብርበት ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፫ ፡ የተመለከተውን ፡ የማስታወቂያ ፡ ግዳጅ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፬ ፡ እንደ ፡ ተመለከቱ ፡ ሥርዓቶች ፡ አበሮቹና ፡ ምስክሮቹ ፡ ስለሚቀበሉት ፡ መሐላና ፡ የመሳዮቹን ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ለመሆን ፡ መፈለጋቸውን ፡ ማረጋገጫ ፡ መቀበል ፡ ሁሉ ፡ ሳይጠብቅ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ።

በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ ጋብቻ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ማናቸውም ፡ ሥርዓቶች ፡ ሳይጠበቁ ፡ ቀሩ ፡ በማለት ፡ ጋብቻውን ፡ ለመሻርና ፡ ለማፍለስ ፡ መነሾ ፡ ምክን

ያት ፡ አይደለም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣን ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ ሲሽረው ፡ እንደ ፡ ፍቺ ፡ ምክንያት ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፳፫ ፡ (፪ ፡) እና ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፸፩ ።) የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ በነገድ ፡ የልማድ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መሻር ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የሕግ ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኝ ፡ አይደለም ። በሃይማኖትና ፡ በልማድ ፡ ጋብቻዎች ፡ ግዴታዎቹና ፡ ሥነሥርዓቶቹ ፡ ባለመጠበቃቸው ፡ የሚጣለው ፡ መቀጫ ፡ ጋብቻውን ፡ በሾመው ፡ ባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ የዚያ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ነገድ ፡ ወግና ፡ ልማድ ፡ የወሰነውን ፡ የገንዘብ ፡ ቅጣት ፡ ብቻ ፡ መክፈልና ፡ የተበደለው ፡ ወገን ፡ ኪሣራ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ማስቻል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ያን ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ የልማድ ፡ ወግ ፡ ቸላ ፡ በማለት ፡ (በዚያ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ልማድ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተቃራኒ ፡ ልማድ ፡ ቢኖር ፡ ባይኖርም ፡) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱንና ፡ የኪሣራ ፡ ገንዘብ ፡ መጠኑን ፡ ለማውረድ ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ቅጣትና ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ የወጣበት ፡ ወግና ፡ ልማድ ፡ አእምሮ ፡ ሊረዳቸው ፡ የማይችል ፡ ወይም ፡ ለርትዕና ፡ ለበጎ ፡ ምግባር ፡ ጠባይ ፡ (ሞራሊቲ ፡) ተቃራኒ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ልማዱ ፡ ውጤት ፡ እንዳያገኝ ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፳፲ ።)

፲ ፤ የጋብቻ ፡ ውጤቶች ።

ጋብቻ ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤት ፡ መልኮች ፡ ሁለት ፡ ናቸው ፤

ሀ/ በግላዊ ፡ የተለየ ፡ ዝምድናቸው ፤

ለ/ በገንዘባቸው ፡ ነው ።

ጋብቻ ፡ በግላዊ ፡ የተለየ ፡ አቋማቸው ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤቶች ፡ የሚመለከቱት ፡ በአበሮቹ ፡ መካከል ፡ የሚያመጣውን ፡ ግላዊ ፡ ልዩ ፡ ዝምድና ፡ ነው ፤ በገንዘባቸው ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤቶች ፡ የሚመለከቱት ፡ እያንዳንዱ ፡ የግል ፡ የሆኑትንና ፡ የሁለቱ ፡ አበሮች ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ የሆኑትን ፡ ነው ። ጋብቻ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ ብሔራዊ ፡ ሃይማኖትና ፡ ልማድ ፡ ጋብቻ ፡ ብሎ ፡ ሳይለይ ፡ በሁሉም ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ ያው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፳፰ ።) የሩካቤ ፡ ሥጋው ፡ ተግባር ፡ ቢፈጸም ፡ ባይፈጸምም ፡ ጋብቻው ፡ ውል ፡ እንደገቡ ፡ ወዲያውኑ ፡ ውጤቶቹን ፡ ያስከትላል ።

የ ጋ ብ ቻ ፡ ው ል ።

ጋብቻው ፡ ከመሾሙ ፡ በፊት ፡ እጮኞቹ ፡ ጋብቻቸው ፡ በሀብትና ፡ ንብረታቸው ፡ በኩል ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ የሚያስተዳድር ፡ ውል ፡ ሊፈጽሙ ፡ ይችላሉ ፡ ደግሞም ፡ በነዚያ ፡ ሕጉ ፡ ባልከላከላቸው ፡ ማናቸው ፡ ይዞታዎች ፡ ላይ ፡ ጋብቻቸው ፡ በመካከላቸው ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ልዩ ፡ የግል ፡ ግንኙነት ፡ ስለሚመለከቱት ፡ የመተዳደሪያ ፡ ስምምነቶችን ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ሊያሰፍሩ ፡ ይችላሉ ። የጋብቻ ፡ ውሉ ፡ በወደፊት ፡ አበሮቹ ፡ የተፈረመ ፡ ጽሑፍ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፤ አራት ፡ ምስክሮችም ፡ (ሁለት ፡ በባልዮው ፤

በኩል ፡ ሁለት ፡ በሚስቲት ፡ በኩል ፤) እንዲገኙ ፡ ያስፈልጋል ፤ እሊህን ፡ የውል ፡ ቅጦ ች ፡ ከጣሰ ፡ የጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡ የለውም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻ ፳፱ ፡) ከሚዳሩት ፡ አንዱ ፡ ኢ.አኪ.ል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ሰው ፡ (ዕክብ ፡) ሲ. ሆን ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፳፰ ፡ የተመለከቱ ፡ የሚከተሉት ፡ ተፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ይጠበቃሉ ፤

ሀ) ኢ.አኪ.ልን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ከራሱ ፡ ከኢ.አኪ.ሉ ፡ ፈቃደኝነት ፡ በላይ የሞግዚቱ ፡ ምረቃ ፡ (ፈቃድ ፡) አስፈላጊ ፡ ነው ፤

ለ) በፍርድ ፡ የታገደ ፡ ሰውን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ የጋብቻ ፡ ውሉ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የጸደቀ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

የጋብቻ ፡ ውልን ፡ ነክ ፡ በሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ በፍርድ ፡ የታገደን ፡ ሰው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ እንዳይፈጽም ፡ የማያስችለው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ከላይ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፳፱ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሥርዓቶች ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ሳይፈጽም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ውል ፡ ራሱ ፡ ሊያከናውን ፡ ይችላል ።

በቍጥር ፡ ፮፻፴ ፡ መሠረት ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ከተሰናዳ ፡ በኋላ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ወይም ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ካለው ፡ ሰው ፡ (ኖታሪ ፡) ዘንድ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ይገባል ፡ እንዲሁም ፡ ከአበሮቹ ፡ ማንኛውም ፡ መሰይ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፈቀደለት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከውሉ ፡ ለማድረስና ፡ አገላብጦ ፡ ለመመርመር፡ ይቻለዋል ። ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ የሚስማማ ፡ ሰው ፡ ጋብቻው ፡ በሀ ብታቸውና ፡ ንብረታቸው ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ አበሮቹ ፡ የተስማሙ ትን ፡ መረዳቱ ፡ አውራ ፡ ጉዳዩ ፡ ነው ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ ላንዳንድ ፡ ፍርድ ፡ ነክ ፡ ድርጊ ቶች ፡ የጥንዱ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ መስማማት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ ይኋል ።

የጋብቻ ፡ ውል ፡ ከተዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ እንዲ ሻሻል ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ጥቅም ፡ የሚጠይቅ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ አበሮቹ ፡ በጠየቁት ፡ መ ሠረት ፡ በቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ (የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡) አማካይነት ፡ ማናቸውም፡ ልውውጥ ፡ ሊከናወን ፡ ይቻላል ፤እንግዲህ ፡ የመዠመሪያውን ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ የሚመ ረምር ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተከናወነውን ፡ መሻሻል ፡ ይገነዘበው ፡ ዘንድ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸመው ፡ ማናቸው ፡ ልውውጥ ፡ ትክክለኛ ፡ ቅጂ ፡ በፍር ድ ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ወይም ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ይ ቀመጣል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፴፪ ።) ከጋብቻው ፡ በፊት ፡ ምንም ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ስላላሰናዱ ና ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ በጋብቻ ፡ ዘመናቸው ፡ ውስጥ ፡ ውል ፡ ሊገቡ ፡ ቢሹ ፡ በቤተ ፡ ዘመ ዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካልተፈቀደ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ አንዳችም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ውጤትን ፡ አያገኝም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፴፫ ።) ከጋብቻው ፡ በፊት ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የጋብቻው ፡ ውል ፡ ባልተደረገበት ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ ጋብቻ ው ፡ በግላዊ ፡ የተለየ ፡ ዝምድናና ፡ በሀብት — ንብረት ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶች ፡ በሕጉ ፡ በተወሰኑት ፡ አንቀጾች ፡ መሠረት ፡ ይዳኛሉ ። የጋብቻ ፡ ውል ፡ የአበሮቹን ፡ የተ ለየ ፡ ግላዊ ፡ ግንኙቶችንና ፡ የሀብቶቻቸው ፡ ጉዳዮች ፡ እንዴት ፡ እንደሚተዳደሩ ፡ ከለ ል ፡ አድርጐ ፡ መደርደር ፡ ይገባዋል ፤ እንዲያው ፡ በቀላሉ ፡ ሁሉንም ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ወ ግና ፡ ልማድ ፡ በመወርወር ፡ ፍላጐቶቻቸው ፡ ሊብራሩ ፡ አይችሉም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፴፭።) በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ የስምምነቶቹ ፡ ስልቶች ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጠቅላላ ፡ መልክ ፡ ተመር ተው ፡ እንደሆነ ፡ በሁለቱም ፡ በልዩው ፡ ግላዊ ፡ ዝምድናና ፡ በሀብታቸው ፡ ረገድ ፡ ጋብ

ቻው፡ የሚያስከትላቸው፡ ውጤቶች፡ በሕጉ፡ በሰፈሩት፡ ድንጋጌ፡ አንቀጾች፡ ይዳ ኛሉ ። የጋብቻ፡ ውል፡ በተጋቢዎቹ፡ መካከል፡ የሚዘጋጅ፡ ውል፡ ስለሆነ፡ ሦስተኛ፡ ወገኖችን፡ ነክ፡ የሆነ፡ የውለታ፡ አንቀጾች፡ ሊይዝ፡ አይችልም ። እንዲሁም፡ የጋብ ቻ፡ ውል፡ በሕጉ፡ መሠረት፡ አዛዥ፡ የሆኑትን፡ ድንጋጌዎች፡ (ለምሳሌ፡ የአበሮቹ፡ እርስ፡ በራሳቸው፡ መከባበርን፡ መደጋገፍንና፡ መረዳዳትን፡ (ቊጥር፡ ፮፻፴፮፡) እና፡ የአብሮ፡ መኖር፡ ግዳጅን፡ (ቊጥር፡ ፮፻፴፰፡) ጉዳዮች፡) ተቃራኒ፡ በሆነ፡ መልክ፡ ለማከናወን፡ አይችልም ።

<u>የጋብቻ፡ ልዩና፡ ግላዊ፡ ውጤቶች ።</u>

ሕጉ፡ በሚፈቅድላቸው፡ ጉዳዮች፡ ላይ፡ አበሮቹ፡ በሌላ፡ መልክ፡ ካልተስማሙ፡ በቀር፡ የጋብቻ፡ ልዩና፡ ግላዊ፡ ውጤቶቹ፡ የሚከተሉት፡ ናቸው፡

ሀ/ ባልየው፡ የቤተ፡ ዘመዱ፡ ጌታ፡ (ራስ፡ አውራ) ነውና፡ ባሏ፡ በሚያዛት፡ ሕግን፡ በዘሉ፡ ጉዳዮች፡ ሁሉ፡ ሚስቲቱ፡ ለርሱ፡ የመታዘዝ፡ ዕዳ፡ አለባት፡ ሕጉ፡ አንዳንድ፡ መብቶችን፡ ለሚስቲቱ፡ ስለሚያዝዝላት፡ (ለምሳሌ፡ በቊጥር፡ ፮፻፵፱፡ የግል፡ ሀብቶቻቸውን፡ እያንዳንዱ፡ አበር፡ እንዲያስተዳድርና፡ እንዲሸጥ፡ እንዲለ ውጥ፡ ወይም፡ በፈቀደው፡ መልክ፡ ከእጁ፡ ወደ፡ ሌላ፡ ሰው፡ እጅ፡ እንዲያዘዋውረ ው፡ በሚፈቅድለት፡ በመሳሰሉት፡ ላይ) በሚስቲቱ፡ እንደዚሁ፡ ያለ፡ አንዳችም፡ የመ ታዘዝ፡ ዕዳ፡ የማያመጡበት፡ ነገሮች፡ አሉ፡ (ቊጥር፡ ፮፻፴፭) ። በባልየው፡ መሪነት፡ በትክክለኛው፡ ዘለዓለማዊ፡ (መንፈሳዊ) በሆነ፡ ግብርና፡ በሚጨበጠው፡ ምድራዊ፡ ተግባሮች፡ በኩል፡ ለመላው፡ ቤተሰቦቻቸው፡ እድገት፡ ሲሉና፡ ልጆቻቸውን፡ በሚ ገባ፡ እኳኋን፡ ለማሳደግ፡ ሁለቱም፡ አበሮች፡ ለመረዳዳት፡ የተሳሰሩ፡ ናቸው ። እንደ ዚሁም፡ ይህን፡ ጉዳይ፡ ነክ፡ በሆኑት፡ በጋብቻ፡ ውሉ፡ አበሮቹ፡ የተዋዋሏቸውን፡ ማናቸውን፡ ግዴታዎች፡ ለመፈጸም፡ የተሳሰሩ፡ ናቸው፡ (ቊጥር፡ ፮፻፴፯) ፤

ለ/ ተመሳዮቹ፡ ርስ፡ በራሳቸው፡ መከባበር፡ መደጋገፍና፡ መረዳዳት፡ አለባቸው፡

ሐ/ በሕመም፡ ምክንያት፡ ወይም፡ ከሌላ፡ ምክንያት፡ የተነሣ፡ ችሎታን፡ በማ ጣት፡ ወይም፡ ከቤት፡ በመለየት፡ ወይም፡ ከቤተሰብ፡ በመከብለል፡ ወይም፡ ከዚሁ፡ ተመሳሳይ፡ በሆኑ፡ ሁኔታዎች፡ ምክንያት፡ በቊጥር፡ ፮፻፴፯፡ እንደተመለከተው፡ ከአ በሮቹ፡ አንዱ፡ ቤተ፡ ዘመዱን፡ ነክ፡ የሆኑትን፡ ግዴታዎች፡ ለማከሄድ፡ የተሳነው፡ እንደሆነ፡ ግዴታዎቹን፡ የመፈጸሙ፡ ተግባር፡ በሌላው፡ አበር፡ ላይ፡ ይወድቅበ ታል፡ (ቊጥር፡ ፮፻፴፰፡ ቊጥር፡ ፩፻፭፡ እንዲሁ፡ ይመለከቷል ፤

መ/ ከአበሮቹ፡ አንዱ፡ ከበፊት፡ ጋብቻ፡ ልጆች፡ ቢኖሩት፡ የእንደዚህ ያሉ ት፡ ልጆችን፡ ማስተማር፡ ነክ፡ በሆነው፡ ጉዳይ፡ መብቱ፡ በተለይ፡ የዚያው፡ የወላ ጁ፡ ነው፡ (ቊጥር፡ ፮፻፴፱) ፤

ሠ/ አበሮቹ፡ አንድ፡ ላይ፡ ለመኖር፡ የተሳሰሩ፡ ናቸው፡ አድራጎቱ፡ ለጤንነት፡ በውል፡ (በጣም) ጠንቅን፡ የሚያስከትል፡ ካልሆነ፡ በቀር፡ የጋብቻ፡ መተሳሰር፡ የተ ለመደን፡ ሩካቤ፡ ሥጋን፡ ተግባር፡ ያጠቃልላል፡ (ቊጥር፡ ፮፻፵) ፤

ረ/ ባልዮው ፡ የጋራ ፡ መኖሪያ ፡ ሥፍራን ፡ መርጦ ፡ ይመድባል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባል የው ፡ የመደበው ፡ የጋራ ፡ መኖሪያ ፡ ቦታ ፡ እንዳሻው ፡ በመሆኑ ፡ ከጋብቻው ፡ ውል ፡ አንቀጾች ፡ ጋራ ፡ ተቃራኒ ፡ ሁኖ ፡ ቢገኝ ፡ ሚስቲቱ ፡ ውሳኔውን ፡ በመቃወም ፡ አቤቱታ ዋን ፡ ለቤተዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ልታሰማ ፡ ትችላለች ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፵፩) ፤

ሰ/ ምንም ፡ እንኳ ፡ አብሮ ፡ የመኖሮ ፡ ግዴታ ፡ (ይህንንም ፡ በሚቃወም ፡ መልክ ፡ አበሮቹ ፡ በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ከቶ ፡ ሊስማሙ ፡ አይችሉም ፡) ቢኖር ፡ ቅሉ ፡ በጋብቻቸው ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ አበሮቹ ፡ ልኩ ፡ ለተቆረጠ ፡ ወይም ፡ ላልተቆረጠ ፡ ጊዜ ፡ ተለያይተው ፡ ለመኖር ፡ ሊስማሙ ፡ ይችላሉ ፤ በዚህም ፡ ገጽ ፡ የተፈጸመውን ፡ ስምምነት ፡ ማፍረሱ ፡ በዘፈቀደ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ከጣምሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ማንኛው ፡ በማናቸው ፡ ጊዜ ፡ ተለያ ይቶ ፡ የመኖሩን ፡ ስምምነት ፡ ሊሽረው ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ከሃይማኖት ፡ እምነታቸው ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻውን ፡ በፍቺ ፡ ለማፍረስ ፡ የተሳናቸው ፡ ሁለት ፡ መሳዮች ፡ ጋብቻው ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ « በገበታና ፡ በምኝታ › በመለያየት ፡ ሊስማሙ ፡ ይችላሉ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ፍርዳዊ ፡ መለያየትን ፡ አያስተነትንም ፤ ግን ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ በስምምነት ፡ መለያየትን ፡ እንዲያገኙ ፡ ያስችላቸዋል ፤

ቀ/ አበሮቹ ፡ ርስ ፡ በራሳቸው ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ታማኝ ፡ ሁኖ ፡ መገኘት ፡ አለባ ቸው ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፵፫) ፤

በ/ ባልየው ፡ ለሚስቱ ፡ ጋሻ ፡ ከለላ ፡ ሁኖ ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ፤ ለቤተሰቡ ፡ እድ ገት ፡ ብቻ ፡ እስከሆነ ፡ ድረስ ፡ በግል ፡ ሀብቷና ፡ በጠቅላላ ፡ የጠባይ ፡ ግብሯ ፡ ባልየው ፡ ሚስቲቱን ፡ ሊመራትና ፡ ሊመክራት ፡ ይችላል ፤ በምንም ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ይህንን ፡ መብቱን ፡ በግል ፡ ያለአገባብ ፡ ወይም ፡ በሚያበሳጫት ፡ መልክ ፡ ሊጠቀምበት ፡ አይች ልም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፵፬) ፤

ተ/ እያንዳንዱ ፡ አበር ፡ በመረጠው ፡ ሞያና ፡ ተግባር ፡ ሊሰማራ ፡ ይችላል ፡ ሌላ ው ፡ አበር ፡ በዚያ ፡ ሥራና ፡ ተግባር ፡ መዋሉን ፡ ሊቃወም ፡ የሚችለው ፡ የተባለው ፡ ሟያ ፡ ለትዳራቸው ፡ ጥቅም ፡ ተቃራኒ ፡ ሁኖ ፡ ሲገኝ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፵፭) ፤ የተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መሰማራት ፡ በንግድ ፡ ሕጉ ፡ ከቍ ፡ ፲፮—፳፩ ፡ በተመ ለከተው ፡ ይዳኛል ፤

ቸ/ ለቤታቸው ፡ አገልጋዮችን ፡ ገረድና ፡ አሽከር ፡ ለመቅጠር ፡ የባልየው ፡ አቅ ም ፡ ባልፈቀደለት ፡ ጊዜ ፡ የቤትን ፡ አያያዝ ፡ ተግባር ፡ ግዴታዎችን ፡ ሚስቲቱ ፡ ማከና ወን ፡ አለባት ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፵፮) ።

በአበሮቹ ፡ በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ውስጥ ፡ በሚከተሉት ፡ አንቀጾች ፡ የተዘረዘሩትን ፡ የጋብቻ ፡ ውጤቶቹን ፡ የሚሽር ፡ ስምምነት ፡ ሊገቡ ፡ አይችሉም ፤

(፩) ቍ ፡ ፮፻፴፮ — ስለመከባበር ፡ መደጋገፍና ፡ መረዳዳት ፤

(፪) ቍ ፡ ፮፻፴፯—አንዱ ፡ አበር ፡ ሲደናቀፍ ፡ ስለቤተሰቡ ፡ የማስተዳደር ፡ ግዴታዎች ፡ አመራር ፤

(፫) ቍ ፡ ፮፻፴፱ — ከቀድሞ ፡ ጋብቻው ፡ ስላፈራቸው ፡ ልጆች ፡ የተለየ ፡ መብቱ ፤

(፬) ቍጥር ፡ ፮፻፵ — ስለ ፡ አብሮ ፡ መኖር ፤

(፫) ቊጥር ፣ ፮፻፶፫ ስለታማኝነት ፣ (ምንም ፣ እንኳ ፣ አበሮቹ ፣ ከዚህ ፣ ግዴታ ፣ ወደውጭ ፣ ለማፈንገጥ ፣ እንደማይችሉ ፣ በዚህ ፣ አንቀጽ ፣ ላይ ፣ በነጠረ ፣ መልክ ፣ ጐልቶ ፣ ባይጠቀስ ፣ በጋብቻ ፣ ውሉ ፣ ለዚህ ፣ ተቃራኒ ፣ በሆነ ፣ መልክ ፣ የተስማሙት ፣ ምንም ፣ ዐይነት ፣ ዋጋ ፣ ያለው ፣ ውጤት ፣ የማይሰጥ ፣ መሆኑን ፣ ማመን ፣ ይገባል) ።

<u>ጋብቻ ፣ በገንዘብ ፣ ሀብት ፣ ላይ ፣ የሚያስከትለው ፣ ውጤቶች ።</u>

ጋብቻ ፣ በገንዘብ ፣ ላይ ፣ ስለሚያስከትለው ፣ ውጤቶቹ ፣ ሲታይ ፣ አበሮቹ ፣ በተጋቡ ፣ ጊዜ ፣ በነበራቸው ፣ ሀብትና ፣ ከጋብቻው ፣ በኋላ ፣ እያንዳንዳቸው ፣ ባፈሯቸው ፣ ሀብት ፣ መካከል ፣ መለየት ፣ ያስፈልጋል ። በቊጥር ፣ ፮፻፵፫ ፣ መሠረት ፣ መሰዮቹ ፣ ያላቸው ፣ ሀብት ፣ ሁሉ ፣ በምሉ ፣ የጋራ ፣ ማለት ፣ ለሁለቱም ፣ አበሮች ፣ የአንድ ፣ ላይ ፣ የሆነ ፣ ሀብት ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ ይገመገማል ፤ ይሁን ፣ እንጂ ፣ ከጣምሮቹ ፣ አንዱ ፣ የግል ፣ ሀብቱ ፣ ይኸም ፣ ማለት ፣ የዚያ ፣ ሀብት ፣ ነጠላ ፣ የተለየ ፣ ባለቤት ፣ መሆኑን ፣ ለማረጋገጥ ፣ የሚችለው ፣ ይህን ፣ ሐሳብ ፣ ሊያፈርሰው ፣ ይችላል ። ከሦስተኛ ፣ ወገኖች ፣ ጋራ ፣ በሚያገናኝ ፣ ነገር ፣ ሦስተኛው ፣ ወገን ፣ ስለዚህ ፣ ቋሚ ፣ ጉዳይ ፣ አውቆ ፣ ወይም ፣ ሊያውቅ ፣ ዘንድ ፣ በተገባው ፣ ነበረ ፣ የሚባል ፣ ካልሆነ ፣ በቀር ፣ የስምምነቱ ፣ ማረፊያ ፣ የሆነው ፣ ሀብት ፣ የግል ፣ ሀብት ፣ እንጂ ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ አለመሆኑ ፣ መረጋገጡ ፣ እንደዚያ ፣ ያሉትን ፣ ሦስተኛ ፣ ወገኖች ፣ የሚነካ ፣ አይደለም ። ለምሳሌ ፣ ሁለት ፣ አበሮች ፣ ጋብቻው ፣ በገንዘባቸው ፣ ላይ ፣ ስለሚያስከትለው ፣ ውጤቶች ፣ አስተዳደር ፣ ወስነው ፣ የጋብቻ ፣ ውል ፣ ገቡና ፣ እንደዚህ ፣ የመሰለውን ፣ የጋብቻ ፣ ውልም ፣ ከቊጥር ፣ ፮፻፴ ፣ ድንጋጌዎች ፣ ጋራ ፣ በሚስማማ ፣ መልክ ፣ ከፍርድ ፣ ቤት ፣ ቤተ ፣ መዛግብት ፣ አስቀመጡ ፣ ተብሎ ፣ ይመላል ። እንግዲህ ፣ በማናቸውም ፣ አንዱ ፣ ሀብት ፣ ላይ ፣ በጋብቻ ፣ ውሉ ፣ ከለል ፣ ብሎ ፣ እንደተመለከተው ፣ እንደዚያ ፣ ያለው ፣ ሀብት ፣ በእርግጡ ፣ የሚስቲቱ ፣ ግል ፣ ሀብት ፣ ሳለ ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ ከባልየው ፣ ጋራ ፣ ቢስማማበት ፣ ሦስተኛው ፣ ወገን ፣ በፍርድ ፣ ቤት ፣ ቤተ ፣ መዛግብት ፣ የተቀመጠውን ፣ የጋብቻ ፣ ውሉን ፣ ቅጅ ፣ በመከታተል ፣ የግል ፣ ሀብት ፣ መሆኑን ፣ ለማረጋገጥ ፣ ሲችል ፣ በቸልተኝነቱ ፣ ወዶ ፣ የገባበት ፣ ጣጣ ፣ ስለሆነ ፣ ሚስቲቱ ፣ እንዲህ ፣ ያለው ፣ ሀብት ፣ የራሴ ፣ የግል ፣ ሀብት ፣ ነው ፣ በማለት ፣ መልሰ ፣ ለመጠየቅ ፣ ወይም ፣ ለመውሰድ ፣ መብት ፣ አላት ።

ጋብቻው ፣ ከአበሮቹ ፣ አንዱ ፣ በሞት ፣ በመለየቱ ፣ ምክንያት ፣ በፍቺ ፣ ወይም ፣ በፍርስ ፣ ምክንያት ፣ እስከተፈጸመ ፣ ድረስና ፣ ሀብቱ ፣ በአበሮቹ ፣ መካከል ፣ ወይም ፣ ሁኔታው ፣ እንደሚያመለክተው ፣ ከመሰዮቹ ፣ በንዱ ፣ ወራሾች ፣ በሌላው ፣ መሰይ ፣ መካከል ፣ እስከሚተነተን ፣ ድረስ ፤ የጋራ ፣ ሀብቱ ፣ ባለቤትነት ፣ የማይከፋፈል ፣ የማይሰነጠቅ ፣ የየአንዳንዳቸው ፣ እኩል ፣ ዕጣ ፣ ያለበት ፣ የሁለቱ ፣ አበሮች ፣ ያንድ ፣ ላይ ፣ ሀብት ፣ እንደሆነ ፣ ይቀራል ። ከአበሮቹ ፣ አንዱ ፣ በሞት ፣ በተለየ ፣ ጊዜ ፣ ሌላው ፣ አበር ፣ ከጋራ ፣ ሀብቱ ፣ የሚካፈለው ፣ ድርሻ ፣ (ዕጣ) <u>በወራሽነት ፣</u> ሳይሆን ፣ የጋራው ፣ ሀብት ፣ ተጋሪ ፣ ባለቤትነቱ ፣ የተነሣ ፣ መሆኑን ፣ ደጋግሞና ፣ ለይቶ ፣ መግለጽ ፣ ያሻል ። ከቊጥር ፣ ፮፻፴፫ ፣ በሚስማማ ፣ መልክ ፣ በጋብቻው ፣ ወቅት ፣ በተስማሙበት ፣ ውል ፣ መሠረት ፣ አበሮቹ ፣ ያንድ ፣ ላይ ፣ ሀብቱን ፣ የጋራ ፣ ባለቤትነት ፣ ሊሽሩት ፣ ይችላሉ ። እንዲሁም ፣ በቊጥር ፣ ፮፻፷ ፣ እንደተመለከተው ፣ አንዳንድ ፣ ዕዳዎች ፣ ማለት ፣ ለአበሮቹ ፣ የትዳር ፣ ጣጣ ፣ ሲባል ፣ የገቡበት ፣ ዕዳዎች ፣ የጋራ ፣ ሀብትን ፣ የሚመለከት ፣ ዕዳ ፣ መሆኑን ፣ መግለጽ ፣ ያስፈልጋል ፤ ስለዚህ ፣ የጋራ ፣ ሀብቱ ፣ በአበሮቹ ፣ መካከል ፣ በሚተነተንበት ፣ ጊዜ ፣ እነዚህ ፣ ዕዳዎች ፣ የጋራ ፣ ንብረቱ ፣ ከሚያወጣው ፣ ዋና ፣ ገንዘብ ፣

ሒሳብ ፡ እንዲነሡ ፡ ይገባል ። ለምሳሌ ፡ የጋብቻ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ባልየው ፡ በየወሩ ፡ የሚያፈራው ፡ ደመወዝ ፡ (በየወሩ ፡ የኢ/ብር ፡ ፮፻ ፡ ይበል) ብቻ ፡ ቢሆንና ፡ ጋብቻው ፡ የቆየው ፡ ለአምስት ፡ ዓመት ፡ እድሜ ፡ (ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ የኢ/ብር ፡ ፴፮ሺ ፡ አድርጎ ፡ ማለት ፡ ነው) ቢሆንና ፡ ለትዳር ፡ ጣጣ ፡ (ለምሳሌ ፡ ለምግብ ፡ ለልብስ ፡ ለልጆች ፡ መማሪያ) በየወሩ ፡ የኢ/ብር ፡ ፭፻ ፡ ይበል ፡ ወጭ ፡ ቢደረግ ፡ ሊተነተን ፡ (ሊከፋፈል) የሚገባው ፡ ያንድ-ላይ ፡ ሀብት ፡ ከኢ/ ብር ፡ ፴፮ሺ ፡ ላይ ፡ የኢ/ብር ፡ ፴ሺ ፡ ተነስቶለት ፡ የኢ/ብር ፡ <u>፮ሺ ፡</u> ነው ፡ እንጂ ፡ የኢ/ብር ፡ <u>፴፮ሺ</u> ፡ አይደለም ።

በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ በተቃራኒ ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ ካልተዋዋሉ ፡ በቀር ፡ <u>የግል ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡</u> የሚከተሉትን ፡ የከተተ ፡ ነው ፤

ሀ/ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ አበር ፡ የነበረውን ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፤

ለ/ በጋብቻው ፡ ውስጥ ፡ እያንዳንዱ ፡ አበር ፡ በውርስ ፡ ወይም ፡ በስጦታ ፡ የተቀበለውን ፡ ሀብት ፤

ሐ/ በጋብቻው ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ የግል ፡ ገንዘቡ ፡ በሆነው ፡ ያገኘው ፡ ሀብትን ፡ ወይም ፡ ከአበሮቹ ፡ ያንዱ ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ (ሀብት ፡)የሆነውን ፡ ባለቤትነት ፡ እጅ ፡ ከማዛወር ፡ በተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ያገኘው ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ የዚያው ፡ ከአበሮቹ ፡ ያንዱ ፡ የግል ፡ ሁብት ፡ የሆነውን ፡ በማለዋወጥ ፡ (ልውጫ ፡) የተገኘ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ነው ፤ ይህም ፡ የገባው ፡ በጋብቻው ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ ስለሆነ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ የዚያው ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ ለመሆኑ ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ እንዲያረጋግጡ ፡ ያስፈልጋል ፡ (ይህም ፡ ማረጋገጫ ፡ የሚደረገው ፡ ባለ ፡ ጥቅሙ ፡ አበር ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡) (ቁጥር ፡ ፮፻፵፯ ፡ እና ፡ ፮፻፶፪ ፡ (፪)) ።

በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ በተቃራኒ ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ ካልተስማሙ ፡ በቀር ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ የሚከተሉትን ፡ ያጠቃልላል ፤

ሀ/ የአበሮቹን ፡ ደሞዞችና ፡ ያፈሯቸውን ፡ ገንዘብን ፡ (ጥቅሞችን ፤) እና ፡

ለ/ እያንዳንዱ ፡ አበር ፡ ሊኖረው ፡ ከሚችለው ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ የሚያመጣው ፡ ገቢን፤ ይኸም ፡ ከአበሮቹ ፡ ያንዱ ፡ የግል ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ከሆነው ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ መሬት ፡ ክራዮች ፡ የሚገኘው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እና ፡

ሐ/ ለሁለቱም ፡ አበሮች ፡ በደፈናው ፡ (አንድ ፡ ላይ ፡) በስጦታ ፡ ወይም ፡ በውርስ ፡ የተሰጠውን ፡ ነው ።

የግል ፡ ሀብት ፡ አስተዳደር ፡ ተግባር ፡ ለባለ ፡ ሀብቱ ፡ አበር ፡ ታትቷል ፡ ባለቤቱም ፡ መሳይ ፡ ይህን ፡ ሀብቱን ፡ (እንዳፈቀደው ፡ ሊሸጠው ፡ ሊለውጠው ፡ ሊያዘዋውረው ፡ ወይም ፡ ሊሰጠው ፡ ማለት ፡ ነው ፡) እንዳሻው ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ፡ (ቁጥር ፡ ፮፻፵፱ ።) ከመሳዮቹ ፡ አንዱ ፡ ያንደኛውን ፡ (የሌላውን ፡) አበር ፡ የግል ፡ ሀብትንና ፡ ንብረትን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲያስተዳድርለት ፡ ባልና ፡ ሚስቱን ፡ በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ከመስማማት ፡ የሚያግዳቸው ፡ ምንም ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ የለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ መልክ ፡ ካልተዋዋሉ ፡ በቀር ፡ ያስተዳደር ፡ የዓመት ፡ ሁኔታ ፡

መግለጫ ፣ ባለቤት ፣ ለሆነው ፣ አበር ፣ እንዲሰጥ ፣ ይገባል ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፶፱)። እንደዚሁም ፣ ከአበሮቹ ፣ አንዱ ፣ በግል ፣ ንብረቱ ፣ ላይ ፣ ሌላውን ፣ እሱን ፣ መሰል ፣ እንደራሴው ፣ ሆኖ ፣ እንዲሠራ ፣ ሊወክለው ፣ ይችላል ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፶፮ ።)

የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረትን ፣ ስለማስተዳደር ፣ ጉዳዮች ፤

ሀ / በደሞዞች ፣ ከግል ፣ ሀብት ፣ ከሚገኙት ፣ ጥቅሞችና ፣ ገቢ ፤ እና ፣

ለ/ ከላይ ፣ ከተመለከቱት ፣ ነገሮች ፣ የተለየ ፣ ሌላ ፣ በሆነው ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ መካ ከል ፣ መለየት ፣ ይገባል ።

በመሠረቱ ፣ የጋራ ፣ ሀብቱን ፣ የሚያስተዳድር ፣ ባልዮው ፣ ቢሆን ፣ ቅሉ ፣ ሚስቲቱ ፣ የምታፈራውን ፣ ጥቅሞች ፣ ደሞዞችና ፣ ሚስቲቱ ፣ ከግል ፣ ሀብት ፣ ንብረቷ ፣ በምታገኘው ፣ ገቢ ፣ ላይ ፣ ማስተዳደሩ ፣ መብቷ ፣ ስለሆነ ፣ የእንደዚህ ፣ ያለውን ፣ ሀብት ፣ ባልየው ፣ አያስተዳድርም ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፶፮ ።) ደግሞ ፣ በቁጥር ፣ ፮፻፴፰ ፣ ከተዘረዘሩት ፣ ምክንያቶች ፣ የተነሣ ፣ ባልየው ፣ ለማስተዳደር ፣ ሲሳነው ፣ የጋራ ፣ ሀብት–ንብረትን ፣ በምሉ ፣ ሚስቲቱ ፣ እንድታስተዳድር ፣ ባለመብት ፣ ነች ። ከዚህም ፣ በላይ ፣ ለቤተ ፣ ዘመዱ ፣ ጥቅም ፣ ሲሆን ፤ ለምሳሌ ፣ ለትዳራቸው ፣ እድገት ፣ በሆነ ፣ መልክ ፣ ባልየው ፣ ሀብት–ንብረቱን ፣ ለመመልከት ፣ እንዳልቻለ ፣ ሲረጋገጥ ፣ ወይም ፣ ባልየው ፣ ለትዳሩ ፣ (ለቤተ—ሰቡ ፣ ያለበትን ፣ ግዴታዎች ፣ ቸላ ፣ በማለት ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረቱን ፣ ሲሰት—ነው ፣) ሚስቲቱ ፣ የጋራ ፣ ሀብት—ንብረትን ፣ እንድታስተዳድር ፣ የቤተ ፣ ዘመዱ ፣ ገላጋዮች ፣ ሊፈቅዱላት ፣ ይችላሉ ፤ የቤተ ፣ ዘመዱ ፣ ገላጋዮች ፣ እንደዚህ ፣ ሊወስኑ ፣ የሚችሉት ፣ ሚስቲቱ ፣ በጠየቀች ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፶፯ ፣ (፫) ።)

እያንዳንዱ ፣ አበር ፣ ጥቅሞቹንና ፣ ደሞዙን ፣ ለመቀበል ፣ እና ፣ ለዚሁ ፣ ጉዳይ ፣ ሲባልና ፣ ደግሞ ፣ ከግል ፣ ሀብት ፣ ንብረቱ ፣ ለሚገባው ፣ ገቢ ፣ መኖሪያ ፣ ይሆነው ፣ ዘንድ ፣ የተለየ ፣ የባንክ ፣ ሂሣብ ፣ ለመክፈት ፣ የመቻል ፣ ባለ ፣ መብት ፣ ነው ፤ ይሁን ፣ እንጂ ፣ ይህ ፣ ሲሆን ፣ ሌላው ፣ አበር ፣ ስለ ፣ ጥቅሞቹ ፣ ሁሉ ፣ ስለደሞዞቹና ፣ ስለ ፣ ተቀበለው ፣ ገቢ ፣ ሁኔታ ፣ ሲጠይቅ ፣ እንዲሰጠው ፣ ግዴታው ፣ ነው ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፶፬ ።) ለቤተሰብ ፣ ጥቅም ፣ ሲባል ፣ አንዱ ፣ መሰል ፣ ሲጠይቅ ፣ የዚያኛውን ፣ አበር ፣ ደሞዞችና ፣ ከግል–ሀብት ፣ ንብረት ፣ ገቢን ፣ እንዲቀበልለት ፣ (አንዴም ፣ ለዚሁ ፣ ደረሰኝ ፣ እንዲሰጥለት ፣) የቤተ–ዘመዱ ፣ ገላጋዮች ፣ ለሌላው ፣ መሳይ ፣ ሊፈቅዱ ፣ ይችላሉ ፣ እንዲሁም ፣ ደግሞ ፣ ጥቅሞቹን ፣ ደሞዙንና ፣ ገቢውን ፣ በምሉ ፣ ወይም ፣ በከፊል ፣ በሰው ፣ ሰው ፣ እጅ ፣ እንዲያዙ ፣ (እንዲከበሩለት ፣) ለመፍቀድ ፣ ይችላሉ ። ይኸም ፣ ለምሳሌ ፣ ባለደሞዙን ፣ እንደተቀበለ ፣ ወዲያውኑ ፣ ገንዘቡን ፣ በመጠጥ ፣ ላይ ፣ ቢከሰክስ ፣ ደሞዙን ፣ በሚከፍለው ፣ ሰው ፣ በሰጡ ፣ እጆች ፣ እንዲያዝ ፣ (እንዲከበር ፣) ያዝዙ ፣ ዘንድ ፣ ሚስቲቱ ፣ የቤተ–ዘመድ ፣ ገላጋዮቹን ፣ ልትጠይቅ ፣ ትችላለች ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፶፭ ።)

ምንም ፣ እንኳ ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረትን ፣ ባልየው ፣ ቢያስተዳድር ፣ ቅሉ ፣ እንዲህ ፣ ያለው ፣ ያስተዳደር ፣ ተግባሩ ፣ እንዳሻው ፣ ከጅ ፣ ለማስወጣትና ፣ ለማስተላለፍ ፣ ለመሸጥ ፣ ለመለወጥ ፣ የሚያስችለው ፣ ባለ ፣ መብትነት ፣ አይደለም ፣ (የጋራ ፣ ሀብትን ፣ ሚስቲቱ ፣ እንድታስተዳድር ፣ አደራው ፣ በተጣለባት ፣ ጊዜም ፣ እንደዚሁ ፣ ነው ፣ አይፈቀድላትም ።) የጋራ ፣ ሀብት–ንብረትን ፣ ነክ ፣ በሆኑ ፣ ጉዳዮች ፣ በሚነጋገሩበት ፣ ጊዜ ፣ የሁለቱ ፣ አበሮች ፣ መስማማትን ፣ የሚያስፈልግበት ፣ አንዳንድ ፣ ነገሮች ፣ አሉ ፤ እሊህም ፤

ሀ/ የማይንቀሳቀስ ፡ የጋራ–ንብረትን ፡ ስም ፡ በለቤት–ነት ፡ ማዛወር ፤

ለ/ ዋጋው ፡ ከኢ.ት/ $ 500 በላይ ፡ የሆነውን ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ የጋራ ፡ ሀብትን ፡ ስም ፡ ለሌላው ፡ ማዛወርና ፡ በሁለቱ ፡ አበሮች ፡ ስም ፡ የተመዘገቡትን ፡ (ሴኩሪቲስ ፡) መያዣ/ ማገቻ ፡ ሰነዶች ፡ (ያበዳሪነት ፡ ማስረጃ ፡ የጥቅም ፡ ዕጣ ፡ እሊህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሁሉ ፡) ባለቤት–ነት ፡ ለማስተላለፍ ፤

ሐ/ ከኢ.ት/ $ 100 ለሚልቅ ፡ ብድር ፡ ውል ፡ መግባት ፤ እና ፡

መ/ በዋጋው ፡ ከኢ.ት/ $ 100 ለሚልቅ ፡ ቢጤ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ስጦታ ፡ ማበርከት ወይም ፡ ከኢ.ት /$ 100 በላይ ፡ ለሚበደር ፡ ሰው ፡ ዋስ ፡ ሆኖ ፡ መቆም ፡ ናቸው።

በዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ ተግባሮች ፡ ለማከናወን ፡ ስለሚያስፈልገው ፡ የአበሮቹ ፡ መስማማት ፡ ልዩ ፡ ያፈጻጸም ፡ ሥርዓቶች ፡ እንዲኖረው ፡ ሕጉ ፡ አያስገድድም ፤ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ስምምነት ፡ በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ሲገባና ፡ የቃል ፡ (ይህም ፡ ያስኬዳል/ ይመስላል ፡) ሊሆን ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ አንዱ ፡ አበር ፡ ከሌላው ፡ አበሩ ፡ ጋራ ፡ ሳይግባባ ፡ ከላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ ተግባሮች ፡ ማናቸውንም ፡ አንዱን ፡ ቢያደርግ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ቅጣትን ፡ እንደሚያስከትልበት ፡ ሕጉ ፡ ለይቶ ፡ በጉልሕ ፡ አያብራራም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለቅጣቱ ፡ ፍርድ ፡ ነክ ፡ ድርጊቱ ፡ በመጠኑ ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ውጤት ፡ አልባና ፡ ባዶ ፡ ተብሎ ፡ ይገመገም ፡ ዘንድ ፡ ሐሳብ ፡ ቀርቧል ፡ ይኸም ፡ ማለት ፡ በጉዳዩ ፡ ያልተስማማው ፡ አበር ፡ ወራሾች ፡ ውጤት ፡ አልባነቱን ፡ መዳኛ ፡ ምክንያታቸው ፡ አድርገው ፡ ለመከራከር ፡ ይችላሉ ፡ ነው ። ዋጋ ፡ አልባነቱ ፡ የፍርድ ፡ ነክ ፡ የሆነውን ፡ ድርጊት ፡ የፈጸመውን ፡ አበር ፡ (ራሱን ፡) ሊያድነው ፡ አይችልም ፡ እና ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አበር ፡ በግል ፡ ሀብቱ ፡ በኩል ፡ የዚያኛው ፡ የፍርድ ፡ ነኩን ፡ ተግባር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ለመፈጸም ፡ የተነጋገረው ፡ ሰው ፡ ተጠያቂ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቀራል ።

ከአበሮቹ ፡ ከአንዱ ፡ ላይ ፡ የሚጠየቁት ፡ እዳዎች ፡ ከዚያው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረትና ፡ ከጋራ ፡ ሀብት–ንብረት ፡ ላይ ፡ ተቀንሶ ፡ ሊመለስ ፡ ይቻላል ፡ እንጂ ፡ ከሌላው ፡ (ባለ ፡ እዳ ፡ ካልሆነው ፡) የግል ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ አይደለም ፡ (ቍጥር ፡ ፲፻፶፱ ።) ይህ ፡ አንቀጽ ፡ እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ በአንዱ ፡ አበር ፡ የሚከፈሉ ፡ እዳዎችን ፡ ያወሳና ፡ የየእዳዎቹን ፡ ዓይነት ፡ አይለይም ፤ ስለዚህ ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ከጋብቻው ፡ በፊት ፡ ለገባባቸው ፡ እዳዎችና ፡ ደግሞ ፡ ውርስ ፡ ሲቀበል ፡ (አብሮ ፡) የወረሳቸውን ፡ እዳዎች ፡ ከንደኛው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት–ንብረቱና ፡ የጋራ ፡ ሀብት–ንብረቱ ፡ ላይ ፡ ተቀናሽ ፡ የሚሆኑ ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ።

ለትዳር ፡ ጣጣ ፡ ሲባል ፡ የተገቡባቸው ፡ እዳዎች ፡ (እሊህም ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፳ ፡ ላይ ፡ ተዘርዝረዋል ፡) የሁለቱም ፡ አበሮች ፡ ያንድ ፡ ላይና ፡ የያንዳንዳቸው ፡ (በነጠላ ፡) እዳዎች ፡ ናቸውና ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከሁለቱም ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረቱና ፡ ደግሞ ፡ ከጋራ ፡ ሀብት–ንብረቱ ፡ ላይ ፡ ተነስቶ ፡ ሊወጧቸው ፡ ይቻላል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፶፱ ።) አበሮቹ ፡ ከአቅማቸው ፡ ጋራ ፡ ተመጣጣኝ ፡ የሆነ ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ወጭ ፡ መዋጮ ፡ እንዲመድቡ ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፳፩ ።) ለትዳሩ ፡ ጣጣ ፡ ሲባል ፡ የሚገቡባቸው ፡ እዳዎች ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ መሆናቸው ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፳ ፡ ተመልክተዋል ፡ እሊሁም ፤

ሀ/ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ መኖሪያ ፡ (የኑሮ ፡ ጣጣ ፡) ምግብ ፡ ማደሪያ ፡ ልብስና ፡ የልጆች ፡ ትምህርት ፡ መማሪያ ፤

ለ/ ባንዱ ፡ አበር ፡ ወይም ፡ በሁለቱም ፡ አበሮች ፡ የሚከፈል ፡ ኑሮን ፡ ለመጠበቅ ፡ ምግብ ፡ ለመስጠት ፡ ያለን ፡ ግዴታ ፡ ለመምላት ፡ የገቡባቸው ፡ እዳዎች ፤ እና

ሐ/ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ እንደሊህ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ የሚወስኗቸው ፡ ሌሎች ፡ እዳዎች ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ገላጋዮቹ ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ አበዳሪው ፡ ሲጠይቅ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

፫ ፤ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡

የመፍረሱ ፡ መነሾ ፡ ምክንያቶች ፡

የጋብቻ ፡ ወራት ፡ ዘመን ፡ የሚደመደምበት ፡ በሦስት ፡ መንገዶች ፡ ነው ፤

ሀ/ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ በሞት ፡ ሲለይ ፤

ለ/ ከጋብቻው ፡ አውራ ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱ ፡ በመጣሱ ፡ ምክንያት ፡ በምጥንታ ፡ (ቅጣት) ድንጋጌዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ሲያዝ ፤ እና ፡

ሐ/ በፍቺ ፡ ነው ።

ሕጉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ አያደርግም ፤ ጋብቻዎች ፡ ሁሉ ፡ የሃይማኖት ፡ ሆነ ፡ የብሔራዊ ፡ ወይም ፡ የልማድ ፡ የጋብቻ ፡ ወራት ፡ ከተባሉት ፡ ሦስት ፡ መንገዶች ፡ ውስጥ ፡ ባንዱ ፡ ከፍጻሜ ፡ ዘመኑ ፡ ይደርሳል ።

ጋብቻ ፡ በፍቺ የሚደመደምባቸው ፡ ጠባይና ፡ ሁኔታዎች ፡ ለሁሉ ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ አብነት ፡ ይሆናሉ ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ቊጥር ፡ ፮፻፷፬ ፡ እንደመደበው ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ በቃኸኝ ፡ (ወይም ፡ በቃሽኝ) አልፈልግም ፡ የማለት ፡ አለመፈለግን ፡ ፍቺ ፡ አይቆጥረውም ፤ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ በመስማማት ፡ በአበሮቹ ፡ የጋራ ፡ ፈቃድ ፡ የሚደረገው ፡ ፍቺ ፡ በቊጥር ፡ ፮፻፷፮ ፡ የተከለከለ ፡ ነው ። ፍቺ ፡ ሊፈቀድ ፡ የሚቻለው ፡ በሕግ ፡ በተመሠረቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ነው ፤ እሊህም ፡ መነሻ ፡ ምክንያቶች ፡ (ሀ) ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ እና ፡ (ለ) ሌላ ፡ ምክንያቶች ፡ ተብለው ፡ በሁለት ፡ ክፍል ፡ ተመድበዋል ። ለፍቺ ፡ ጥያቄ ፡ የሚቀርበው ፡ ለቤተዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አይደለም ፡ (ቊጥር ፡ ፮፻፷፯) ፤ ይኸም ፡ በቊጥር ፡ ፮፻፷፰ ፡ የተወሰኑት ፡ ሰዎች ፡ ማለት ፡ ነው ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ለተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ በጐደለ ፡ መምልያ ፡ ዘርፍ ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የሥልጣን ፡ ዘርፍ ፡ የሚሆነውም ፡ ፍቺ ፡ ተነግሮ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ እንዳልሆነ ፡ ሊወስን ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነው ፡ በሚለው ፡ አስተያየት ፡ (ቊጥር ፡ ፮፻፷፱) ። ይህም ፡ ማለት ፡ ሕጉ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ገላጋዮች ፡ ፍቺ ፡ መናገራቸውን ፡ (መለፈፋቸውን) ሊያረጋግጥ ፡ የሚችል ፡ የመጨረሻው ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ (ከዚህ ፡ ግርጌ ፡ በተሰጡት ፡ ሁኔታዎች ፡ ካልሆን ፡ በቀር) ነገሩ ፡ በመዠመሪያ ፡ ለቤተዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ቀርቦ ፡ የነበረ ፡ ካልሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለፍቺ ፡ የቀረበን ፡ ማመልከቻ ፡ ጥያቄ ፡ ለማየት ፡ ችሎታ ፡ የለውም ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመፋታት ፡ ሲባል ፡ የቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ በሥርዓት ፡ መልክ ፡ ሊቀበልና ፡

ሊያውቀው ፡ የሚችለው ፡ ገላጋዮቹ ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ (ቍጥር ፡ ፲፻፷፰ ፡ እና ፡ ፲፻፸፰) ወይም ፡ ለአእምሮ ፡ ግምት ፡ ያጠግባል ፡ ተብሎ ፡ በሚገመገም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ (ቍጥር ፡ ፲፻፵፲) ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ በቃታቸው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡፡

ለመፋታት ፡ ሲባል ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ገላጋዮቹ ፡ የሚቀርበው ፡ ልመና ፡ (ጥያቄ) የሚደረገው ፡ ከአበሮቹ ፡ በንዱ ፡ ወይም ፡ በአበሮቹ ፡ በሁለቱም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ እንጂ ፡ በማንም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ እንዲሁም ፡ ከውሳኔ ፡ ከመደረሱ ፡ በፊት ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ የፍቺው ፡ ነገር ፡ እርምጃ ፡ ከፍጻሜ ፡ ከመድረሱም ፡ በላይ ፡ በሟቹ ፡ አበር ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ባለጥቅም ፡ ነን ፡ በዮች ፡ ሰዎች፡ ነገሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ለመቀስቀስ ፡ አይቻልም ፡ (ቍጥር ፡ ፲፻፷፯) ፡፡ ፍቺን ፡ ለመፍቀድ ፡ የሚያስችሉት ፡ ሁኔታዎችና ፡ ፍቺው ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ የተንጠለጠሉት ፡ ፍቺውን ፡ የለመነው ፡ አበሬ ፡ ጓደኛው ፡ ያጠፋው ፡ ጥፋት ፡ ለማፋታት ፡ ከባድ ፡ መነ ሾ ፡ ምክንያት ፡ ለመሆኑ ፡ ለማስረዳት ፡ በመቻሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ (ቍጥር፡፲፻፷፯)፤ ቍጥር፡ ፲፻፺–፲፻፺፫ ፡ በሌላ ፡ ከባድ ፡ ባልሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ እንዲፋታ ፡ በተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ የገንዘብ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ፍቺው ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ ያትታል ፡፡ የፍቺው ፡ ልመና ፡ ያለጥርጥር ፡ በታወቁ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ የቤ ተሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ልመናው ፡ ከቀረበላቸው ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔአቸውን ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ፤ (ማሳሰቢያ፤ ቍጥር ፡ ፲፻፷፰ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ትርጉም ፡ የውሳኔውን ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ወራት ፡ ይለዋል ፡፡ በፈረንሣይኛው ፡ የሕጉ ፡ ዋና ፡ ቅጂ ፡ ጽሑፍ ፡ ይኸው ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ወራት ፡ ተብሎ ፡ ተገልጿል)፡፡

የፍቺ ፡ መነሾ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ ሁለት ፡ አይነቶች ፤

ሀ/ አጥፊነቱ ፡ በአበሩ ፡ ላይ ፡ የሚጣል ፡ ሲሆን ፡ እና ፡

ለ/ ከአበሩ ፡ የፈቃድ ፡ ኃይል ፡ (አቅም) የተለዩት ፡ ምክንያቶች ፡ ናቸው ፡፡ ለመ ዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ የተመደቡት ፤

(፩) ዝሙት ፡

(፪) ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ አድራሻው ፡ በማይታወቅበት ፡ መልክ ፡ አበሩ ፡ ከጋ ብቻ ፡ ሰፈሩ ፡ ከቤቱ ፡ ኮብልሎ ፡ ሲጠፋ ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፲፻፷፱) ፡፡

ለሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የተመደቡት ፤

(፩) እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ አእምሮው ፡ ተናውጾበት ፡ በእ ብዶች ፡ ሠፈር ፡ (መምሕፃን ፡ ሲዘጋበት፤)

(፪) በአድራሻው ፡ መታጣቱ ፡ በፍርድ ፡ ሲረጋገጥ ፡ (ቍጥር ፡ ፲፻፸ ፤)እና ፡

(፫) የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣን ፡ መሻሩን ፡ ሲያስታውቅ (ቍጥር ፡ ፲፻፸፩ ፡፡) ናቸው ፡፡

በሃይማኖት ፡ ሥርዓት ፡ የተከናወነን ፡ ጋብቻ ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣን ፡ መሻር ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፤ የፍቺ ፡ መነሻ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑ ፡ የሚቀረው ፡ አ በሮቹ ፡ ጋብቻው ፡ እንደተሻረ ፡ እያወቁ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ መኖራቸውን ፡ ሲቀጥሉ ፡ ነው፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከባድ ፡ እንዳይደለ ፡ የፍቺ ፡ ምክንያት ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ፡፡

ኃላፊነቱ ፡ በአበሩ ፡ ላይ ፡ ስለሚወድቁበት ፡ የፍቺ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶችን ፡ ለሚ መለከተው ፡ ጉዳይ ። እነዚህ ፡ የፍቺ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ ከመሆናቸው ፡ የሚገላግል ፡ ያላጠፋው ፡ አበር ፡ ኃጥኡን ፡ በጠፋው ፡ ጥፋት ፡ ይቅር ፡ ብሎ ፡ ሲያልፈው ፡ ነው ። የኃ ጢአተኛው ፡ ምግባር ፡ ከቋረጠ ፡ በኋላ ፡ እስኪ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ለመፋታት ፡ አ ቤቱታ ፡ ካልቀረበም ፡ ያው ፡ ይቅርታ ፡ መደምደሚያ ፡ ይሆናል ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፸፱ ።)

ከባድ ፡ ባልሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፡ ለመፋታት ፡ በሚቀርብ ፡ ጥያቄ ፡ በአበሮቹ ፡ መካከል ፡ እርቅና ፡ ስምምነት ፡ እንዲወርድ ፡ መጣሩ ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ግዴታ ፡ ነው ፡ ከዚሁ ፡ ዓላማቸው ፡ ለመድረስ ፡ ሲሉም ፡ ለማስታረቅና ፡ ለማስማማት ፡ ይበጃል ፡ የሚሉዋቸውን ፡ አስተያየቶችን ፡ ሁሉ ፡ ሊወስኑ ፡ ይችላሉ ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፹ ።) ለማስ ታረቅ ፡ ያቃታቸው ፡ እንደሆነም ፡ በፍቺው ፡ ቅጥና ፡ ሁኔታዎችን ፡ (ማለት ፡ ፍቺው ፡ በገንዘባቸው ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ ስለ ፡ ኑሮ ፡ አጠባበቅ ፡ መተዳደሪያ ፡ እና ፡ ስለ ፡ ሕፃናት ፡ ሞግዚትነት ፡ መብት ፡ ነክ ፡ በሆኑት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡) አበሮቹ ፡ እንዲስማሙ ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ አበሮቹን ፡ ለማግባበት ፡ እንዲጥሩ ፡ ያስፈል ጋል ። አበሮቹም ፡ ከንዲህ ፡ ያለው ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ አበሮቹ ፡ ከተስማሙ በት ፡ ግዴታዎችና ፡ አኳኋን ፡ ጋራ ፡ በሚግባቡ ፡ መልክ ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ይበ ይናሉ ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፹፩) ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ብይኑ ፡ የሚጸድቀው ፡ በቁጥር ፡ ፩፻ ፹፪ ፡ መሠረት ፡ ፍቺው ፡ መነገሩን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲያረጋግጥ ፡ ነው ። አበሮቹ ፡ በይታ ረቁ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ፍቺው ፡ ግዴታዎች ፡ ከስምምነት ፡ ላይ ፡ ሳይደርሱ ፡ ቢቀሩ ፡ ለመ ፋታት ፡ ጥያቄው ፡ ከደረሰበት ፡ ዕለት ፡ ገምሮ ፡ ባለው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የፍቺ ፡ ውሳኔ ፡ ያደርጋሉ ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ የአንድ ፡ ዓመ ት ፡ ጊዜ ፡ በአበሮቹ ፡ ስምምነት ፡ ወደ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ሊራዘም ፡ ይችላል ። ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ አበሮቹ ፡ ከመጋባታቸው ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ መልክ ፡ ሊስማሙበት ፡ ይችላሉ ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፹፫)።

ከባድ ፡ ከሆኑ ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ ካልሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፡ ለቤተ—ሰቡ ፡ የሽ ምግልና ፡ ዳኞች ፡ የፍቺ ፡ ጥያቄ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ቁርጥ ፡ ውሳኔአቸውን ፡ እስከሚሰጡ ፡ ድረስ ፡ የቤተ—ዘመድ ፡ ገላጋዮች ፡ አበሮቹንና ፡ ልጆቹን ፡ (ሕፃናቱን ፡) ለመደገፍ ፡ አስ ፈላጊ ፡ ሊሆኑ ፡ ስለሚችሉት ፡ ነገሮች ፡ ቋሚ ፡ ያልሆኑ ፡ የጊዜው ፡ ትእዛዞችን ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ ። ይኸም ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ አበሮቹና ፡ ስለልጆቹ ፡ መተዳደሪያ ፡ አበል ፡ ስለ ፡ አበ ሮቹ ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ አስተዳደር ፡ ስለ ፡ አበሮቹ ፡ መኖሪያ ፡ ሥፍራ ፡ የጊዜው ፡ የሆኑ ፡ ትእዛዞችን ፡ ሊወስኑ ፡ ይችላሉ ፡ ነው ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፹፬)። እሊህን ፡ ማናቸውንም ፡ የጊ ዜው ፡ ትእዛዞች ፡ ሊያስረዱት ፡ ለሚቻል ፡ በጎ ፡ ተግባር ፡ ሲባል ፡ በማናቸውም ፡ ምክ ንያት ፡ እንደገና ፡ ክልሶ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ወይም ፡ ለመሰረዝ ፡ ይቻላል ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፹፭)።

የቤተ—ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ የመጨረሻውን ፡ ውሳኔአቸውን በሚያደርጉበት ፡ ጊዜ ፡ ፍቺውን ፡ የሚናገር/ የሚያጐላ ፡ ብይንን ፡ ይሰጣሉ ። ደግሞም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ብይን ፡ ውስጥ ፡ ከቁጥር ፡ ፩፻፹፮—፩፻፹፰ ፡ ድረስ ፡ ከተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ ጋራ ፡ በሚ ዋደድ ፡ መልክ ፡ ከጋብቻው ፡ የተወለዱት ፡ ሕፃናት ፡ በማንኛው ፡ እጅ ፡ እንደሚጠበቁ ፡ (በማን ፡ ሞግዚትነት ፡ እንደሚኖሩ ፡) እና ፡ ስለ ፡ አበሮቹ ፡ የግልና ፡ የጋራ ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ሂሳብ ፡ ማጣራት ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ትእዛዞችን ፡ እንዲሰጡ ፡ ያስ ፈልጋል ። ከፍቺው ፡ መግለጫ ፡ ውስጥ ፡ በመጀመሪያው ፡ ብይን ፡ ያልተብራራ ፡ አከራ ካሪ ፡ ነገር ፡ ቢነሣ ፡ የቤተ—ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ እሊሁኑ ፡ ከፍቺው ፡ በኋላ ፡ የተቀሰቀሱትን ፡ ጉዳዮች ፡ (የሚያስተኛ ፡) የሚያስተካክል ፡ ተጨማሪ ፡ ብይንን ፡ ሊሰ

ጡ ፡ ይችላሉ ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ በጎደል ፡ መላ ፡ ዘርፍ ፡ (ተጨማሪ ፡) ብይን ፡ የመዠመሪያው ፡ ብይን ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ከስድስት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ፡ (ቊጥር ፡ ፩፻፺) ። ስለ ፡ ልጆቹ ፡ (አቃቢነት ፡) መጠበቅ ፡ (ማለት ፡ ከአባትየው ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ከናቲቱ ፡ ዘንድ ፡ ሁነው ፡ ይጠበቁ ፡ ብሎ ፡ ስለመወሰኑ) እና ፡ ስለ ፡ አያያዛቸው ፡ አስተዳደር ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ማናቸውን ፡ ትእዛዞች ፡ በሚሰጡበት ፡ ላይ ፡ አውራ ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ሊታይ ፡ የሚገባው ፡ የሕፃናቱ ፡ ጥቅም ፡ ነው ። የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ በምድራዊው ፡ እና ፡ በትክክለኛው ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ (ሞራል)፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ የልጆቹን ፡ ምቾት ፡ ብቻ ፡ በመመልከት ፡ እንዲወስኑ ፡ ያስፈልጋል። ሕፃናት ፡ በናቲቱ ፡ ባለ ፡ አደራነት ፡ እንዳይቀመጡ ፡ የሚከላ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ የአምስት ፡ ዓመትና ፡ በዕድሜያቸው ፡ ከዚያ ፡ በታች ፡ የሆኑት ፡ የለጋ ፡ (ጮርቃ፡) ዕድሜ ሕፃናት ፡ አደራ ፡ ጠባቂነት ፡ በናቲቱ ፡ ላይ ፡ እንዲጣል ፡ ያስፈልጋል ። ልጆችን ፡ ስለሚመከት ፡ በማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ለልጆቹ ፡ መልካም ፡ እድገት ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ በማናቸውም ፡ ሰዓት ፡ እንደገና ፡ ተመርምሮ ፡ ሊለዋወጥና ፡ ሊስተካከል ፡ ይገባል ። ይኸም ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ በናቲቱ ፡ ባለአደራ ፡ ጠባቂነት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ እናቲቱ ፡ ከበጎውና ፡ ከትክክለኛው ፡ ቀን ፡ ምግባር ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ አኑዋኗር ፡ ብትይዝ ፡ ትእዛዙ ፡ እንደገና ፡ ታይቶ ፡ አባትየው ፡ የልጆችን ፡ አቃቢነት ፡ ተግባር ፡ በሚገባ ፡ ለማከናወን ፡ የበቃ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ የጠባቂነት ፡ ባለአደራ ፡ ሞግዚትነቱ ፡ ለርሱ ፡ ይሰጣል ። ልጆችን ፡ ነክ ፡ ስለሆነው ፡ ትእዛዝ ፡ እንደገና ፡ ታይቶ ፡ እንዲለወጥ ፡ ጥያቄን ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ የሚያቀርብ ፡ የልጆቹ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ አውራጅ ፡ ዘመድ ፡ ነው ፡ (ቊጥር ፡ ፩፻፺፩ ፡ እና ፡ ፩፻፺፪።)

ጋብቻ ፡ሲፈርስ ፡ በአበሮቹ ፡ መካከል ፡ ያለን ፡ የገንዘብ ፡ ሀብት ፡ ግንኙነት ፡ ማጣራት ።

በአበሮቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ ሀብት ፡ ግንኙነት ፡ የማጣራቱ ፡ ተግባር ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ መንገዶች ፡ በማናቸውም ፡ አንድ ፡ የመፍረሻ ፡ መንገድ ፡ ጋብቻ ፡ ሲፈርስ ፡ የሚያስከትለው ፡ አውራ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ እንደጋብቻው ፡ አፈራረስ ፡ መንገድ ፡ (ማለት ፡ በሞት ፡ በፍቺ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱ ፡ በመጣሱ ፡ በምጥንታ ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ መፍረስ) ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ አለው ። በክር ክር ፡ ላይ ፡ የተንጠለጠለው ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነት ፡ ብሔራዊ ፡ ወይም ፡ የሃይማኖት ፡ ወይም ፡ የልማድ ፡ ቢሆን ፡ የሀብት ፡ ግንኙነትን ፡ የማጣራት ፡ ተግባርን ፡ የሚዳኙት ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፡ ከጋብቻው ፡ መንገዶች ፡ የተለዩ ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይለዋወጡ ፡ ለሁሉም ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ ያው ፡ የሆኑ ፡ ናቸው ።

ሀ/ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ በሞት ፡ በመለየቱ ፡ ምክንያት ፡ ጋብቻው ፡ ስለፈረሰ ፡ የሚያመጣው ፡ የማጣራት ፡ ተግባር ፤

አበሮቹ ፡ የግልና ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረቱን ፡ አከፋፈል ፡ መልክና ፡ ቅጥ ፡ የሚዳኝ ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ገብተው ፡ እንደሆነ ፡ የሀብት ፡ ግንኙነት ፡ ማጣራቱ ፡ ተግባር ፡ ከውሉ ፡ ጋራ ፡ በሚዋደድ ፡ መልክ ፡ ይከናወናል ። በባልና ሚስቱ ፡ መካከል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ውል ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ የማጣራቱ ፡ ተግባር ፡ በሕግ ፡ ከተወሰኑት ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፡ ጋራ ፡ በሚስማማ ፡ መልክ ፡ ይፈጸማል ፡ (ቊጥር ፡ ፩፻፺፫) ።

የመዠመሪያው ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ እያንዳንድ ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረቱ ፡ ሁኖ ፡ የተመደበውን ፡ ይዞ ፡ እንዲሄድ ፡ የሚያስችል ፡ ነው ፡ (ቁጥር ፡ ፲፻፹፬) ። ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ ባለቤትነት ፡ መብቱ ፡ እጅ ፡ ስም ፡ ተዛውሮበትና ፡ መዘዋወሩ ፡ ያስገኘውም ፡ ሀብት ፡ ከጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረቱ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ መቀላቀሉን ፡ ሊያስረዳ ፡ ከቻለ ፤ እንኪያስ ፡ ይኸው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ ባለቤትነት ፡ እጅ ፡ ሲዛወር ፡ ያስገኘው ፡ ዋጋ ፡ ልክን ፡ የሚያህል ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ነገሮች ፡ መልክ ፡ ከጋራው ፡ ሀብት ፡ ቀንሶ ፡ ሊወስድ ፡ መብት ፡ አለው ። ሁለቱም ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ዕቃዎች ፡ ቀንሶ ፡ የመውሰድ ፡ መብት ፡ ያሏቸው ፡ እንደ ሆነ ፡ እንግዲያስ ፡ ሚስቲቱ ፡ (ወይም ፡ ወራሾቿ ፡ እንደአጋጣሚውና ፡ እንደ ሁኔታው) ድርሻዋን ፡ በቀዳሚነት ፡ ቀንሳ ፡ ለመውሰድ ፡ ዕድል ፡ አላት ፡ ቁጥር ፡ ፲፻፹፭)። ይህም ፡ የቀዳሚነት ፡ ዕድል ፡ ለሚስቲቱ ፡ የተሰጣት ፡ እንደደንቡ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረትን ፡ የሚያስተዳድረው ፡ አበር ፡ ባልየው ፡ ስለ ሆነ ፡ ነው ።

አንዱ ፡ አበር ፡ በሠራው ፡ ድርጊት ፡ ምክንያት ፡ የሌላው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብትን ፡ ወይም ፡ የጋራ ፡ ሀብታቸውን ፡ በጎዳ ፡ ጊዜ ፡ ተበዳዩ ፡ አበር ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ የሚኖረው ፤

ሀ/ ድርጊቱን ፡ የፈጸመው ፡ አበር ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ድርጊት ፡ ለመፈጸም ፡ ምንም ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤ ወይም ፡

ለ/ የተፈጸመው ፡ ድርጊት ፡ የብልሹ ፡ መጥፎ ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ፍሬ ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ አበር ፡ መብቶች ፡ በማጭበርበርና ፡ በማታለል ፡ የተፈጸመ ፡ ድርጊት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ለ "ሀ" የሚሆነው ፡ ምሳሌ ፡ በቁጥር ፡ ፲፻፺፰ ፡ የተመለከቱትን ፡ የሁለቱም ፡ አበሮች ፡ ስምምነት ፡ በሚያስፈልግባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ፍርድ ፡ ነክ ፡ ድርጊቶች ፡ ያለሚስቲቱ ፡ ስምምነት ፡ ባልየው ፡ ፈጽሞት ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ለእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ድርጊቶች ፡ ኪሣራዎችን ፡ የሚወስነው ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ አዛዥ ፡ ድንጋጌ ፡ ስለሆነ ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ ለማምለጥ ፡ አበሮቹ ፡ ስምምነት ፡ ለመግባት ፡ አይችሉም ። ደግሞም ፡ የማጣራቱ ፡ ተግባር ፡ ቢከናወንና ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ለመከናወኑ ፡ ደረሰኝ ፤ ቢሰጥም ፡ ቅሉ ፡ ድንጋጌው ፡ ቆራጭ ፡ አዛዥ ፡ ድንጋጌ ፡ ስለሆነ ፡ ምንጊዜም ፡ ውጤት ፡ አለው ፡ (ቁጥር ፡ ፲፻፹፯) ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚቻልበት ፡ አበሩ ፡ በሞት ፡ ከተለየበት ፡ ዕለት ፡ ዠምሮ ፡ ወደኋላ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ከማይልቅ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የተፈጸሙ ፡ ድርጊቶችን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ (ቁጥር ፡ ፲፻፹፰) ። እንዲሁም ፡ የሌላው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ የዚህኛውን ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረትን ፡ ወይም ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረቱን ፡ ረግጦ ፡ በመጉዳት ፡ የጸጋው ፡ (የሀብቱ ፡) ዋጋ ፡ መጠን ፡ መትረፍረፉን ፡ (መዳበሩን) ሊያስረዳ ፡ የሚችለው ፡ አበር ፡ ካሣ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ፡ (ቁጥር ፡ ፲፻፹፱) ። እንዲሁም ፡ ባል ፡ በተለየ የግሉ ፡ ቤት ፡ የሆነውን ፡ ለመጠገን ፡ (ለማሻሻል) የሚስቲቱ ፡ የተለየ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ከሆነው ፡ ቢበደርና ፡ እዳውን ፡ መልሶ ፡ ለመክፈል ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ ቢሞት ፡ ሚስቲቱ ፡ ኪሣራ ፡ ለመቀበል ፡ ባለ መብት ፡ ነች ።

ለጋራ ፣ ሀብቱን ፣ የሚመለከቱ ፣ ጉዳዎች ፣ (ለምሳሌ ፣ ለትዳር ፣ ጥቅም ፣ ሲባል ፣ የገቡባቸው ፣ ዕዳዎች) ሁሉ ፣ ከተቀነሱበት ፣ በኋላ ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረቱ ፣ ከሞት ፣ በተረፈው ፣ አበርና ፣ በሚቴ ፣ አበር ፣ ወራሾች ፣ መካከል ፣ እኩል ፣ ይተነተናል ። አበሮቹ ፣ በጋብቻ ፣ ውሉ ፣ ወይም ፣ በማናቸው ፣ ሌላ ፣ ስምምነት ፣ ላይ ፣ ሀብት ፣ ንብረት ፣ እኩል ፣ በእኩል ፣ ሳይሆን ፣ (በተለያዩ) ክፍና ፣ ገቅ ፣ በሚሉ ፣ ድርሻዎች ፣ ይከፈል ፣ ዘንድ ፣ ሊስማሙ ፣ ይችላሉ ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፹፱) ። ከዚህ ፣ ላይ ፣ ይህን ፣ ጉዳይ ፣ ነክ ፣ ከሆነው ፣ የሚነሳው ፣ አሻሚውና ፣ አከራካሪው ፣ ጉዳይ ፣ ከአበሮቹ ፣ አንዱ ፣ ሲሞት ፣ ውጤት ፣ የሚያገኘው ፣ ማናቸውም ፣ የስምምነት ፣ ግዴታ ፣ የሕጉ ፣ ቁጥር ፣ ፩ሺ.፩፻፲፬ ፣ ተቃራኒ ፣ ነውን ፣ ወይንስ ፣ አይደለም ፣ የሚለው ፣ ነው ፤ በዚህ ፣ ይዘት ፣ ላይ ፣ እስከሁን ፣ ድረስ ፣ አንድም ፣ የተሰጠ ፣ የፍርድ ፣ ውሳኔ ፣ የለም ።

ለ/ ጋብቻ ፣ በፍቺ ፣ ሲፈርስ ፣ ስለማጣራት ፣ ተግባር ፤

ለመፋታት ፣ በተፈቀደ ፣ ጊዜ ፣ የግልና ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረት ፣ በንዴት ፣ ያለ ፣ አኳኋን ፣ እንዲጣራ ፣ የመወሰኑ ፣ ጉዳይ ፣ የቤተሰቡ ፣ የሽምግልና ፣ ዳኞች ፣ ውሳኔአቸውን ፣ እንዲሰጡባቸው ፣ ከተመደቡት ፣ ጉዳዮች ፣ አንዱ ፣ ነው ። እንደዚህ ፣ ያለን ፣ ውሳኔ ፣ በሚያደርጉበትም ፣ ጊዜ ፣ የቤተዘመድ ፣ ገላጋይ ፣ ዳኞቹ ፣ ስለዚህ ፣ ጉዳይ ፣ ከቁጥር ፣ ፮፻፺ ፣ እስከ ፣ ቁጥር ፣ ፮፻፺፩ ፣ የተጣሉትን ፣ መሠረተ ፣ ሐሳቦች ፣ መከተል ፣ ይገባቸዋል ። በጠቅላላ ፣ አነጋገር ፣ ሲመለከቱት ፣ የማጣራቱ ፣ ተግባር ፣ እንደዚያው ፣ ጋብቻ ፣ በሞት ፣ መለያየት ፣ ሲፈርስ ፣ እንደሚደረገው ፣ ያለ ፣ ነው ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፺) ። ነገር ፣ ግን ፣ ከዚህ ፣ መሠረተ ፣ ሐሳብ ፣ በላይ ፣ በተጨማሪ ፣ ሕጉ ፣ ከፍቺው ፣ በፊት ፣ በአበሮቹ ፣ መካከል ፣ የተፈጸመ ፣ የጋብቻ ፣ ውል ፣ ወይም ፣ ምንም ፣ ዓይነት ፣ ስምምነት ፣ ሊለዋውጣቸው ፣ የማይቻለውን ፣ አንዳንድ ፣ ደንቦችን ፣ ይወስናል ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፺ (፬)) ።

በጋብቻው ፣ በዓል ፣ አሳቦ ፣ ወይም ፣ ጋብቻው ፣ በማለቱ ፣ ምክንያት ፣ የተሰጣጡትን ፣ ስጦታዎች ፣ ሁሉ ፣ የቤተሰቡ ፣ ገላጋዮቹ ፣ ይመለስ ፣ ዘንድ ፣ ሊያዝዙ ፣ ይችላሉ ። ስጦታውን ፣ ያበረከተው ፣ ሰው ፣ ከአበሮቹ ፣ አንዱ ፣ ለሌላው ፣ አበር ፣ ቢሆን ፣ ወይም ፣ ሌሎች ፣ ሰዎች ፣ ለአበሮቹ ፣ ያደረጉት ፣ ቢሆን ፣ አበርካቹ ፣ እንዲመለስለት ፣ ከጠየቀ ፣ ይመለስለታል ፤ እንዲሁም ፣ ስጦታውን ፣ ያበረከተው ፣ ሞቶ ፣ እንደሆነም ፣ ወራሾቹ ፣ እንዲመለስላቸው ፣ ሊጠይቁ ፣ ይችላሉ ። በጋብቻው ፣ ሥነ ፣ በዓል ፣ ጊዜ ፣ ወይም ፣ ጋብቻውን ፣ ምክንያት ፣ በማድረግ ፣ ለአበሮቹ ፣ ወይም ፣ ከነርሱ ፣ አንዱ ፣ ከሌላ ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ ጋራ ፣ ሊገባበት ፣ ይችል ፣ የነበረውን ፣ ወይም ፣ የገባውን ፣ የማናቸውንም ፣ የጥቅሞች ፣ ተስፋ ፣ ቃልን ፣ የቤተሰቡ ፣ ገላጋዮች ፣ ሊሠርዙት ፣ ይችላሉ ፣ (ቁጥር ፣ ፮፻፺፭) ። እነሆ ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ የተወሰነ ፣ ገንዘብ ፣ ልክን ፣ ቆርጦ ፣ በየወሩ ፣ ከአበሮቹ ፣ ላንዱ ፣ ለመክፈል ፣ የተስፋ ፣ ቃል ፣ ቢገባ ፣ ወይም ፣ ለጋብቻ ፣ መገላገያ ፣ ይሆን ፣ ዘንድ ፣ ህላዌን ፣ ሳይለውጥ ፣ እንዲኖርበትና ፣ እንዲጠቀምበት ፣ አንድ ፣ ቤትን ፣ ከአበሮቹ ፣ ላንዱ ፣ ሰጥቶት ፣ እንደነበረ ፣ የቤተዘመድ ፣ ገላጋዮች ፣ ዳኞቹ ፣ ይህንኑ ፣ ለአበሩ ፣ ተሰጥቶ ፣ የነበረውንና ፣ እንደዚህ ፣ ያለውን ፣ ጥቅም ፣ ሊሠርዙበት ፣ ይችላሉ ፣ ማለት ፣ ነው ።

ስለጋራውና ፣ ስለ ፣ የግል ፣ ሀብት ፣ ንብረቱ ፣ ስለሚመለከቱት ፣ ጉዳዮች ፣ በሚነጋገሩበት ፣ ጊዜ ፣ የቤተ ፣ ዘመዱ ፣ የሽምግልና ፣ ዳኞች ፣ ፍቺውን ፣ ያስከተ

ለው ፣ መነሾ ፣ ምክንያት ፣ ከባድ ፣ ወይም ፣ ከባድ ፣ ያይደለ ፣ እንደሆን ፣ መመ ርመር ፣ አለባቸው ፤ እንዲሁም ፣ ደግሞ ፣ የፊቺው ፣ መነሾ ፣ ምክንያትን ፣ ያመ ጣው ፣ ጥፋት ፣ ወደአንዱ ፣ አባሪ ፣ የጠባይ ፣ ጉድለት ፣ የሚያመራ ፣ እንደሆነ፣ መለየት ፣ አለባቸው ።

የፍቺው ፣ መነሾ ፣ ምክንያት ፣ ከባድ ፣ ሆኖ ፣ ጥፋቱ ፣ ወደ ፣ አንዱ ፣ አባሪ፣ ጠባይ፣ ጉድለት ፣ ሲያዘም ፤ አጥፊው ፣ አባሪ ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረቱን ፣ በምሉ ፣ ላላጠፋው ፣ አባሪ ፣ እንዲተውለት ፣ ሊታዘዝ ፣ ይቻላል ። እንደዚሁም ፣ አጥ ፊው ፣ አባሪ ፣ ከግል ፣ ሀብቱ ፣ ውስጥ ፣ ከሢሦ ፣ (ከአንድ ፣ ሦስተኛ ፣)የማይለ ቀውን ፣ ዕጣ ፣ ከፍሎ ፣ ላላጠፋው ፣ (ንጹሕ ፣)አበሩ ፣ እንዲተውለት ፣ ሊታ ዘዝ ፣ ይቻላል ። እንደዚህ ፣ ያለው ፣ መቀጫም ፣ (ቅጣት ፣) በቍጥር ፣ ፰፻፺፩ ፣ እንደተመለከተው ፣ ስለስጦታዎች ፣ መልስ ፣ ለሰጭ ፣ ማስረከብ ፣ ከተወሰነው ፣ በላይ ፣ በተጨማሪ ፣ ሊጣል ፣ ይቻላል ። መቀጫዎቹም ፣ ጥፋት ፣ አልባ ፣ በሆ ነው ፣ አበር ፣ ላይ ፣ ከቶ ፣ ሊጣሉበት ፣ አይቻልም ። ወይም ፣ ምንም ፣ እንኳ ፣ የፍቺው ፣ መነሾ ፣ ምክንያት ፣ ከባድ ፣ ቢሆንም ፣ ቅሉ ፣ አጥፊነቱ ፣ በማያመራ በት ፣ አበር ፣ ላይ ፣ መቀጫዎቹ ፣ ሊጣሉበት ፣ አይቻልም ፣ በእንደዚህ ፣ ያሉት ፣ ነገሮች ፣ ላይ ፣ የሀብት ፣ ግንኙነትን ፣ የማጣራቱ ፣ ተግባርም ፣ እንደዚያው ፣ ጋብቻ ፣ በሞት ፣ በመለያየት ፣ ሲፈርስ ፣ እንደሚደረገው ፣ ያለ ፣ ነው ።

የፍቺው ፣ መነሾ ፣ ከባድ ፣ ባልሆነ ፣ ምክንያት ፣ የሆነ ፣ እንደሆነ ፣ ከላይ ፣ የተዘረ ዘሩት ፣ መቀጫዎች ፣ (ማለት ፣ ስጦታዎችን ፣ መመለስ ፣ — ቍጥር ፣ ፰፻፺፩ ፣ እና ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረትንና ፣ ከግል ፣ ሀብቱ ፣ የተቆረጠ ፣ ድርሻ ፣ በመቀጫ ፣ መልክ ፣ መስጠቱ ፣ — ቍጥር ፣ ፰፻፺፪ ፣) ፍቺውን ፣ በጠየቀው ፣ ሰው ፣ ላይ ፣ ብቻ ፣ ይወድቅበት ፣ ዘንድ ፣ ማዘዝ ፣ ይቻላል ፣ (ቍጥር ፣ ፰፻፺፬)። ይህ ፣ ሕግ ፣ ያለመው ፣ ከከበዱት ፣ መነሾ ፣ ምክንያቶች ፣ በንዱ ፣ ላይ ፣ ካልተመሠረተ ፣ በቀር ፣ የፍቺ ፣ ጥያቄዎች ፣ እንዳይቀርቡ ፣ ለማጣጣል ፣ (ላለመደፋፈር ፣)ነው ፣ የፍቺው ፣ ምክንያት ፣ ከባድ ፣ ባልሆነበት ፣ ላይ ፣ እንዲፋታ ፣ ልመናውን ፣ የሚ ያሚቀርበው ፣ ሰው ፣ (ራሱ ፣)የመፋታቱን ፣ ፈቃድ ፣ ማግኘቱ ፣ በገንዘብ ፣ ሀብት ፣ በኩል ፣ እንደሚያዋጣው ፣ (እንደማያተርፈው ፣)ሊያውቀው ፣ ይች ላል ፣ ማለት ፣ ነው ።

ምንም ፣ እንኳ ፣ የቤተ ፣ ሰቡ ፣ ገላጋዮች ፣ የተጠቀሱትን ፣ መቀጫዎች ፣ ከግብር ፣ ላይ ፣ ያውሏቸው ፣ ዘንድ ፣ ቢገባ ፣ መቀጫዎቹን ፣ በምን ፣ መልክና ፣ ጠባይ ፣ በመሰላቸ ውና ፣ ይበጃል ፣ በሚሉበት ፣ መንገድ ፣ በግብር ፣ ላይ ፣ እንዲውሉ ፣ ማደላደሉ ፣ የነርሱ ፣ ፈንታ ፣ ነው ። የቤተዘመድ ፣ የሽምግልና ፣ ዳኞች ፣ ስለመቀጫዎች ፣ (ቍጥር ፣ ፰፻፺፩ ፣ እና ፣ ፰፻፺፪ ፣) የሰፈሩትን ፣ ደንቦች ፣ ዓይኖቻቸውን ፣ ጨፍነው ፣ የሚከተሏቸው ፣ አይ ደሉም ፤ በግብር ፣ ላይ ፣ ሊያውሏቸውም ፣ ይችላሉ ፤ በኅሊናቸው ፣ እንደመሰላቸውና ፣ ይበጃል ፣ ብለው ፣ እንደሚገምቱት ፣ ደንቦቹን ፣ በምሉ ፣ ወይም ፣ በከፊል ፣ በግብር ፣ ላይ ፣ ሊያውሏቸውም ፣ ይችላሉ ። ይህን ፣ በነጻ ፣ እንደመሰላቸው ፣ የመወሰን ፣ ተግባር ከፍና ዝቅ ፣ እያደረጉ ፣ በሚገለገሉበት ፣ ጊዜ ፣ ለድርጊታቸው ፣ አጥጋቢ ፣ የሆነ ፣ ምክንያት ፣ እንዲኖራቸውና ፣ እሊሁም ፣ በውሳኔአቸው ፣ ላይ ፣ እንዲሰፍሩ ፣ ይገባል ። ደንቦቹን ፣ በምሉ ፣ ወይም ፣ በከፊል ፣ በግብር ፣ ላይ ፣ ለማዋል ወይም ፣ ላለማዋል ፣ በሚወስኑ በት ፣ ጊዜ ፣ የቤተ ፣ ዘመድ ፣ ገላጋይ ፣ ዳኞቹ ፣ ሊያመዛዝኑት ፣ የሚገባቸው ፣ የፍቺ ፣ ጥያቄውን ፣ እንዲቀርብ ፣ የገፋፉትንና ፣ የከበቡትን ፣ ምክንያቶችን ፤ የበዳዩን ፣ ወገን ጥፋት ፣ ደረጃን ፣ ያላጥፊው ፣ አበርን ፣ የጠባይ ፣ አቋምንና ፣ አመራርን ፤ እንዲሁም ፣ ጥያ

ቂውን ፡ የቀሰቀሰው ፡ መነሾ ፡ ምክንያትንና ፡ የጥያቄውን ፡ የበጎና ፡ ትክክለኛ ፡ ጠባይ ፡ (ሞራል ፡)ትይንቱን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልጋል ፡ (ቊጥር ፡ ፮፻፺፭ ።)

ሐ/ ጋብቻ ፡ በሞት ፡ ወይም ፡ በፍቺ፡ምክንያቶች ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ምክንያቶች ፡ ሲፈርስ ፡ ስለማጣራት ፡ ተግባር ፤

ቊጥር ፡ ፮፻፺፮ ፡ ስለጋብቻ ፡ የተወሰኑት ፡ ግዴታዎች ፡ በመጣስ ፡ ጋብቻው ፡ በም ጥንታ ፡ ሕግ ፡ በቅጣት ፡ ሲፈርስ ፡ ስለ ፡ አበሮቹ ፡ የሀብት ፡ ንብረት ፡ ግንኙነት ፡ ማጣራት ፡ ተግባር ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦችን ፡ ይዘረዝራል ። እነዚህም ፡ ደን ቦች ፡ እንደሚከተለው ፡ ናቸው ፤

ሀ/ ከቊጥር ፡ ፮፻፺ ፡ —፮፻፺፩ ፡ ድረስ ፡ የተመለከቱት ፡ ሐሳቦች ፡ እንደ ፡ ረዳትና ፡ መሪ ፡ ሐሳቦች፡ብቻ ፡ የሚቆጠሩ፡ናቸው ፡ እንጂ ፡ በምንም ፡ በኩል ፡ እነርሱ ፡ ከፈለሙት ፡ መንገድ ፡ እንዳይወጣ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የሚገቱ ፡ አይደሉም ፤

ለ/ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የራሱን ፡ ውሳኔ ፡ የሚያደርገው ፡ በርትዕ ፡ (በፍትሕ ፡ / በትክክ ልነት ፡) መሠረት ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፡

ሐ/ ርትዕን ፡ በሚዳኝበት ፡ (በግብር ፡ ላይ ፡ በሚያውልበት ፡)ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያመዛዝነው ፡ በተለይ ፡ የአበሮቹን ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ያንዱን ፡ ታማኝነ ትን ፡ (ትክክለኛነት ፡ ቅንነትን ፡) ወይም ፡ አጭበርባሪነትን ፡ (አታላይነትን ፡) ከጋብቻው ፡ የተገኙ ፡ (እንዳለበት፡) ልጆች ፡ ጥቅምን፡እና ፡ አበሮቹ፡በተጋቡበት፡ ቀንና ፡ ጋብቻውን ፡ በፈረሱበት ፡ ቀን፡መካከል ፡ ማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ (ከነርሱ ፡ ጋራ ፡)ፍርድ ፡ ነክ ፡ የሆነን ድርጊት ፡ ፈጽሞ ፡ እንደሆነን ፡ በቅንነት ፡ (በእምነት ፡)የተነጋገሩትን ፡ ፍርድ፡ነኩን ፡ ተግባር ፡ የፈጸሙትን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጥቅምን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማመዘን ፡ ነገሩን ፡ ይመለከታል ።

ከዚህ ፡ ላይ ፡ ሊያስታውሱት ፡ የሚገባው ፡ የጋብቻ ፡ ግዴታዎች ፡ በመጣሳቸው ፡ በምጥንታ ፡ (በቅጣት ፡)ጋብቻው ፡ በሚፈርስበት ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ጋብቻውን ፡ የማፍ ረሱ ፡ ጉዳይና ፡ የሚያስከትለው ፡ የሀብት ፡ ግንኙነትን ፡ የማጣራት ፡ ተግባሩ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንጂ ፡ የቤተሰብ ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞች ፡ ጉዳይ ፡ እንዳይደለ ፡ ነው ።

፮፤ የወዶገብነት ፡ (አጉል/ ውጥንቅጥ ፡) ኅብረት ፡ እና ፡ ሌላ ፡ ግንኙነቶች ፡ ወዶገብነት ፡ ኅብረት ፤

ዘወግና ፡ ልማድ ፡ ሥርዓት ፡ (ሕግ ፡) መሠረት ፡ ቀድሞ ፡ በደምዝ ፡ በሚል ፡ ይታ ወቅ ፡ የነበረውን ፡ ጋብቻ ፡ ዓይነት ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ አይቀበለውም ። ይሁን ፡ እ ንጂ ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ የሚገኙበትን ፡ ያንድ ፡ ላይ ፡ ኑሮ ፡ ሀልውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ በሕግ ፡ ያውቀዋል ፤ ለዚህ ፡ ሀል ውም ፡ የወዶ —(ለምዶ ፡)—ገብነት ፡ ኅብረት ፡ (ወይም ፡ ውጥንቅጥ ፡ ፅምረት ፡ (ጥምረት፡) ወይም ፡ ኅብረት ፡) የሚል ፡ ስምን ፡ ሕጉ ፡ አውጥቶለታል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥም ረት ፡ አንዳንድ ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤቶችን ፡ ይወልዳል ፡ እንጂ ፡ የወዶ ፡ ለምዶነት ፡ ኅብረት ፡ ጋብቻ ፡ አይደለም ። ውጤቶቹም ፡ ሕጋዊው ፡ ጋብቻ ፡ ከሚወልዳቸው ፡ ውጤቶች ፡ በጣ ም ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ። የውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ቋሚ ፡ በሕርዩው ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ ጋብቻ ፡ ሕግ ፡ በወቀለት ፡ ሥርዓቶች ፡ መልክ ፡ የሚከናወን ፡ (የሚሾም ፡) ምንም ፡ ዓ ይነት ፡ ጋብቻ ፡ የሌለበት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ በቀላሉ ፡ አንዳንድ ፡ የተወሰኑን ፡ ውጤቶች ፡ የሚቀሰቅስ ፡ (የሚያነሣ ፡) ሀልው ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ትርጓሜ ፡ በሚያስኬደው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ስንመለከተው ፡ ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚኖረው ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ላይ፡ ሲኖሩና ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በመቆጠር ፡ ሲተዳደሩ ፡ ነው ፡፡ በየዕለቱ ፡ ኑሯቸው ፡ እራሳቸውን ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አካል ፡ አድርገው ፡ በመተዳደር ፡ ሕይወታቸውን፡ እስከ ፡ መሩ ፡ ድረስ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ተብለው ፡ መስለው ፡ በሌሎች ፡ ዘንድ ፡ ራሳቸውን ፡ ማቅረቡ ፡ (መወከሉ/ማስተዋወቁ ፡) አስፈላጊ ፡ አይደለም ፡፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ሰርክ ፡ ቢገናኙና ፡ እንዲያውም ፡ ባልተሸፋፈነ ፡ አኳኋን ፡ (ማለት ፡ ይህ ፡ ግብራቸው ፡ በሌሎች ፡ ዘንድ ፡ ጐልቶ ፡ እስቲያውተመትሙብትና ፡ እስቲታወቅ ፡ ድረስ ፡) እንዲሁም ፡ የተደጋገመ ፡ ሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድናዎች ፡ (የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነቶች ፡) ቢኖራቸው ፡ እንኳ ፡ ቅሉ ፡ ይህ ፡ ሀልው ፡ በራሱ ፡ ሱታፌውን ፡ እንደ ፡ ወዶ ፡ ለምዶ ፡ ኅብረት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ለማስቆጠር ፡ በቂ ፡ አይደለም ፤ ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚያስከትለውን ፡ የሕግ ፡ ውጤቶችንም ፡ ሊወልድ ፡ አይችልም ፡ (ቊጥር ፡ ፯፻፰ ፡፡)

ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ መኖሩን ፡ ማረጋገጡ ፡ የምስክር ፡ ማስረጃ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፤ ይኸም ፡ የምስክር ፡ ማስረጃ ፡ የሚነጻጸረው ፡ ከሌሎች ፡ ከካባቢያቸው ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ባላቸው ፡ የማኅበራዊ ፡ አኗኗር ፡ ደረጃ ፡ መጠን ፡ ነው ፡፡ ይህም ፡ ያኗኗር ፡ አቋም ፡ የወንድየውና ፡ የሴትዮዋ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ እና ፡ ጎረቤቶች ፡ በእውነቱ ፡ ሳይጋቡ ፡ እንደተጋቡ ፡ እንደሚኖሩ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርገው ፡ ሲገምቷቸው ፡ (ሲቆጥሯቸው ፡) ማለት ፡ ነው ፡ (ቊጥር ፡ ፯፻፲፰ ፡፡) እንግዲህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ያኗኗር ፡ አቋም፡ እንዳለ ፡ የሚያስረዳው ፡ የታመኑ ፡ ምስክሮችን ፡ በማስመስከር ፡ ነው ፡፡ እንደዚሁም ፡ ምስክሮችን ፡ አቅርቦ ፡ ያኗኗር ፡ አቋም ፡ አለመኖሩን ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ፡፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ምስክር ፡ ማስረጃ ፡ ሲታጣ ፡ ከጽሑፍ ፡ ነጋሪ ፡ በለሥልጣን ፡ ፊት ፡ (በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ «በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ » ያለውን ፡ ነው ፤) በተፈጸመ ፡ የጽሑፍ ፡ ክንውን ፡ ያኗኗር ፡ አቋምን ፡ ያስረዱል ፡ (ቊጥር ፡ ፯፻፲፱ ፡ እና ፡ ፯፻፳ ፡፡)

<u>የወዶ ፡ ገብነት ፡ ኅብረት —</u>

ሀ/ በወንድየውና ፡ በሴትዮዋ ፡ መካከል ፡ ኑሮን ፡ ለመጠበቅ ፡ የመተዳደሪያ ፡ አበል ፡ ግዴታን ፤

ለ/ በወንድየውና ፡ በሴትዮዋ ፡ መካከል ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረትን ፤

ሐ/ በወንድየውና ፡ በሴትዮዋ ፡ መካከል ፡ ማናቸውንም ፡ የውርስ ፡ መብቶችን ፡ (ቊጥር ፡ ፯፻፲፭ ፡ ፯፻፲፪ ፡ እና ፡ ፯፻፲፫) ፡ አይፈጥርም ፡፡

ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ በደንበኛው ፡ ጋብቻ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያለ ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድናን ፡ የመሰለ ፡ መተሳሰሪያን ፡ አያስከትልም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለሕዝብ ፡ በጎ ፡ ኑሮ ፡ የሕዝብ ፡ ሰላም ፡ ሥርዓትን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ በውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚኖሩት ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ እንደተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ ታይተው ፡ የወንዱና ፡ የሴቲቱ ፡ ዘመዶች ፡ (የጋብቻ ፡ ዝምድናን ፡ ወሰን ፡ ጥሰው ፡) እንዳይጋቡ ፡ ክልክል ፡ ናቸው ፡ (ቊጥር ፡ ፯፻፲) ፡፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ዋጋ ፡ ከደንበኛው ፡ ጋብቻ ፡ ጋራ ፡ (እኩል ፡) ተመጣጣኝ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ከኅብረቱ ፡ ለሚወለዱት ፡ ልጆች ፡ አባትነትና ፡ እናትነት ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ለተወለዱት ፡ ልጆች ፡ የሚሆኑት ፡ ደንቦች ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ለተወለዱት ፡ ልጆችም ፡ ይሆናሉ ፡ (ቊጥር ፡ ፯፻፲፩) ፡፡

የውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ያፈጸጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በማንም ፡ ጊዜ ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ። የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞቹም ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚነሱ ትን ፡ ነገሮች ፡ ለማየት ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ የላቸውም ፤ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚነ ሱትን ፡ ክርክሮች ፡ ሁሉ ፡ ለማየት ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፴) ። ኅብረቱን ፡ የምትሰርዘው ፡ (የምትሽረው ፡) ሴቲቱ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ለ ወንድ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ እንድትከፍል ፡ አይደረግም ፤ ወይም ፡ በኅብረቱ ፡ ወራት ፡ ወንዱ ፡ አበርክቷት ፡ ሊሆን ፡ የሚችለውንም ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ መልሳ ፡ እንድታስረክበው ፡ አይደረግም ። ኅብረቱን ፡ የሚያፈርሰው ፡ ወንድየው ፡ ሲሆ ን ፡ ግን ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፲፯ ፡ መሠረት ፡ ሴቲቱ ፡ ለሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ኑሮ ፡ መተዳደሪያ ፡ ወጭዎቿ ፡ በቂ ፡ የሚሆናትን ፡ ገንዘብ ፡ ወንዱ ፡ እንዲከፍላት ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አ ላት ፡ (እስከዚህ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ በአማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። በእንግሊዝኛው ፡ ትርጒም ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ስድስት ፡ ወራት ፡ ተብሏል ። በሕጉም ፡ ፈረንሣይ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋና ፡ ቅጅ ፡ ስድስት ፡ ወራት ፡ ተብሏል ።)

ከማእሰረ ፡ ጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ግንኙቶች ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ የተሰጣቸው ፡ የወንድና ፡ የሴ ት ፡ ግንኙነቶች ፡ (ሀ) ፡ ጋብቻ ፡ እና ፡ (ለ) ፡ ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በጋብቻ ፡ ረገድ ፡ ሦስት ፡ የጋብቻዎች ፡ አይነቶች ፡ አሉ ፡ ከእነዚህም ፡ የተለያዩ ፡ ሌሎች ፡ ከቶ ፡ የሉም ፤ እነዚህም ፡ ብሔራዊ ፡ የሃይማኖትና ፡ የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ የተባሉት ፡ ናቸው ። በቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፸፪ ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ (ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡) ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ይ ሠራበቸው ፡ የነበሩት ፡ የልማድ ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ (ከነዚያ ፡ ውስጥ ፡ በዚህም ፡ ሕግ ፡ ጸ ድቀው ፡ ከቀሩት ፡ ልማዶች ፡ በቀር ፡) መሻራቸውን ፡ ማስታወስ ፡ ያስፈልጋል ። ቍጥር ፡ ፯፻፹፩ ፡ በወንድና ፡ በሴት ፡ መካከል ፡ ያለን ፡ የግንኙነትን ፡ ይዞት ፡ አጥብቆ ፡ ሲያጠይቅ ፤ ግንኙነቱ ፡ የተነሣው ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከወዶ–ለምዶ ፡ (ከውጥንቅጥ ፡) ኅብረ ት ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ በወንድና ፡ በሴት ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ግንኙነት ፡ ምንም ፡ አንዳች ፡ ውጤት ፡ እንደሌለው ፡ ያረጋግጣል ። ከሕጋዊ ፡ ወይም ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ጥምረት ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ግንኙነቶች ፡ ምንም ፡ አንዳች ፡ የሕግ ፡ ውጤት ፡ ስለሌላቸው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢ ሆን ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ (በሌላ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡) በወንድና ፡ በሴ ት ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ አለ ፡ የሚል ፡ ይዞትን ፡ ሊያነሣበት ፡ አይችልም ። እነሆ ፡ ቆየ ት ፡ ብለን ፡ እንደምንረዳው ፡ ከአንዲት ፡ (በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡) አንድ ፡ ወንድ ፡ ጋራ ፡ ከተጋባች ፡ ሴት ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ አባቱ ፡ የዚያችው ፡ ሴት ፡ ባል ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ያንንም ፡ ልጅ ፡ ሊክድ ፡ የሚችለው ፡ አባት ፡ ያው ፡ ብቻ ፡ ነው ። በቍጥር ፡ ፯፻ ፹፩ ፡ (፪) ፡ መሠረት ፤ ልጄ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ለመካድ ፡ ለሚሻ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የሕፃኑ ፡ እናት ፡ በእውነቱ ፡ ከሌላ ፡ ወንድ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነቶችን ፡ ፈጽማለች ፡ ብሎ ፡ ለ ማለት ፡ አይቻለውም ። ምክንያቱም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የተነሣ ፡ ሊሆን ፡ አይችልምና ፡ ነው ።

ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ውጭ ፡ በሚገኝ ፡ ግንኙነት ፡ ባሉ ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ የተወለዱ ፡ ልጆችን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮ ች ፤ ቍጥር ፡ ፯፻፹፩ ፡ (፫) ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ ልጆች ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የመተሳሰር ፡ ዝምድናዎች ፡ ያሏቸው ፡ ከናታቸው ፡ ጋራ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል ። ይህ ፡ መሪ ፡ ሐሳብ ፡ ከቍጥር ፡ ፯፻፸፯ – ፯፻፺፰ ፡ እንደ ፡ ተደነገጉት ፡ የበሕርይ ፡ አባቱ ፡ ልጅነቱን ፡ ላወቀለት ፡ ልጅ ፡ አይሆንም ፡ ወይም ፡ ልጅን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በጉድፈቻ ፡ ልጅነት ፡ ሲቀ

በለው ፣ በፍርድ ፣ ረገድ ፡ ልጅ ፡ በዝምድና ፡ (ግንኙነት ፣) የተሳሰረው ፣ ከናቲቱ ፣ ጋራ ፣ ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ ከተቀበለውም ፡ አባት ፣ ወይም ፡ በጉድፈቻ ፣ ልጅነት ፣ ከተቀበለው ፣ ሰው ፣ ጋራ ፣ ስለሚሆን ፣ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፣ መሪ ፣ ሐሳብ ፣ ለእንደዚህ ፡ ላለው ፣ ልጅ ፣ አያገለግልም ።

<u>፯ ፡ በጋብቻዎች ፣ በፍቺዎችና ፣ በወዶለምዶ ፣ ኅብረቶች ፣ ስለሚነሡት ፣ ክርክሮች ።</u>

በቍጥር ፣ ፯፻፳፪ ፡ እና ፡ ከተከታታዮቹ ፡ የፍትሐ ፣ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ በትጭጭቶች ፡ በጋብቻዎችና ፣ በውጥንቅጥ ፡ ጽምረት ፡ የሚነሡት ፣ ክርክሮች ፡(ጭቅጭቆች ፡) ከንውን ፣ መልክ ፣ የሚዳኙትን ፣ ደንቦች ፡ መሥርቷል ። በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፣ ያለው ፣ መተጫጨት ፣ ተደርጎ ፣ እንደሆነ ፣ ወይም ፡ የጋብቻው ፡ በዓል ፣ ተሹሞ ፣ እንደሆነና ፣ እንደ ዚህ ፣ ከሆነ ፣ ዘንዳም ፡ ጋብቻው ፣ በሕግ ፣ ፊት ፡ ዋጋ ፣ ያለው ፣ እንደሆነ ፤ እንዲሁም ፣ ወይም ፣ በሁለት ፡ ሰዎች ፣ መካከል ፣ ውጥንቅጥ ፣ ኅብረት ፡ ተዘርግቶ ፡ እንደሆነ ፣ ለመወሰን ፣ የዳኝነት ፣ ምሉ ፣ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፣ (ቍጥር ፣ ፯፻፳፪ ፣ ፯፻፳፱ ፣ ፯፻፴) ። ደግሞም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፣ ከውጥንቅጥ ፣ ጽምረት ፣ የሚነሡትን ፣ ጉዳዮች ፣ ሁሉ ፣ ለመወሰን ፡ ፍጹም ፡ የዳኝነት ፣ ሥልጣን ፣ አላቸው ። ይሁን ፣ እንጂ ፡ ከትጭጭት ፣ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ በሚነሡት ፡ ክርክሮች ፣ ረገድ ፣ ክርክሮቹ ፣ በመዠመሪያው ፣ ክፍል ፣ የሚታዩት ፣ በቤተ ፡ ሰቡ ፣ ገላጋዮች ፣ ዳኞች ፡ ይሆን ፣ ዘንድ ፣ ያስፈልጋል ።

በመተጫጨት ፡ ምክንያት ፣ ወይም ፡ የትጭጭት ፡ ስምምነትን ፣ በማፍረስ ፣ ምክንያት ፣ ስለሚነሡት ፡ ክርክሮች ፣ ገላጋይ ፣ ዳኞቹ ፣ በትጭጭቱ ፣ ጊዜ ፡ ምስክሮች ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፣ ናቸው ። በመዠመሪያ ፣ ደረጃ ፣ ምስክርነት ፡ ተደልድለው ፣ የነበሩ ፣ ካሉ ፣ ገላጋይ ፣ ዳኞቹ እንደነዚህ ፡ ያሉት ፣ ምስክሮች ፣ ይሆናሉ ። በትጭጭቱ ፣ ጊዜ ፣ ወይም ፣ ቆየት ፡ ብለው ፡ (ባለጉዳይ) ወገኖቹ ፣ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፣ ሌሎች ፡ ሰዎች ፣ እንዲሆኑላቸው ፣ ከመደልደል ፡ የሚያግዳቸው ፣ አንዳችም ፣ ምክንያት ፣ የለም ፣ (ቍጥር ፣ ፯፻፳፫) ።

በጋብቻው ፣ ገራት ፣ ውስጥ ፡ በሚነሡት ፡ ነገሮች ፣ የቤተሰቡ ፣ ገላጋይ ፣ ዳኞቹ ፣ በጋብቻው ፣ ጊዜ ፡ ምስክሮች ፡ ሁነው ፣ የነበሩት ፣ ናቸው ። እንደዚሁም ፣ ጥቂት ፣ ሰዎች ፣ የመዠመሪያ ፣ ደረጃ ፣ ምስክሮች ፣ በመሆን ፣ ተደልድለው ፣ የነበሩ ፣ ካሉ ፣ የቤተ ዘመዱ ፣ ገላጋይ ፣ ዳኞቹ ፡ እነዚሁ ፣ የመዠመሪያ ፣ ደረጃ ፣ ምስክሮች ፣ መሆን ፣ አለባቸው ። በሚጋቡበት ፣ ጊዜ ፡ ወይም ፣ ዘግየት ፣ ብለው ፣ ለምሳሌ ፣ ክርክሩ ፣ በግልጽ ፣ በሚነሣበት ፣ ጊዜ ፣ አበሮቹ ፣ ክርክሩን ፣ እንዲያዩላቸው ፣ ገላጋይ ፡ ዳኞች ፣ የሚሆኑ ፣ ሌሎች ፣ ሰዎችን ፣ ሊደለድሉ ፣ ይችላሉ ፡ (ቍጥር ፣ ፯፻፳፭) ። ደግሞም ፣ በሞት ፣ መለየት ፣ ጋብቻው ፡ ሲፈርስ ፣ አስቀድመው ፣ (በመዠመሪያው ፡ ክፍል) ክርክሮቹን ፣ ለማየት ፡ መብት ፣ ያላቸው ፣ የቤተ ፣ ዘመዱ ፣ የሽምግልና ፣ ዳኞቹ ፣ ናቸው ፣ (ቍጥር ፡ ፯፻፳፮) ። ማናቸውም ፣ ዓይነት ፡ ክርክር ፣ በጋብቻው ፣ ወራት ፣ ሳይሆን ፡ ፍቺው ፡ ከተለፈፈ ፣ በኋላ ፣ ቢነሣ ፣ ክርክሩ ፣ ከነዚያው ፣ ፍቺውን ፣ ከበየኑት ፡ ገላጋይ ፣ ዳኞች ፣ ፊት ፣ ይቀርባል ፣ (ቍጥር ፣ ፯፻፳፯) ። የቤተሰቡ ፡ የሽምግልና ፣ ዳኞቹ ፡ ሕግ ፣ በሚፈቅድላቸው ፣ ጊዜ ፡ ውስጥ ፣ ከውሳኔ ፣ ለመድረስ ፣ አቅቷቸው ፣ ፍቺውን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ በሚበይንበት ፣ ጉዳይ ፣ ላይ ፡ ሕጉ ፣ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የተለየና ፣ የጐላ ፣ ድንጋጌ ፡ አላደረገም ፣ (ቍጥር ፣ ፯፻፴፪ን ፣ ይመለከቷል)። ነገር ፣ ግን ፣ በእንደዚህ ፣ ያሉት ፣ ነገሮች ፣ ከፍቺው ፡ በኋላ ፣ የሚነሣው ፣ ክርክር ፣ ለፍርድ ፣ ቤቱ ፣ እንዲቀርብ ፣ ይገባል ። ከውጥንቅጥ ፣ ኅብረት ፣ የሚነሡት ፣ ክርክሮች ፣ በፍርድ ፣ ቤቱ ፡ የሚቀርቡ ፣ ናቸው ። (ቍጥር ፣ ፯፻፴) ።

real "separation of powers" at the *top* (incidentally, it may be inappropriate even to suggest that a separation of supreme powers doctrine – completely alien to the national tradition – be imported from abroad).

2. LEGISLATION

Legislation by Emperor *cum* Parliament under Arts. 88–90 or by imperial decree under Art. 92[10] constitutes the ordinary law between the Constitution above, and *non*-sovereign Administrative enactments below. Such legislation's dependence on the Constitution under Art. 122 may be, as stressed above, somewhat platonic. Conversely, such legislation's enforceability as against illegal lower enactments, although unmentioned in Art. 122, is a more practical proposition because under Art. 62 the *Administration* can be sued for any "wrongful" acts, which would include both those unconstitutional and those infringing ordinary legislation.

3. ADMNISTRATIVE ENACTMENTS

All Administrative acts are subordinate to the Constitution, and the *non*-sovereign ones (including, *e. g.*, those published by "Legal Notice") to ordinary legislation. There is a great variety of administrative enactments, and their nomenclature was far from unified, as a glance at past "Negarit Gazetas" will show. It will suffice here to stress that while *within*, respectively, the Constitutional or legislative category, rules are normally (subject to interpretation) equal, Administrative acts are further subordinated to one another;

a) Acts of lower authority obviously may not contradict those of higher authority;

b) According to world precedents and the "communis opinio doctorum"[11] an authority's particular decision may not infringe its own general rule or order. Until charged or repealed, such rule stands above its maker.

Infringement of either principle (a) or (b) or, *a fortiori*, of superior legislative provisions or of constitutional precepts, would be an illegality amounting to a "wrongful" act in the sense of Art. 62 of the Constitution and Art. 2035 plus

---

10. There is hardly a difference, *in effect*, between legislation proclaimed pursuant to Arts. 88-90 and legislative decrees based on Art. 92. This Article, poorly drafted, is confusing. In actual constitutional practice, imperial decrees issued between Parliament's sessions:

a) may repeal prior legislation;

b) do not lapse upon non-submission to reconvened Parliament, but continue in force until positively repealed. Parliamentary approval, if any, merely changes the terms of legal reference

11. *E. g.*, G. Vedel, *Droit Administratif*, Paris, 1958, vol. I, p. 161.

2126 of the Civil Code, and would thus enable the ordinary courts to grant relief where appropriate. But Art. 62 also provides a "right of action" against those bringing malicious "or unfounded" suits against the administration: this may deter even genuine claimants from bringing borderline cases.[12] Incidentally, any appeals for relief should first be brought to higher authority within the Administration itself (administrative remedies should normally be exhausted before going to court).[13] This need cause no hardship where administrative appeals follow precisely regulated patterns (*cf.* note 13). To what degrees such patterns are followed is unknown to this writer. Another premise for effective remedies is psychological: how far are administrators considered as servants, rather than masters, of the administered?

CONCLUSION

An approximate picture of the hierarchy of laws in Ethiopia results from an elementary analysis of the relevant Constitutional (and Civil Code) articles against a minimum background of Comparative Law. Theoretically, the Constitution is supreme, as in the United States. Practically there is, since the end of Federation, a remote analogy with those foreign systems where ordinary *legislation* is supreme (Great Britain), or at least free from judicial control (pre-1958 France). The following remarks on the pre-1958 French system may indeed bear some relevancy to our own situation: "It is the failure of the French courts to assert a review power over the constitutionality of acts of the legislature that . . . has in effect placed the French legislature in a position of practical supremacy not unlike that enjoyed by the British."[14] "The French courts . . . do not stand up against the legislator."[15] Neither do the

12. Said provision has no other effect. Legally, it is meaningless:
   a) Even without this provision, the Administration can, as any defendant can, claim damages if the court finds that the suit was malicious in terms of Article 2032 Civil Code (Intent to injure).
   b) Even with this provision the Administration should not, it is submitted, as no defendant should, be awarded damages (apart from cost-awards) on the sole ground that the suit turned out to be "unfounded". Indeed, no legal "remedies or penalties" to such effect have been enacted here or elsewhere, and none could be so enacted without affecting everybody's right to have a legal dispute determined in court.
13. This principle is reflected, for instance, in Sec. 54—62 of Income Tax Decree No. 19 of 1956. Appeals from the tax assessments made by the income tax authorities go first to the administrative Commission of Tax Appeal. The latter's decisions, in turn, are appealable (on points of law) before the High Court.
14. B. Schwartz, *French Administrative Law and the Common Law World*, New York 1954, p. 95.
15. *Id.* at 300. At present day, this statement remains true only regarding ordinary courts. Since 1958 France has a peculiar Constitutional court, whose primary task is preservation of the Prime Minister's constitutional powers of legislation (which are residual) from parliamentary interference. See M. Prélot, *Institutions politiques et droit constitutionnel*, Paris 1962, No. 484, 592 and 593.

Ethiopian courts so stand up. Nor would it be very pointful for them to do it in our wise system where the supreme co-legislator (the Emperor) is *also* the supreme judge. Because of this peculiar constitutional context, our Art. 122, though much more pungent in form, is much less significant in fact than its counterpart (Art. VI p. 2) in the United States Constitutiton, which throws no light on our problem.

As to *Administrative* acts, they can be, in France, " . . . subject both of an action to annul and of an action for damages. . . . In the action to annul, the challenged act is set aside if the court determines that it is *ultra vires*. In the action for damages against the State, the determination of the illegality of the act causing the injury leads to a judgment against the State on the basis of the fault it has committed in not making sure that its officers respect the principle of legality while performing their function - a fault that involves its tort liability."[16] This second type of action can be entertained by the Ethiopian courts on the basis of Art. 62 (*cum* Civil Code Arts. 2035 and 2126). For the first type of action, no such specific legal basis can be found. Indeed, apart from the Emperor, in whom, conformably to a sensible tradition, is vested supreme authority in all fields (Art. 26), there seems to exist, in Ethiopia, no judicial instance generally empowered to annul governmental enactments on ground of illegality. This assumption seems indirectly supported by the fact that, after enactment of the 1955 Constitution, special legislation was still deemed necessary, *e. g.*, to vest in the High and the Supreme Court a power to review the legality of particular tax assessments.[17] *A fortiori*, general governmental enactments seem immune from judicial nullification *erga omnes* in either general, or precedent-setting terms (as distinct from ordinary case-decision terms *inter partes*), notwithstanding Article 122 of the Constitution, which is largely programmatic; this, unless Article 122 can be indirectly bolstered by applying a United States patterned *stare decisis* doctrine to Supreme Court case-disposals,[18] in other words by putting in force Art. 16 of the suspended Courts Proclamation of 1962;[19] or unless some special Court with powers generally to cancel[20] illegal or unconstitutional enactments[21] is created (Continental pattern), always bearing in mind that the whole problem may be a little unreal in our wise system where one person (the Emperor) is head of *both* the Administration and the Judiciary, and, the Federal duality of institutions is at end.

---

16. *Id* at 278. All such actions are brought, in France, before special administrative courts, including the supreme "Conseil d'Etat."
17. See Income Tax Decree No. 19 of 1956.
18. In so far as not reversed by the Imperial *Celot*.
19. *Stare decisis*, however, may bring a premature rigidity into the legal system as a whole.
20. Subject to reversal by the Imperial *Celot*.
21. Such court could also give advisory opinions at drafting stage.

Due to lack of case-reports, this terse analysis is purely tentative. Future cases (or more reflection) may impose its modification. Our chief aim is to provoke thought on the issues involved, further discussion of which should be in practical detail. This paper's theoretical method may indeed be somewhat out of place in traditional society for which a living hierarchy of persons was always more significant than an abstract one of laws. A "flawless" hierarchy of laws is not an ideal of universal validity. I hope to have demonstrated that it may be incompatible – at top level – with a beneficial system of undivided supreme powers. At other levels, the obstacle may be merely lack of awareness and implementing devices.

<u>የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጠምራ ፡ ክስ ፤</u>

በፊሊፕ ፡ ግሪቨን ፤ ፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የካሳ ፡ ክስ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ለአደረሰው ፡ ጉዳት ፡ የገንዘብም ፡ ሆነ ፤ ሌላ ፡ ጥፋት ፡ የሚከስበት ፡ ማለት ፡ ነው ። (አንቀጽ ፡ ፪ሺ፳፯ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ) ። ይህም ፡ ጉዳት ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ወንጀል ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የወንጀል ፡ ጥፋት ፡ ከሆነ ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ጥፋቶች ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ። በአንቀጽ ፡ ፪ሺ፴፭ ፡ እንደተመለከተው ፡ መሠረታዊ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጥፋትን ፡ አጥፍቶ ፡ የሚያልፍበት ፡ አንድን ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ደንብ ፡ በመጣስ ፡ ጉዳት ፡ ያደረሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ።

ሁለቱም ፡ ዓይነት ፡ ጥፋቶች ፡ በጠባያቸው ፡ ስለሚለያዩ ፡ ከዚህ ፡ የሚነሱት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይታያሉ ። የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ዓላማቸው ፡ የተለየ ፡ ሲሆን ፤ ምክንያታቸውና ፡ አስተያየታቸው ፡ የተለየ ፡ ነው ፤ የወንጀሉ ፡ ቅጣትና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ካሳም ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ጥፋቶች ፡ አንድ ፡ በሆነ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ተግባር ፡ ስለሚነሱ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የወንጀሉንና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ክስ ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማየት ፡ ለሥራ ፡ ማቀላጠፍ ፡ ይጠቅማል ። የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ የሚመለከተው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ካሳም ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለመተዳደሪያ ፡ የሚወስነው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለወንጀል ፡ ቅጣት ፡ ሊወስን ፡ አይችልም ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፭ ፡ ወንጀል ፡ መሥራቱን ፡ እንኳ ፡ ቢያውቅ ፤ ይህ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻ና ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፬—፩፻፶፱ ፡ በጉልህ ፡ የተመለከተው ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የአንድነት ፡ ክስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። በ፩ሺ፱፻፵፱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እንደተመለከተው ፡ የወንጀልን ፡ ክስ ፡ የሚመለከተው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ ካሣ ፡ እንዲያገኝ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ፤ (ለምሳሌ ፥/ አንቀጾች ፡ ፪፻፸፫—፪፻፸፯—፪፻፺፬) ። አዲስ ፡ ሆኖ ፡ የተሠራው ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገሮች ፡ በጣምራ ፡ የሚሠራበት ፡ ጠቅላላው ፡ መሠረት ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የጥፋት ፡ ኃላፊነት ፡ በወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰማበት ፡ ሁኔታና ፡ ሁለቱ ፡ የሚገናኙበት ፡ ሕጋዊ ፡ ሥሪት ፡ ከቀድሞው ፡ ይልቅ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጥንቃቄ ፡ ተሠርቷል ።

፩ ፤ ግዴታዎች ፡

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻ ፡ አንድ ፡ ጥፋት ፡ <u>ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት</u> ፤ (፩) ከደረሰ ፡ የተጐዳው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሰዎች ፡ አጥፊው ፡ እንዲክስ ፡ ወይም ፡ እንዲተካ (፪)

፩፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ የሚለው ፡ ቢቀር ፡ መልካም ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ ጉዳቱ ፡ ትንሽ ፡ ከሆነ ፡ የጣምራ ፡ ካሳ ፡ አይፈቀድም ፡ ማለት ፡ ይመስላል ።

፪፤ የገንዘብ ፡ መተካት ፡ ትእዛዝ ፡ በወንጀለኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለወንጀልና ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔርም ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ እንዲታይ ፡ ባይጠቅም ፡ በራሱ ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ፡ (አንቀጽ ፡ ፺፱/፪)ና ፡ ፩፻፶፱ ፡ (፪) ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ።

ሲል ፡ ተደንግጓል ። ክሱንም ፣ ለማቅረብ ፣ የተጐዱት ፣ ወይም ፡ ካሳ ፣ የሚጠይቁት ፣ ሰዎች ፣ በአንድ ፣ ላይ ፣ የወንጀሉን ፣ ክሶች ፣ ለማቅረብ ፣ ይችላሉ ። የወንጀልና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔርም ፣ ጣምራ ፣ ክስም ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፡ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ በአንቀጾች ፣ ፩፻፶፬—፩፻፶፱ ፣ በተመለከተው ፣ መንገድ ፣ ወይም ፣ አኳኋን ፣ ይፈጸማሉ ።

፩፤ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፶፬ ፣ (፫/ (፫ ፣ መሠረት ፣ ተጐጂው ፣ አንድም ፣ ሰው ፣ ሆነ ፤ ሕዝብ ፣ በሙሉ ፣ የወንጀልና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ጣምራ ፣ ክስ ፣ ሊደረግ ፣ ይቻላል ። ነገር ፣ ግን ፣ የወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ እራሱ ፣ በማነሳሳት ፣ የጣምራ ፣ ክስ ፣ ይቅረብ ፣ ለማለት ፣ አይችልም ። ነገሩ ፣ በመጀመሪያ ፣ ሲሰማ ፤ ተጐዳሁ ፣ ያለው ፣ ወገን ፣ በማመልከቻ ፣ (፩፻፶፬/፩) ፣ (፬) ፣ በፊት ፣ የጣምራ ፣ ክስ ፣ ይታይልኝ ፣ ብሎ ፣ ማመልከት ፣ አለበት ፣ (፭) ።

አንዳንድ ፣ አስፈላጊ ፣ ነገሮች ፣ ካልተፈጸሙ ፣ በስተቀር ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፣ በአንድ ፣ ላይ ፣ በጣምራ ፣ መታየት ፣ የለባቸውም ፡ ከተባለ ፣ እነዚህን ፣ ነገሮች ፡ መፈጸም ፣ አለመፈጸማቸውን ፣ ለይቶ ፣ ለመወሰን ፣ ማመልከቻው ፣ ፍርድ ፣ ቤቱን ፡ ይረዳዋል ። በዚህም ፣ አኳኋን ፣ አንቀጽ ፣ ፩፻፶፬ ፣ ማመልከቻው ፣ (ሀ) ፣ የተፈለገውን ፡ የካሳ ፣ ዓይነት ፣ ለምሳሌ ፣ ምትክ ፣ ወይም ፣ ካሳ ፣ ወይም ፣ ሁለቱን ፣ (ለ) ፣ የተፈለገውን ፣ የካሳ ፣ መጠን ፣ (፮) ፣ (ሐ) ፣ ተከሳሹ ፣ ወይም ፣ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፣ ከተጠሩት ፡ ሌላዎች ፡ ስለ ፣ ካሳው ፣ መጠንና ፣ ተገቢ ፣ መሆን ፣ የሚመሰክሩ ፣ ከሳሹ ፣ ለመጥራት ፣ የሚችል ፡ ነው ፣ በማለት ፣ ያዛል ። (፮) ፣

እነኚህ ፣ አስፈላጊ ፣ ነገሮች ፣ አስፈላጊዎቹ ፣ በሙሉ ፣ ስለማይሆኑ ፣ የወንጀልና ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፡ ድርብ ፣ ክስ ፣ ነገሩ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የሚሰጡት ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፣ መጨመር ፣ አለባቸው ። በአንቀጽ ፣ ፩፻፶፭ ፣ (ሠ) ፣ ና ፣ (፪) ፣ መሠረት ፣ ስለሚጠየቀው ፣ ካሳና ፣ ስለ ፣ ምስክሮቹ ፣ መግለጫ ፣ ነገሮች ፣ ያስፈልጋሉ ። በተጨማሪም ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻፶፭ ፡ (፩) ፣ (ኪ) ፡ (መ) ፣ ና ፣ (ረ) ፣ መሠረት ፣ ተጨማሪ ፣ መግለጫዎች ፡ ያስፈልጋሉ ። እንደነዚህ ፣ ያሉትን ፣ መግለጫዎች ፣ ካላገኘ ፡ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ማመልከቻውን ፡ ለመቀበል ፣ ላለመቀበል ፣ ለመወሰን ፣ ያስቸግረዋል ። ስለዚህ ፣ አመልካቹ ፣ ተከሳሹ ፣ መቅረብ ፣ እንዳለበት ፣ (፰) ፣ በየትኛውም ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፣ ካሳውን ፣ እን

፫፤ አይደለም ፡ ተብሎ ፣ ካልተነገረ ፣ ከሕግ ፡ የሚጠቀሱት ፣ ሁሉ ፣ ከወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ ነው ።

፬፡ ይህ ፣ ተከሳሹ ፣ ክታወቀ ፣ በኋላ ፣ (አንቀጽ ፣ ፩፻፷፰) ፣ ክሱ ፣ ከመነበቡ ፣ (፩፻፷፱) ፣ አንቀጽ ፣ ፱ ፣ በፊት ፣ ማመልከቻው ፣ ይቀርባል ፣ ይል ፣ ይመስላል ።

፭፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፣ ነገር ፡ በሕጉ ፣ የተረጋገጠ ፣ ባይሆንም ፡ በአንቀጾች ፡ ፩፻፶፬—፩፻፶፱ ፣ መሠረት ፣ ማመልከቻው ፣ መሰማት ፣ ያለበት ፣ በመጀመሪያ ፣ ላይ ፣ ነው ። ግን ፣ ይህ ፣ ዓይነት ፣ መንገድ ፣ ይግባኝ ፣ ለተባለበት ፣ ነገር ፣ አይደለም ።

፮፡ የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ለንብረትና ፣ ለሞራል ፣ ካሳ ፣ የጠየቀ ፣ እንደሆነ ፣ የሁለቱ ፣ ጥያቄዎች ፣ በተራ ፣ መቅረብ ፣ አለባቸው ።

፯፡ ከሳሹ ፣ እንደ ፣ ዐቃቤ ፣ ሕግ ፣ ሆኖ ፣ በሚሠራበት ፣ ጊዜ ፣ ከምስክሮቹ ፣ የትኞቹ ፣ ለወንጀሉ ፣ የትኞቹ ፣ ደግሞ ፣ ለካሳው ፣ መሆናቸውን ፣ ገልጾ ፣ ማስረዳት ፣ አለበት ፣ ይኸም ፣ የሆነው ፣ ምስክሮቹ ፣ በአልተጠሩበት ፣ ንብተው ፣ እንዳይመሰክሩ ፣ ነው ። የተጐዳው ፣ ወገን ፣ ተጨማሪ ፣ ምስክሮች ፣ ለመቁጠር ፣ ካልፈለገ ፤ በየትኞቹ ፣ ምስክሮች ፣ ነገሩን ፣ ለማጣራት ፣ እንዳሰበ ፣ ማረጋገጥ ፣ አለበት ።

፰፤ በውነቱ ፣ ክሱ ፣ ጉዳት ፣ ባደረሰው ፣ ሳይሆን ፣ በሌላው ፣ መቅረብ ፣ አለበት ። ይኸውም ፣ ማለት ፣ አንድ ፣ መኪና ፣ ነጅ ፡ የራሱ ፣ ያልሆነውን ፣ መኪና ፣ እየነዳ ፣ በቸልተኛነት ፣ ሰው ፣ ቢገድል ፤ ካሳው ፣ ከነጂ ፣ ሳይሆን ፣ ከባለመኪናው ፣ መጠየቅ ፣ አለበት ። (የመኪናው ፣ ባለቤት ፣ በነጂ ፣ ጥፋት ፣ ከሌለ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፪፻፹፯ ፣ መሠረት ፣ ለካሳው ፣ ኃላፊ ፣ ነው) ።

ደተጠቀቀና ፡ ማስረጃዎቹን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ፤ ይኸውም ፡ ክሱ ፡ የተፈቀደ ፡ እንደሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ ስለክሣው ፡ መከላከያውን ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ ይረደዋል ።

፪፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ ተመልክቶ ፤ በራሱ ፡ ሥልጣንም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አሳሳቢነት ፡ ወይም ፡ በተከሳሹ ፤ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፩) ፡ ወይም ፡ (፪) ፡ መሠረት ፡ ለመቀበል ፡ የማይቻልበት ፡ ምክንያት ፡ ከተገኘ ፡ ማመልከቻውን ፡ አይቀበለውም ። በዚህም ፡ መሠረት ፡ የሚከተሉት ፡ አስተያየቶች ፡ ይሰጡ ፡ ይሆናል ።

፫፤ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (ሀ) ፡ ና ፡ (ለ) ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ የማይቀበለው ፡ በጣም ፡ ወጣት ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ (አንቀጽ ፡ ፫) ፡ ዕድሜው ፡ በ፲፰ ፡ ና ፡ ፲፭ ፡ ዓመታት ፡ በሆነ ፡ ሰው ፡ ክስ ፡ ሲቀርብ ። የዚህ ፡ መከልከል ፡ ዓላማው ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። ወላጆቹ ፡ ወይም ፡ ለወላጆችም ፡ ምትክ ፡ ሁነው ፡ የሚቆጠሩት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፺፱ ፡ ና ፡ ፪ሺ፩፻፺፮/ ከሕፃኑ ፡ ጋር ፡ ለጥፋቱ ፡ ኃላፊ ፡ ከሆኑ ፤ የተበደለው ፡ ወገን ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚከለከልበት ፡ ምክንያት ፡ አጥጋቢ ፡ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ለጥፋቱ ፡ ኃላፊ ፡ የሆነው ፡ ከሕፃኑ ፡ ጭምር ፡ ለመከሰስ ፡ ስለሚችል ፡ ነው ። ግን ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፩) ፡ (ሀ) ፡ መሠረት ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ ለወንጀል ፡ ጣምር ፡ ክስ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ካልተፈጸሙ ፡ ክስ ፡ ይቆያል ፡ የሚለውን ፡ ለማስወገድ ፡ ከሆነ ፡ ክሱን ፡ ላለመቀበል ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ለወንጀል ፡ ክስ ፡ ዕድሜው ፡ አልደረሰም ፡ ከማለት ፡ (፲፭ ፡ ዓመት) ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ዕድሜው ፡ አይፈቅድም ፡ (፲፰ ፡ ዓመት ፡) ማለት ፡ ነበር ።

፬፡ ተከሳሹ ፡ ካልቀረበ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከቻውን ፡ አይቀበለውም ። የዚህ ፡ መከልከል ፡ ከለመለመዱም ፡ በላይ ፡ ምክንያቱ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም፡ ክሱ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ቢቀርብ ፡ ባይቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጥ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ። (፱)

ስለሁለቱም ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ፡ ብሎ ፡ መደንገግ ፡ ይሻል ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ የማይቀበሉትን ፡ ነገር ፡ ማመልከቻውን ፡ መቀበልና ፡ ነገሩን ፡ መመልከት ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ነው ። የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ ስለወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ለመከሰስ ፡ ሲፈልግ ፡ ማመልከቻ ፡ ከማቅረቡና ፡ የምስክሮቹን ፡ ዝርዝር ፡ ከመመልከቱ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቶሎ ፡ መላክ ፡ አለበት ፡ ምክንያቱም ፡ እነዚህ ፡ ዝርዝሮች ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ ለመስጠት ፡ ስለማይችሉ ፡ ነው ።

(ለ) ማመልከቻውንም ፡ ነገሩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከተጀመረ ፡ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ የሚገባው ፡ ሁኖ ፡ ካልተገኘ ፡ ለማሰናበት ፡ ይቻላል ። የመጀመሪያው ፡ ደንብ ፡ የተመሠረተው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድን ፡ መንገድ ፡ ከመረጡ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ለመዛወር ፡ አይቻልም ፡ በሚለው ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ነው ። የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ካሳውን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ወይም ፡ በወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊጠይቅ ፡ ሲችል ፤ ከአንዱ ፡

፱፡ ይህ ፡ መከልከል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለትንሽ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ጥፋት ፡ ማመልከቻ ፡ ከቀረበለት ፡ አይቀበልም ፡ ማለት ፡ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተከሳሹ ፡ ግድ ፡ ማቅረብ ፡ የለበትም ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፷፰) ወይም ፡ ባይቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ። (አንቀጽ ፡ ፩፻፷ ፱)

ከጠየቀ ፣ ወደ ፣ ሌላው ፣ ለመዛወር ፣ አይችልም ፣ (፲) ነገር ፣ ግን ፣ አስፈላጊዎቹ ፣ ነገሮች ፣ አልተፈጸሙም ፣ በማለት ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ማመልከቻውን ፣ አልቀበልም ፣ ለማለት፣ ይችላል ።

ይህ ፣ ሊሆን ፣ የሚችለው ፣ ግን ፣ ጉዳዩ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ሳይሆን ፣ በወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የቀረበ ፣ እንደሆነ ፣ ነው ።

(ሐ) በአንቀጽ ፣ ፩፻፶፭ ፣ (፩) (ሠ) ወይም ፣ (ረ) መሠረት ።

የፍትሐ ብሔሩ ፣ ነገር ፣ ያከብደዋል ፣ ወይም ፣ የወንጀሉን ፣ ነገር ፣ ይጐትተዋል ፣ በማለት ፣ የተሰናበተ ፣ ክስ ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ በአንቀጽ ፣ ፩፻ ፣ መሠረት ፣ ለመግለጽ ፣ ወይም ፣ ለማብራራት ፣ ይቻላል ። በዚሁም ፣ አንቀጽ ፣ መሠረት ፣ ነገሩ ፣ አስቸጋሪ ፣ ከሆነና ፣ ጥናትም ፣ የሚደረግበት ፣ ሲሆን ፣ ወይም ፣ ያዋቆች ፣ አስተያየት ፣ የሚሰጥበት ፣ ከሆነ ፣ የወንጀሉ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ነገሩን ፣ ወደ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሊያዛውረው ፣ ይችላል (፲፪) ። የፍትሕን ፣ ነገር ፣ ለማካሄድ ፣ ሲባል ፣ የፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ የወንጀል ፣ ጣምራ ፣ ክስ ፣ እንደሚፈቀደው ፣ ሁሉ ፣ አልመች ፣ ካለ ፣ ነገሩን ፣ ለመስማት ፣ ማመልከቻውን ፣ መቀበል ፣ አይፈቀድም ።

(መ) ደግሞም ፣ የተጠየቀው ፣ የክሳ ፣ ገንዘብ ፣ መጠኑ ፣ ነገሩን ፣ ከሚያየው ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ሥልጣን ፣ በላይ ፣ ከሆነ ፣ ነገሩን ፣ መቀበል ፣ አይችልም ። ለምሳሌ ፣ የወንጀለኛ ፣ መቅጫን ፣ ሕግ ፣ አንቀጽ ፣ ፫፻፴፱ ፣ በመቃወም ፣ ጉዳት ፣ ደርሶበት ፣ የተጐዳው ፣ ሰው ፣ $1000 በወረዳ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ለመጠየቅ ፣ አይችልም ። የወረዳው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ለፍትሐ ፣ ብሔርና ፣ ለወንጀል ፣ ክስ ፣ ከ100 ብር ፣ በላይ ፣ በሆነ ፣ ገንዘብ ፣ ሥልጣን ፣ የለውም ።

እነኝህን ፣ ነገሮች ፣ ነክ ፣ የሆኑትን ፣ ነገሮች ፣ ሁሉ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ማመልከቻውን፣ አልቀበልም ፣ ማለት ፣ አለበት ። ነገር ፣ ግን ፣ በሁለት ፣ ነገሮች ፣ ጥያቄ ፣ ብቻ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ምርጫ ፣ ሊኖረው ፣ ይችላል ። እነኝህም ፣ ነገሮች ፣ ጥያቄ ፣ (ሀ) በፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ክስ ፣ ለተጠየቀው ፣ ገንዘብ ፣ የሚመሠክሩት ፣ ምስክሮች ፣ በጣም ፣ ብዙዎች ፣ ናቸውን? (ለ) የፍትሐ ፣ ብሔሩን ፣ ክስ ፣ መስማትስ ፣ ነገሩን ፣ አስቸጋሪ ፣ ያደርገዋል ፣ ወይስ ፣ ይጐትተዋል? የሚሉት ፣ ናቸው ፤ ሁለቱም ፣ ጥያቄዎች ፣ አወን ፣ ተብለው ፣ ከተመለሱ ፣ ማመልከቻም ፣ መገደፍ ፣ አለበት ።

፲፤ ነገር ፣ ግን ፣ ምርጫው ፣ የግድ ፣ መጨረሻ ፣ ነው ፣ ማለት ፣ አይደለም ። የተጐዳው ፣ ወገን ፣ በወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ በወንጀልና ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ክስ ፣ ቢያቀርብም ፤ ፍርድ ፣ ከመስጠቱ ፣ በፊት ፣ ክሱን ፣ አንስቶ ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ሊቀርብ ፣ ይችላል ። (አንቀጽ ፣ ፩፻፶፮) በውጭ ፣ አገር ፣ የሚሠራው፣ እንደሚያመለክተው ፣ በፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ የቀረበው ፣ ክስ ፣ ለፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ያለ ፣ ሥልጣኑ ፣ ከሆነ ፣ ወይም ፣ በስሕተት ፣ የወንጀልን ፣ ነገር ፣ ወደ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔሩ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ከሄደ ፣ ነገሩን ፣ ከዚሁ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ አቁሞ ፣ ወደ ፣ ወንጀል ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ለመውሰድ ፣ ይቻላል ። ነገሩ ፣ የቀረበለት ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ነገሩ ፣ በሌላ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ተጀምሮአል ፣ ብሎ ፣ ባለጉዳዮቹ ፣ ካላመለከቱ ፣ ማመልከቻውን ፣ ማሰናበት ፣ እንደሌለበት ፣ ማስታወስ ፣ ይጠቅማል ።

፲፩፤ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ የተጐዱት ፣ ወገኖች ፣ ወይም ፣ ክስ ፣ መብት ፣ ያላቸው ፣ የትኞቹ ፣ እንደሆኑ ፣ ለማወቅ ፣ ትንሽ ፣ ያዳግት ፣ ይሆናል ።

፲፪፤ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት ፣ መሠረት ፣ ክሱን ፣ የማሰናበቱን ፣ ጉዳይ ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫው ፣ ሕግ ፣ እንደተደነገገው ፣ ምርጫ ፣ ማይሆን ፣ ጊዴታ ፣ ነው ።

፫፤ አንዳንድ ፡ ሰዎችም ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፰ ፡ ከተመለከቱት ፡ ነገሮች ፡ ምክንያት ፡ በቀር ፡ በሌላስ ፡ ማመልከቻው ፡ ይገደፍ ፡ ይሆን ፡ ብለው ፡ ሣያስቡ ፡ አይቀሩም ። በተለይም ፡ ተከሳሹ ፡ ክሳሹ ፡ ጉዳዩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት ፡ የለበትም ፡ ብሎ ፡ ለመቃወም ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ መብት ፡ አለ ፡ ወይ ? ተብሎ ፡ ይጠየቅ ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ በሕጉ ፡ በደንብ ፡ ያልተገለጠ ፡ ነገር ፡ እንደሚከተለው ፡ መልስ ፡ ሊሰጠው ፡ ይቻላል ።

ተከሳሽ ፡ ነገሩ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በዕርቅ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ተሰጥቶበት ፡ አልቋል ፡ በማለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዳያየው ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ነገሩ ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተጀምሮአል ፡ በማለት ፡ እንዳይታይ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። ወይም ፡ ከሳሹ ፡ መብት ፡ የለውም ፡ ወይም ፡ አልተሰጠውም ፡ በማለትም ፡ ሊቃወም ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ዳግም ፡ ነገሩ ፡ በሽምግልና ፡ ያልቃል ፡ በማለት ፡ ሊቃወም ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፰ ፡ (፩) ፡ (ሐ) ፡ ና ፡ (መ) ፡ መሠረት ፡ ነገሩ ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይታያል ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ መብት ፡ የለውም ፡ ከሚሉት ፡ መቃወሞች ፡ በስተቀር ፡ ሌላዎቹ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ በወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ለሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ምን ፡ መልስ ፡ ይሰጣቸዋል ?

(ሀ) ለፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ ለወንጀል ፡ ለሚደረገው ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ክሳ ፡ የተጠየቀበት ፡ ነገር ፡ ከሆነ ፡ ማመልከቻው ፡ ይገደፋል ። ነገር ፡ ግን ፡ የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፡ ካሳ ፡ ፍርድ ፡ ተሰጥቶ ፡ እንደሆነ ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ የወንጀሉን ፡ ነገር ፡ በሚያቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ፍርድ ፡ ዳግመኛ ፡ እንዲታይ ፡ ለመጠየቅ ፡ አይችልም ። ይህም ፡ ነገሩ ፡ በፍርድ ፡ ቤትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ባለ ፡ ጉዳዮቹ ፡ ተስማምተው ፡ ከተፈጸመ ፤ ውጤቱ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ (አንቀጽ ፡ ፫ሺ፫፻፲፪) (፩) ። ነገር ፡ ግን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚለውን ፡ ዓላማ ፡ ከተከተለ ፡ በነገሩ ፡ በመጀመሪያ ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ የማይቻል ፡ ይመስላል ። ግን ፡ በወንጀል ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ካሳ ፡ ከተጠየቀ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ነገር ፡ የወንጀሉ ፡ ጉዳይ ፡ እስኪያልቅ ፡ መቆየት ፡ አለበት ።

(ለ) ተከሳሹ ፡ የወንጀሉና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፡ ስለተሰናከለ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ መታየት ፡ የለበትም ፡ ብሎ ፡ የተቃወመ ፡ እንደሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፶፫ ፡ (፪) ፡ መሠረት ፡ መቃወሙን ፡ ለመሻር ፡ ይችላል ። በወንጀል ፡ ጥፋት ፡ የሚጠየቅ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ካሳ ፡ የወንጀሉ ፡ ጉዳይ ፡ ከልቆመ ፡ ቆመ ፡ ለማለት ፡ አይቻልምና ፡ ነው ።

(ሐ) ተከሳሹ ፡ ነገሩ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቦታ ፡ ምክንያት ፡ ነገሩን ፡ ማየት ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ የተቃወመ ፡ እንደሆንም ፤ ይህ ፡ መቃወም ፡ ሊሠረዝ ፡ ይቻላል ፤ ምክንያቱም ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ወይም ፡ በወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ ስለአለው ፡ ነው ። የተጐጂ ፡ ምርጫ ፡ ነገሩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ሥልጣኑ ፡ ለሌላ ፡ ይሆን ፡ ነበር ፡ በሚል ፡ መሠናክል ፡ የለበትም (፲፫) ።

፲፫፤ ተከሳሹ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ መቃዎሞች ፡ ሊያነሳ ፡ የሚችልባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ምክንያቱም ፡ የሁለቱም ፡ ሥልጣን ፡ ስለሚገናኝ ፡ ነው ። የወንጀል ፡ ጥፋት ፡ አብዛኛውን ፡ በተሠራበት ፡ ቦታ ፡ ይታያል ። እንደዚሁም ፡ በአልሆነ ፡ ነገር ፡ ለተደረገ ፡ ጥፋት ፡ ካሳ ፡ የሚጠየቀው ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ ነው ። ግን ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ሕግ ፡ አልወጣም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ ስለክሱ ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ ስለአለው ፡ ሥልጣን ፡ የተቃወመ ፡ እንደሆነ ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮችን ፡ ያስከትላል ። ተከሳሹ ፡ በገንዘቡ ፡ መጠን ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ የታቃወመ ፡ እንደሆነ ፤ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፫ (፪) መሠረት ፡ ይሠራል ። ዳግምም ፡ በክሱ ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ ሥልጣኑ ፡ የሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የተቃወመ ፡ እንደሆነ ፤ መቃወሙ ፡ አጥጋቢ ፡ ከሆነ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ አይታይም[፲፱] ። እንደሚታወሰው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩ ፡ የሚያገባው ፡ ከሆነ ፡ መቃወሙ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ ነገሩን ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ አለበት ።

(መ) ክስ ፡ ስለማቅረብ ፡ መጀመሪያ ፡ ስለሚጠየቀው ፡ ፈቃድ ፡ እንደሚታወሰው ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ መጠየቅ ፡ አለበት ፤ በተለይም ፡ በዘመዳሞች ፡ መካከል ፡ ክስ ፡ የተነሣ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ ለወንጀል ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ ከሚቀርበው ፡ ጉዳይ ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ፡ ምክንያቱም ፡ የሚጠየቀው ፡ ፈቃድ ፡ ክሳ ፡ ስለመጠየቅ ፡ ስለአልሆነ ነው ።

(ሠ) በመጨረሻም ፡ ተከሳሹ ፡ ነገሩ ፡ በሽማግሌ ፡ ያልቃል ፡ ሲል ፡ ያመለክት ፡ ይሆናል ፤ ይህም ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ መብት ፡ መቃወም ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ። ለእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፫ ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል ። ይህም ፡ አንቀጽ ፡ ጉዳቱ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ካሣው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ይስማሙ ፡ ይሆናል ፡ የሚል ፡ ነው ። ስምምነቱ ፡ የካሣው ፡ ነገር ፡ በሽማግሌ ፡ ያልቃል ፡ የሚል ፡ ሆኖ ፤ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ያልተስማማ ፡ እንደሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ሺ፫፻፵፬ ፡ መሠረት ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ ለወንጀል ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ አይፈቀድም ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ።

፬፡ አንድ ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ አይደረግበትም ፡ ብሎ ፡ ከወሰነ ፡ ይግባኝ ፡ አይባልበትም ። አንቀጽ ፡ ፩፻፶፫ ፡ (፫) ፡ ይህ ፡ ይግባኝ ፡ እንዳይባል ፡ ብሎ ፡ መወሰን ፡ ተገቢ ፡ ነው ። ተገቢነቱም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ መቃወም ፡ ጠቃሚ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ አይደለም ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ክስ ፡ ማቅረብን ፡ ጨርሶ ፡ ስለማይከለክልና ፡ ስለካሳው ፡ ስለሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ለመቃወም ፡ ስለማይችል ፡ ነው ። ይግባኝ ፡ እንዳይባል ፡ ሲባል ፡ የተጐዳውን ፡ ሰው ፡ ካሣ የሚጠይቅበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመምረጥ ፡ መብቱን ፡ ብቻ ፡ ይቃወምበታል ፡ እንጂ ፤ ሌላ ፡ ውጤት ፡ የለውም ። የተጐዳው ፡ ሰው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርንና ፡ የወንጀልን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመውሰዱ ፡ መንገድ ፡ ቢዘጋበትም ፤ ወደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ለመውሰድ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ ስለአልተነካበት ፡ ነገሩን ፡ ወደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊወስድ ፡ ይችላል ። ከዚህ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ነገሩን ፡ በከለከለው ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወን

፲፱፡ ይህ ፡ የሚሆነው ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ የተጠየቀው ፡ የካሳ ፡ የገንዘብ ፡ መጠን ፡ ነገሩ ፡ ለቀረበለት ፡ ሳይሆን ፡ የሌላው ፡ ሥልጣን ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ አጥፍተው ፡ ለሚጠየቁበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት ፡ አለበት ፡ ይባል ፡ ይሆናል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ የወንጀሉም ፡ ጥፋት ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መታየት ፡ አለበት ፡ ካላለ ፤ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርን ፡ ክስ ፡ አጣምሮ ፡ ለማቅረብ ፡ አያስችልም ። በውነቱም ፡ በመጀመሪያው ፡ የወንጀል ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ ጥቂቶቹ ፡ ብቻ ፡ በዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይታያሉ ።

ጀሉ ፡ ጉዳይ ፡ ከላለቀ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ መመልከት ፡ አይቻልም ፡ ይል ፡ ይሆናል ።
ስለዚህም ፡ ነገር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የጥፋት ፡ ሐላፊነትን ፡ በሚወሰንበት ፡ ጊዜ ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ ያሰናብተው ፡ አያሰናብተው ፡ ነገሩን ፡ ከማየት ፡ አያቆመውም ፡ ይላል ።

፬ ፤ ውጤቶች ።

ለወንጀልና ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ጣምራ ፡ ማመልከቻው ፡ ከተፈቀደ ፤ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ከሳሽ ፡ ሆኖ ፡ ይከራከራል ። እርሱም ፡ እንደሌላው ፡ ተከራካሪዎች ፡ ማለት ፡ እንደከሳሽና ፡ እንደተከሳሽ ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ ይኖሩታል ፤ (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፮ ፡ (፩) ። ይህም ፡ ማለት ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ የክሱን ፡ ቅጅ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፱ ፡ (፬) ፡ መሠረት ፡ ያገኛል ፡ ማለት ፡ ነው ። የተጐዳውም ፡ ወገን ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉና ፡ በተከላካዩ ፡ ከተጠሩት ፡ ምስክሮች ፡ ስለሚጠይቀው ፡ ካሣ ፡ ለማስመስከር ፡ ምስክሮች ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፳፬ ፡ መሠረት ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ። በእንደዚህም ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ የተጠሩት ፡ ምስክሮች ፡ በይቀርቡ ፡ በአንቀጽ ፡ ፺፬ ፡ (፪) (ለ) መሠረት ፡ ቀጠሮ ፡ ይቀበላል ። በአንቀጽ ፡ ፩፻፴፯ ፡ መሠረትም ፡ ካልሆነ ፡ መሪ ፡ መሪ ፡ ጥያቄዎችን ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ምስክሩን ፡ ሊጠይቀው ፡ አይችልም ። ከመረታቱ ፡ በፊትም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያውቀው ፡ የተከሳሹን ፡ ያለፈ ፡ ታሪክ ፡ ማውራት ፡ የለበትም ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፴፰) ። ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ጉዳይ ፡ እንደከሳሹ ፡ ያለ ፡ መብት ፡ አለው ። ለምሳሌ ፡ ስለካሣው ፡ ጉዳይ ፡ መከላከያውን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ቀጠሮ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ፤ ወይም ፡ የመከላከያ ፡ ምስክሮችን ፡ ለማቅረብ ፡ ቀጠሮ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ።

ነገር ፡ ግን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ በወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ረዘምና ፡ ጠለቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። በተጠቀሰው ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ እንደ ሌሎቹ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ መብት ፡ ሲኖረው ፤ ስለማስረጃም ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ያልተለየ ፡ መብት ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ በደንብ ፡ ባለመገለጡ ፡ ከሳሹ ፡ መብት ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ እንደሚጠቀምበት ፡ አልተገለጸም ። ይህም ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫን ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻ ፡ ዓላማ ፡ ዋጋቢስ ፡ ያደርገዋል ። የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ የያዘ ፤ ማመልከቻን ፡ ቢቀበሉ ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ባለማወቅና ፤ ከሳሹስ ፡ ምን ፡ እንደሚሠራ ፡ ባለማወቅ ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ማመልከቻውን ፡ አንቀበልም ፡ ማለቱ ፡ ይሠልጣቸው ፡ ይሆናል ።

በውነቱ ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ሁናቴ ፡ በሁለት ፡ አንቀጾች ፡ ብቻ ፡ በግልጽ ፡ ተነግሯል ። በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፪(፩) ፡ መሠረት ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ማስረጃውን ፡ የሚያቀርበው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሓሳቡን ፡ ካቀረበ ፡ በኋላ ፡ ነው ። በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፮(፪) ፡ መሠረት ፡ ከሳሹ ፡ ስለከሳው ፡ ጉዳይ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማመልከት ፡ የሚችለው ፡ የተከላካዩ ፡ መልስ ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ግን ፡ አንዳንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እነኝህን ፡ የተሰጡ ፡ መግለጫዎች ፡ የከሳሹ ፡ መብቶች ፡ ከሌላዎቹ ፡ ተከራካሪዎች ፡ አንድ ፡ ለመሆኑ ፡ በጣም ፡ እያስረዱም ፡ ይሉ ፡ ይሆናል ። የወንጀለኛ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያልተሟላ ፡ በመሆኑ ፤ ስለወንጀልና ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡ ማብራሪያ ፡ ይፈልጉ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕጎች ፡

የሚሰጡት ፡ እርዳታ ፡ ጥቂት ፡ ነው ። በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ በነሱው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ አይታዩም ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተለየ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ለተጐዱት ፡ ወገኖች ፡ ካሳን ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል(፲፭) ። ነገር ፡ ግን ፡ በውነቱ ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ፤ ምክንያቱም ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ካሳ ፡ የሚጠይቀው ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ተከሳሹ ፡ አጥፊ ፡ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ የካሳው ፡ ጉዳይ ፡ ከወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ጋር ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ክርክር ፡ አይቀርብበትም ፡ ማለት ፡ ነው(፲፮) ። በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ግን ፡ ከሳሹ ፡ ስለማስረጃ ፡ ስለአለው ፡ መብት ፡ ጥቂት ፡ ችግሮች ፡ ብቻ ፡ ያጋጥማሉ ። ምክንያቱም ፡ ዋና ፡ ምርመራ ፤ መስቀልኛ ፡ ምርመራና ፡ የድጋሚ ፡ ጥያቄ ፡ የሚል ፡ በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ውስጥ ፡ ስለሌለ ፡ ነው ። በተለይም ፡ ይህ ፡ ችግር ፡ የሌለው ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ የቀረበውን ፡ ክስ ፡ ደግፎ ፡ ለመናገር ፡ ስለሚችል ፡ ነው (፲፯) ።

ስለዚህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተመለከተው ፡ አሠራር ፡ ተመሳሳይ ፡ የለውም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ስለዚህ ፡ ይህንን ፡ ሕግ ፡ በመጥቀስ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ለሚያጋጥሙት ፡ ችግሮች ፤ ይኸው ፡ የሕግ ፡ መጻፍ ፡ በሚሰጠው ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግና ፡ የጣምራው ፡ ክስ ፡ አላማው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ በመመልከት ፡ ችግሮቹን ፡ ማስወገድ ፡ ይኖራል ። የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ በወንጀል ፡ ጥፋት ፡ ለሚነሱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የኃላፊነት ፡ ውሳኔዎችን ፡ ለማፋጠን ፡ ሊሆንና ፤ የተጐዳውም ፡ ወገን ፡ ካሳ ፡ ለማግኘት ፡ በነገሩ ፡ እንዲከራከር ፡ ስለሚፈቀድለት ፤ ማነኛውም ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ በሚከተለው ፡ መንገድ ፡ መሠራት ፡ አለበት ።

፩ ፡ ክሱ ፡ ከተነበበ ፡ በኋላና ፡ የተከሳሹ ፡ መልስ ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፴፪) ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ካለና ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛ ፡ ነኝም ፡ ቢል ፡ ጥፋቱ ፡ ወዲያው ፡ ካልታወቀ ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፴፫ ፡ እና ፡ ፩፻፴፬) ክሱን ፡ ይጀምራል ። ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ምስክሮቹን ፡ ይመረምራል ፤ ወይም ፡ ይጠይቃል ። እነዚሁም ፡ ምስክሮች ፡ በተከሳሹ ፡ ከተጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በጥያቄው ፡ ለተነሱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ ዳግም ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ፡ (አንቀጾች ፡ ፩፻፴፮ ፡ እና ፡ ፩፻፴፱) ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ከቆጠራቸው ፡ ምስክሮች ፡ አንዱን ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ ይመሰክራል ፡ ብሎ ፡ ካመለከተ ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፬/፪) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ምስክር ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፴፮ ፡ እንደተመለከተው ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ከመሠከረ ፡ በኋላ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ሌሎች ፡ ምስክሮች ፡ ከመጠራታቸው ፡ በፊት ፡ ሊመሠክር ፡ ይችላል ። ግን ፡ ሌላ ፡ መንገድም ፡ ለመከተል ፡ ይቻላል ። ከሳሹ ፡ ምስክሩ ፡ በወንጀሉ ፡ ምስክርነቱ ፡ በሰጠው ፡ ቃል ፡ የመስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ ከመጠየቁ ፡ በፊት ፡ ሊጠይ

፲፭፤ አርክች ፡ በርድ ፡ የወንጀል ፡ አቤቱታ ፤ ማስረጃና ፡ የአሠራሩ ፡ ልምድ ፡ የ፴፪ኛው ፡ እትም ፤ ገጽ ፡ ፪፻፪፩ ፡

፲፮፤ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የሚሠራበት ፡ መንገድ ፡ (የሕንድን ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፵፭ ፤ የሱዳንን ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፲፩ ፤ ማላየሲያን ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፷፩ ፤ የደቡብ ፡ አፍሪካን ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፰፪ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ተመልከት ፡) በኢትዮጵያም ፡ መሠራት ፡ ነበረበት ፤ ምክንያቱም ፡ በኢትዮጵያም ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉን ፡ ካሳ ፡ ካሳጣሬ ፡ የካሳውን ፡ ነገር ፡ አይመለከትም ፡ (አንቀጽ ፡ ፭፻፵፰) ።

፲፯፤ ለምሳሌ ፡ Code d'instruction criminelle, Art. 335: "A la suite des dépositions dés témoins (...), la partie civile ou son conseil et le procureur général seront entendus et développeront *les moyens qui appuient l'accusation*". ተመልከት ።

ቀው ፡ ይችላል ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የመስቀልኛ ፡ ጥያቄው ፡ ስለወንጀሉና ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ሊጠየቅ ፡ ይቻላል ።

በሁለቱም ፡ መንገድ ፡ ለመሥራት ፡ ይቻላል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ በታና ፡ ጊዜው ፡ በመመልከት ፡ የተሻለውን ፡ ለመከተል ፡ ይችላል ፤ ምክንያቱም ፡ ይህንን ፡ ወይም ፡ ያንን ፡ ተከተል ፡ የሚል ፡ ሕግ ፡ ስለሌለ ፡ ነው ። ምናልባት ፡ ሁለተኛው ፡ መንገድ ፡ ጉዳዩን ፡ ያዘበራርቃል ፡ ለማለት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። ደግሞም ፡ ሁለተኛው ፡ መንገድ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱ ፡ በጥንቃቄ ፡ ከተተረጐመ ፡ ከዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ጋር ፡ አይስማማም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ይህ ፡ አንቀጽ ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ ካበቃ ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ የራሱን ፡ ክስ ፡ ያቀርባል ፡ ይላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ምስክር ፡ አበቃ ፡ ለማለት ፡ የሚቻለው ፤ ምስክሩ ፡ መልሶ ፡ መላልሶ ፡ ስለወንጀሉ ፡ በተናገረው ፡ ሁሉ ፡ ከተጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ነው ። የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ምስክር ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ካሳ ፡ ምስክር ፡ ከሰጠ ፡ ያለ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ እንደተሰጠ ፡ ይቆጠራል ። ስለዚህ ፡ ምስክሩ ፡ መጀመሪያ ፡ በከሳሹ ፡ ይጠየቃል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በተከሳሹ ፡ ተጠይቆ ፡ በከሳሹ ፡ እንደገና ፡ ይጠየቃል ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ለካሳ ፡ የሚጠየቀው ፡ ምስክር ፡ ከሳሹ ፡ የሚጠይቀው ፡ ጥያቄ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ተከሳሹ ፡ ሊቃወም ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ መቃወም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፮ ፡ መሠረት ፡ አስፈላጊውን ፡ መልስ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ። ስለማስረጃ ፡ መመዝገብ ፡ የሚደነግገው ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፵፯ ፡ ስለ ፡ ካሳ ፡ በሚሰጠው ፡ ማስረጃም ፡ ጊዜ ፡ ይሠራበታል ።

፪ የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ምስክሮች ፡ ከተሰሙ ፡ በኋላ ፡ ስለካሳው ፡ ነገር ፡ ቢጠየቁ ፡ ባይጠየቁም ፤ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ካሳ ፡ መጠየቅ ፡ ያለውን ፡ ማስረጃ ፡ ያቀርባል ። በእሱም ፡ ጠያቂነት ፡ የቀረቡትን ፡ ምስክሮች ፡ ያስመሰክራል ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መታወስ ፡ አለበት ፤ ይኸውም ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፩ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ያቀረበው ፡ ክስ ፡ የለምና ፡ ተከሳሹ ፡ መከላከል ፡ አያስፈልገውም ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሹን ፡ በነጻ ፡ ማሰናበት ፡ አለበት ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንደተጠቀሰውም ፡ የተከሰሰው ፡ በወንጀል ፡ ካልተፈረደበት ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፫) የካሳ ፡ ፍርድ ፡ አይሰጥበትም ። ስለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሹ ፡ ለቀረበበት ፡ ክስ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ ሲያሳስብ ፡ ብቻ ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ስለሚጠየቀው ፡ ካሳ ፡ ያለውን ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ይጠየቃል ። ይኸም ፡ ማስረጃ ፡ ከዚህ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በተመለከተው ፡ መንገድ ፡ ይካሄዳል ፤ ማለት ፡ ምስክሮቹ ፡ በከሳሹ ፡ መጀመሪያ ፡ ይጠየቁና ፡ በተከሳሹ ፡ የመስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ ተጠያቂው ፤ እንደገና ፡ በከሳሹ ፡ ደግመው ፡ ይጠየቃሉ ።

፲፰፤ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ጥያቄዎቹን ፡ ሲጠይቅ ፡ ተከሳሽ ፡ ካሳ ፡ መክፈል ፡ እንደሚገባው ፡ በማመልከቻ ፡ ብቻ ፡ ያልተወሰነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። በውነቱ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የተጐዱት ፡ ወገኖች ፡ የአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ እረዳት ፡ በመሆን ፡ ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑን ፡ ለማመልከት ፡ ማስረጃ ፡ ሲያቀርቡ ፡ ይታያሉ ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ማስረጃዎች ፡ ከመስመራቸው ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ለመቀበል ፡ አይቻልም ። እርግጥ ፡ ነው ፤ የሚገባና ፡ የማይገባ ፡ ማስረጃ ፡ ብሎ ፡ ለመወሰን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ያዳግት ፡ ይሆናል ። ለምሳሌ ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ተከሳሽ ፡ በማወቅ ፡ ለመሥራቱ ፡ ለማስረዳት ፡ ይፈልግ ፡ ይሆናል ፤ ይኸም ፡ በሞራል ፡ በኩል ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ በሚጠይቀው ፡ ካሳ ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፺፯ ፡) በጣም ፡ ይጠቅም ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ መታወስ ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ይኸውም ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክሱን ፡ በደንብ ፡ ባያካሂደው ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ሥህተቱን ፡ ለማቃናት ፡ አይችልም ። ለማቃናትም ፡ መብት ፡ የለውም ። ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ በዚሁ ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ስህተት ፡ ምክንያት ፡ ቢለቀቅም ፤ ስለ ፡ ካሳው ፡ ጉዳይ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ አያግደውም ። (የፍትሐ ፡ ብሔር ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፱) ፡

፫፤ በተጐዳው ፡ ሰው ፡ ወገን ፡ የሚቀርበው ፡ ክስ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ፤በተከላካዩ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ተጀምሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ምስክሮቹን ፡ ይጠራል ። እነዚህም ፡ ምስክሮቹ ፡ በወንጀሉ ፡ ነገር ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፴፪ (፪)ና ፡ (፫) የምስክርነት ፡ ቃላቸውን ፡ ይሰጣሉ ። ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ የካሳ ፡ ክስ ፡ እንዲመሰክሩ ፡ በተጐዳው ፡ ሰው ፡ የተቆጠሩት ፡ ምስክሮች ፡ በወንጀል ፡ በኩል ፡ ለአለው ፡ ክስ ፡ ምስክርነታቸውን ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ በከሳሹ ፡ ጀማሪነት ፡ ስለካሣው ፡ ይጠየቃሉ ፡ እንዲሁም ፡ ቀጥለው ፡ በተከሳሹ ፡ ከተጠየቁ ፡ በኋላ ፡ መልሰው ፡ ቢያስፈልግ ፡ በከሳሹ ፡ ይጠየቃሉ ።ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ ስለ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ኃላፊነት ፡ ለማስመስከር ፡ ምስክር ፡ የጠራ ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ ምስክር ፡ የወንጀሉ ፡ ጉዳይ ፡ ማስረጃው ፡ ከተመዘገበ ፡ በኋላ ፡ ይሰማል ። ይህም ፡ ምስክር ፡ መጀመሪያ ፡ በተከሳሹ ፡ ይጠየቃል ፡ ቀጥሎም ፡ በተጐዳው ፡ ወገን ፡ ይጠየቅና ፡ ቢያስፈልግ ፡ መልሶ ፡ በተከሳሹ ፡ ይጠየቃል ።

፬፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፯ (፪) መሠረት ፡ የተጐዳው ፡ ሰው ፡ ስለካሣው ፡ ፍርድ ፡ ያመለክታል ። ቀጥሎም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ የሃላፊነት ፡ ክስ ፡ በአዋፊው ፡ ላይ ፡ እንደተመሰከረበትና ፡ የሚጠይቀውም ፡ ካሣ ፡ የተገባ ፡ መሆኑን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይገልጻል ። በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ ዓይነት ፡ ማብራሪያ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀርበው ፡ ተከላካዩ ፡ የአቤቱታ ፡ ቃሉን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ነው ። ተከሳሹም ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ መብት ፡ አለው ። ይህ ፡ ሲባል ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያመለክተው ፡ የመከላከያውን ፡ ማስረጃ ፡ ከወሰደ ፡ በኋላ ፡ ነው? ወይስ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፴፰ (፪) መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመጨረሻ ፡ ማመልከቻውን ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ነው? ሁለተኛው ፡ መንገድ ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፴፱ (፩) ተመልከት) ። ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የማመልከት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ሆኖ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ስለ ፡ ካሣው ፡ ጉዳይ ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ፡ ብሎ ፡ መደንገግ ፡ ባላስፈለገም ፡ ነበር ፡ ምክንያቱም ፡ ይህንን ፡ የመጨረሻ ፡ አቤቱታውን ፡ ሲያቀርብ ፡ ሊያደርገው ፡ ስለሚችል ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራበት ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ ቀደም ፡ ተከተሉ ፡ ስህተትን ፡ ለማስወገድ ፡ ተሰውጧል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፭፤ ከዚህ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተሰጡት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ መግለጫዎች ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ጥፋት ፡ ሲሠራባቸው ፤ በግልም ፡ ጉዳት ፡ ይሠራባቸዋል ። እነኚህም ፡ መግለጫዎች ፡ ማስረጃ ፡ ላልተገኘለት ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ በተሠራ ፡ ጥፋትም ፡ ይሠራባቸዋል ።

(ሀ) የተጐዳው ፡ ሰው ፡ እንደግል ፡ ክስ ፡ አድርጐ ፡ በሚያቀርበው ፡ በግል ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ነገር ፡ መንግሥት ፡ እንደተደረገው ፡ ክስ ፡ እንደሚታየው ፡ ይታያል ።ነገር ፡ ግን ፡ ከሳሹ ፡ በግሉ ፡ በመንግሥቱም ፡ ነገር ፡ የቆመ ፡ እንደሆነ ፡ በመጀመሪያ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ምስክሮች ፡ ቆጥሮ ፡ ከዚያ በኋላ ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ ምስክሮች ፡ ይቆጥራል ።ነገር ፡ ግን ፡ ለወንጀሉ ፡ የተቀጠሩት ፡ ምስክሮች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ካሣ ፡ የሚመሠክሩ ፡ ከሆነ ፡ ስለወንጀሉ ፡ በሰጡት ፡ ቃላቸው ፡ ደጋግመው ፡ ተጠይቀው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ስለካሣው ፡ ሊመሠክሩ ፡ ይችላሉ (፲፱፤) ።

(ለ) ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ ተከሳሹ ፡ አጥፍቻለሁ ፡ ብሎ ፡ ካመነ ፤ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሆነ ፡ በተከላካዩ ፡ ማስረጃ ፡ ሳይቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካልተቃወመ ፡

፲፱፤ እንደሚታወሰው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ የተሰጡት ፡ መግለጫዎች ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተሻለ ፡ መንገድ ፡ ካገኘ ፡ እንደምርጫው ፡ እንዳይሠራ ፡ አይከለክለውም ።

በቀር ፡ በራሱ ፡ እምነት ፡ ሊፈረድበት ፡ ይችላል (፳፤) ። ይህም ፡ ሲባል ፡ የተጐዳውን ፡ ሰው ፡ መብት ፡ ለማሰናከልና ፡ ለመጉዳት ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፱ ፡ (፫) መሠረት ፡ ስለቅጣቱ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከማመልከቱ ፡ በፊት ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ክሱን ፡ ይጀምራል ፡ ማለት ፡ ነው ። ከሳሹ ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉና ፡ በተከላካዩ ፡ ከቀረቡት ፡ ምስክሮች ፡ መካከል ፡ አንዳንዶቹ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ባይሰጥ ፡ ኑሮ ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክሣ ፡ ይመሠክሩ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ካሠበ ፤ እነኝህ ፡ ምስክሮች ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ በሚሠራበት ፡ መንገድ ፡ ቃላቸውን ፡ ይሠጣሉ ። ልዩነቱ ፡ ስለካሣው ፡ የሚሰጠው ፡ የሚቀርበው ፡ ማስረጃ ፡ ከፍርዱ ፡ በኋላ ፡ እንጂ ፡ በፊት ፡ አይሰማም ። የተጐዳውም ፡ ወገን ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሐላፊነት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለማመልከት ፡ መብት ፡ አለው ። ተከሳሹም ፡ እንደዚሁ ፡ ለመመለስ ፡ መብት ፡ አለው ። ይህም ፡ መብት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ ተከሳሹ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፰ የመጨረሻ ፡ ሃሣባቸውን ፡ ከመስጠታቸው ፡ በፊት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

፫ ፡ ፍ ር ድ ።

ዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ ተከሳሹ ፡ ያላቸውን ፡ የመጨረሻ ፡ ጉዳይ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካመለከቱና ፡ ከሳሹም ፡ ስለሚጠይቀው ፡ ካሳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ከጠየቀ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ፤ (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱/፩) ። ቅጣቱም ፡ በቀረቡት ፡ ማስረጃዎች ፡ መሠረት ፡ ይሠጣል ፤ (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱/፫) (፳፩) ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንደተጠቀሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሹ ፡ በወንጀል ፡ አጥፍቶ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ካሳ ፡ ፍርድ ፡ አይሰጥም ፤ (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፰) ። ተከሳሹ ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ አጥፍቶ ፡ ካልተገኘ ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ነገሩን ፡ ማቅረብ ፡ አለበት (፳፪) ። የተጐዳው ፡ ወገን ፡ በክሱ ፡ ከረታ ፡ ፍርዱ ፡ የሚከተሉትን ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። (ሀ) ስለ ፡ ወንጀሉ ፡ ነገር ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፵፱ ፡ መሠረት ፡ የተፈለጉትን ፡ ጉዳዮችና ፡ (ለ) ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ነገር ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፶፱ ፡ የተፈለጉትን (፳፫) ።

(ሀ) የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካሳ ፡ ለመስጠት ፡ ብቻ ፡ ተወስኗል ። ስለዚህም ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሌላ ፡ ከወንጀል ፡ ሥራ ፡ ከሚመነጭ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡

፳፤ ነገር፡ግን ፡ ስለ ፡ ተከሳሹ ፡ ጠባይም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የአለፈ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ማስረጃ ፡ ጥፋቱ ፡ ከተረጋገጠም ፡ በኋላ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ። (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱) (፫)ና ፡ (፬)

፳፩፤ ይኸን፡ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ጉዳይ ፡ አይቃወመውም ። ተከሳሹ ፡ በራሱ ፡ እምነት ፡ ከተፈረደበት ፡ ከሳሹ ፡ በፍርድ ፡ ጥፋቱ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ አያመለክትም ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፵፱ ፡ (፩)።

፳፪፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፱ (፪) ከወንጀል ፡ ሥራ ፡ የተነሱ ፡ ለመሥራት ፡ የተወሰኑ ፡ የሚሰው ፡ ነገሩ ፡ የተሰናበተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይሠራበት ፡ አይሠራበት ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ካሣው ፡ ከወንጀሉ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። የፈረንሳይ ፡ ከፍተኛ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰኔ ፡ ፳ ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ በአወጣው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ የወንጀሉ ፡ ነገርም ፡ ቢሰናበት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ነገር ፡ እስከ ፡ ተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሊታይ ፡ ይችላል ፡ ብሏል ።

፳፫፤ አንቀጽ ፡ ፩፻፶፱ ፡ አልተሟላም ፤ ምክንያቱም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ የካሣ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያየው ፡ የወንጀል ፡ ፍ/ቤት ፡ ጉዳዩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍ/ቤት ፡ ሲታይ ፡ እንደሚገኘው ፡ ያለ ፡ ማብራሪያ ፡ ስለማይገኝ ፡ ነው ፤ (ለምሳሌ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠበት ፡ ምክንያቶች ፤ በየትኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደፈረደና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ መግለጫዎች ፡ መስጠት ፡ ነበረባቸው)

ነገር ፡ መግባት ፡ የለበትም ፡ (፳፱) ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በመጥለፍ ፡ ምክንያት ፡ ጥፋት ፡ አጥፍቶ ፡ ቢገኝና ፤ የተጠለፈችውም ፡ ከዚሁ ፡ ሰው ፡ አርግዛ ፡ ብትገኝ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፻፵፰ ፡ መሠረት ፡ የወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ልጁ ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመፍረድ ፡ አይችልም ። እንደዚሁም ፡ በዝሙትነት ፡ ምክንያት ፡ ተከሳሹ ፡ አባት ፡ ላለመሆኑ ፡ የሚያሳዩ ፡ ማስረጃዎች ፡ ቢቀርቡም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፻፵፱ ፡ መሠረት ፡ ተካሹ ፡ ልጂ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ ማመልከቻ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ፈቃድ ፡ አይሰጥም ።

(ለ) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከጥፋት ፡ ለደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ካሳ ፡ ሊያሰጥ ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ በቸልተኛነት ፡ ሰው ፡ በመግደል ፡ በተደረገ ፡ ጥፋት ፡ ላይም ፡ የንብረት ፡ ጉዳት ፡ ቢደርስ ፡ የነፍስ ፡ ካሳ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ንብረቱ ፡ ካሳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊያሰጥ ፡ አይችልም ። እንዲያውም ፡ በቸልተኝነት ፡ ምክንያት ፡ የደረሰ ፡ ጉዳት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በአናቀጽ ፡ ፮፻፵፫ ፡ እንደተመለከተው ፤ የወንጀል ፡ ጥፋትን ፡ ኃላፊነት ፡ አያስከትልም ። ይህ ፡ አንቀጽ ፡ የወንጀል ፡ ጥፋት ፡ የሚያደርገው ፡ በማወቅ ፡ የተሠራን ፡ ጥፋት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በወንጀል ፡ ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ኃላፊነት ፡ ካልተነሳ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻ ፡ መሠረት ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካሳ ፡ ሊያሰጥ ፡ የሚለው ፡ ሕግ ፡ አልተሠራበትም ፡ ማለት ፡ ነው (፴) ።

(ሐ) ካሣም ፡ በሚያሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለግምቱና ፡ ስለ ፡ ካሣው ፡ አከፋፈል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የሚገኘውን ፡ ሕግ ፡ ይከተላል ። ለምሳሌ ፡ የሟቹ ፡ ወገኖች ፡ ካሣ ፡ የጠየቁ ፡ እንደሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ ለካሣ ፡ ይከፈል ፡ ብሎ ፡ አያዝም ፡ እንጂ ፡ ለመተዳደሪያ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ይከፈል ፡ ብሎ ፡ ለማዘዝ ፡ ይችላል ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፺፭) ፡ ለሞራል ፡ ጉዳት ፡ ካሣ ፡ የተጠየቀ ፡ እንደሆነ ፡ ለካሣ ፡ የሚሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ከ$ 1000 አይበልጥም ፤ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፲፮ ፡ (፫) ።

(መ) ከሳሽ ፡ በነገሩ ፡ የረታ ፡ እንደሆነ ፤ ተከሳሹ ፡ ነገሩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ቢሆን ፡ ኑሮ ፡ የሚከፍለውን ፡ የፍርድ ፡ ቤትና ፡ የሌላውንም ፡ ወጭ ፡ መክፈል ፡ አለበት ፤ (አንቀጾች ፡ ፩፻፶፱ና ፡ ፪፻፺፪) ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሳሹ ፡ ሣይረታ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ከመክፈሉም ፡ በላይ ፡ ተከሳሹ ፡ ያወጣውን ፡ ወጭም ፡ ይከፍላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚከፍለው ፡ ገንዘብ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብ ፡ የሚከፈለው ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፬ ፡ (፩) ግን ፡ ፍርድ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ የሚከፈለው ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፶፱(፩)ለ) እንዲሁም ፡ ሌላው ፡ ወጭ ፡ ነገሩ ፡ የተሰናበተ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ የተለቀቀ ፡ እንደሆነ ፡ እንዴት ፡ እንደሚከፈል ፡ አልተነገረም ። ሁኔታው ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ገንዘቡ ፡ በሙሉ ፡ በከሳሹ ፡ መጀመሪያ ፡ ተከፍሎ ፡ በጉዳዩ ፡ የረታ ፡ እንደሆን ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ በሙሉ ፡ በተከሳሹ ፡ እንዲከፈል ፡ የሚል ፡ ይመስላል ።

፳፱ ይህ ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ በጣምራ ፡ እንዲታይ ፡ ባይፈቀድም ፡ የሚሠራበት ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ኃላፊ ፡ ሆኖ ፡ ካላገኘው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፶፩ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተከሳሹ ፡ ሊፈርድበት ፡ አይችልም ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ይህንኑ ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ መዝለል ፡ አለመዝለል ፡ ያስፈልግ ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ ክርክር ፡ ይነሣል ።

፴ ነገር ፡ ግን ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፷፱ ፡ ትርጉም ፡ መሠረት ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጥፋቶች ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ሲገኙና ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ ነፍስ ፡ በማጥፋቱ ፡ ላይ ፡ የተገኘው ፡ ጥፋት ፡ ያለውቀት ፡ ከሆነ ፡ የነፍስ ፡ ዋጋና ፡ የንብረቱም ፡ ዋጋ ፡ ሊታዘዝ ፡ ይቻላል ።

(ሥ) የተጐዳው ፡ ወገን ፡ በግሉ ፡ እንጂ ፡ በመንግሥት ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ጨምሮ ፡ ካልተከራከረ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ክስና ፡ ስለ ፡ ካሳው ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም (፳፮) ። ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካሳ ፡ አላሰጠው ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮/፩) ። ወይንም ፡ ካሳ ፡ ቢሰጥም ፡ ስለ ፡ ካሳው ፡ መጠን ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ይችላል ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮/፫) ። ነገር ፡ ግን ፡ የሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ ይግባኝ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፶፫ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት ። ተከሳሹ ፡ ግን ፡ በወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ሳይል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካሳ ፡ በማዘዙ ፡ ወይም ፡ ስለአዘዘው ፡ የካሳ ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ይግባኝ ፡ ሊል ፡ ይችላል ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮/፪) ። ስለካሳው ፡ የሚደረገው ፡ ይግባኝ ፡ ለወንጀሉ ፡ ጉዳይ ፡ ይግባኝ ፡ ሲባል ፡ አብሮ ፡ ይሄዳል ፡ (፳፯) በወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ባይባልም ፤ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ጉዳይ ፡ ሥልጣኑ ፡ ወደሆነው ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ፡ (አንቀጽ ፡ ፩፻፹፮/፬ ። ስለካሳ ፡ ጉዳይ ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ በወንጀሉ ፡ ተከሳሹ ፡ ካልተረታ ፡ ካሳ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ። ይህም ፡ ማለት ፡ ተከሳሹ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ክስና ፡ ስለካሳው ፡ ጉዳይ ፡ ይግባኝ ፡ ብሎ ፡ ሳለ ፡ የወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉን ፡ ካሳ ፡ ካሰናበተው ፤ ስለካሳውም ፡ ያለውን ፡ ይግባኝ ፡ ማሰናበት ፡ አለበት ። ግን ፡ ስለካሳው ፡ ጉዳይ ፡ በወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ቢሰናበት ፡ ሥልጣን ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል (፳፰) ።

(ረ) ግን ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ካሳና ፡ ስለሌላዎችም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡ ፍርድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደተሰጠ ፡ መቆጠርና ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፡ (አንቀጽ ፡ ፪፻፲) ። ይኸም ፡ ይደረጋል ፡ ሲባል ፡ እንዲከፍል ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ ለመክፈል ፡ ችሎታ ፡ ሲኖረው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፩ ፡ መሠረት ፡ ለፍርድ ፡ ቤትና ፡ ለሌላ ፡ ወጭ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ሳይሆን ፡ ለካሳ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ከጠየቀ ፡ ከተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የተወረሱት ፡ ዕቃዎች ፡ ተሸጠው ፡ ያስያዘውና ፡ በመቀጮ ፡ የከፈለው ፡ ገንዘብም ፡ ተጨምሮ ፡ ይከፈላል (፳፱) ። ነገር ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ማመልከቻ ፡ ሲቀርብለት ፡ የሕግ ፡ ርዳታ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ እንደሚመረምረው ፡ ሁሉ ፡ ስለተፈረደበት ፡ ሰው ፡ የሀብት ፡ ሁኔታ ፡ ማጥናት ፡ አለበት ። ስለዚህም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በአዘዘው ፡ መሠረት ፡ ስለተፈረደበት ፡ ሰው ፡ ድሀ ፡ መሆን ፡ የቀረበው ፡ ራፖር ፡ አጥጋቢ ፡ ሆኖ ፡ ካላገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በወንጀል ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፩ ፡ መሠረት ፡ ካሳ ፡ እንዲከፍል ፡ ማዘዝ ፡ የለበትም ። ስለድህነት ፡

፳፮፣ በመንግሥት (በኩል) በተደረገው ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ አቃቤ (ሕጉ ፡ ክስ) ካላቀረበ (የተጐዳውን) ወገን ፡ ክስ ፡ አቅርብ ፡ ብሎ ፡ መብት ፡ ሊሰጠው ፡ አይችልም ፤ አንቀጽ ፡ ፵፪(፩) ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወንጀሉን ፡ ቢያቆም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሳለው ፡ ሥራ ፡ አይደለም ። በመንግሥት ፡ በኩል ፡ ስለአለው ፡ ካሣ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ነገሩን ፡ ለመከታተል ፡ ወይም ፡ ለመተው ፡ የአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ መብት ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ ፡ቀጽ ፡ ፩፻፹፰ ፡ እንደሚለው ፡ ስለ ፡ ወንጀሉ ፡ ጉዳይ ፡ ለማመልከት ፡ ወይም ፡ ለመከራከር ፡ የሚችሉት ፡ የሚገባቸው ፡ ወይም ፡ የተጐዱት ፡ ወገኖች ፡ ማለት ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ ናቸው ፤ እንደ ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ የማይከራከረው ፡ የይግባኝ ፡ ሥልጣኑም ፡ የተጐዳው ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ካሣ ፡ ብቻ ፡ ይነጋገራል ። የይግባኝ ፡ ሥልጣኑም ፡ በተለየ ፡ አንቀጽ ፤ ማለት ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፹፮ ፡ ተመልክቷል ።

፳፯፣ መጀመሪያ ፡ ክሱ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉንና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ከፈቀደ ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የጣምራውን ፡ ክስ ፡ መቀበል ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ የለበትም ። ይኸውም ፡ ይግባኝ ፡ የተባለበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የካሳውን ፡ ይግባኝ ፡ የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ ያቆየዋል ፡ ወይም ፡ ያክብደዋል ፡ ብሎ ፡ አልቀበልም ፡ ማለት ፡ አይችልም ።

የቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ ወይም ፡ ልመና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከተቀበለው ፡ መንግሥቱ ፡ ስለተፈረደበት ፡ ድሀ ፡ ለከሣሹ ፡ ያልፋል ፤(የወንጀኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፩(፫)።

፪ በወንጀልና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ የሚነሱት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ችግሮች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ አስቸጋሪነታቸው ፡ ከዚህ ፡ ያነሰ ፡ ይነሱ ፡ ይሆናል ። በተለይም ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ችግሮች ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ ተፈቅዶ ፤ የወንጀሉ ፡ ነገር ፡ ሲያቆም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ነገር ፡ የቀጠለ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ችግሮች ፡ የሚገኙት ፡ በተለይም ፡ ተከሳሹ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ምሕረት ፡ የተደረገለት ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህም ፡ ችግሮች ፡ መሠረታዊ ፡ የሆነውን ፡ የጣምራ ፡ ክስ ፡ ደንብ ፡ በመከተል ፡ ሊወገዱ ፡ ይችላሉ ።

(ሀ) ተከሳሹ ፡ ሳይፈረድበት ፡ ወይም ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑ ፡ ሳይረጋገጥ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ በመንግሥት ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ክስ ፡ ይቆማል ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪፻፳፫ ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ ከሞተ ፡ ክሱም ፡ አይቀጥልም ፡ ፍርድም ፡ አይሰጥም(፸)። ነገር ፡ ግን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፡ በሟቹ ፡ ወራሾች ፡ ላይ ፡ ሊቀጥል ፡ ይችላል ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፶፪ (፫) ። ነገር ፡ ግን ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ በመቀጠል ፡ ያየው ፡ ይሆን ፡ ወይ? ብሎ ፡ መጠየቅን ፡ ያስከትላል።በፈረንሣይ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከፍተኛ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ (የፈረንሣይ) ፡ በየካቲት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ በወሰነው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፤ መልሱ ፡ ለማየት ፡ ወይም ፡ ለመቀጠል ፡ የወንጀሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይችል ፡ ነበር።በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ መልሱ ፡ ሊያይ ፡ አይችልም ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ የቀረበለት ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉ ፡ ጥፋት ፡ መሠራቱ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ካሣ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ፡ ስለተባለ ፤ ተከሳሹ ፡ የወንጀል ፡ ሥራው ፡ ከመረጋገጡ ፡ በፊት ፡ ከሞተ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ የማየት ፡ ሥልጣኑ ፡ ወዲያውኑ ፡ ያቆማል ። ነገር ፡ ግን ፡ የፍትሐ፡ብሔሩ፡ክስ፡ለወንጀሉ፡የተሰጠውን፡ያህል፡የይርጋ፡ዘመን ፡ ይሰጠዋል ። ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ፡የተነሳው፡ከወንጀሉ፡በደል፡ስለሆነ፡ነው ።

፷፰፡ግን ፡ ተከሳሹ ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ተረትቶ ፡ በወንጀሉ ፡ እንጂ ፡ በካሳው ፡ ይግባኝ ፡ ቢልና ፡ በኋላ ፡ ነፃ ፡ ቢወጣ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ይነሳል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይግባኝ ፡ ተብሎበት ፡ የወንጀሉን ፡ ጉዳይ ፡ ያስናበተው ፡ ፍርድ፡ ቤት፡ሁለቱም ወገኖች ፡ ተስማምተው ፡ የተቀበሉትን ፡ ማለት ፡ ይግባኝ ፡ ያልተባለበትን ፡ የካሣ፡ ክስ ፡ አንቀጽ፡ ፩፻፶፷ ፡ ወንጀሉን ፤ ያሠናበተ ፡ ካሣውን ፡ ማሰናበት ፡ አለበት ፡ ስለአለ ፡ ማስናበት ፡ አለበትን ? መልሱ፡ ማድረግ ፡ አለበት ፡ የማለት ፡ ይመስላል ። አንደኛ ፡ ያልቀረበለትን ፡ ነገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማየት ፡ የለበትም። ሁለተኛም ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፶፰ ፡ የሚከለክለው ፡ የወንጀሉንና ፡ የካሳውን ፡ ነገር ፡ የሚያየው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ ካስናበተው ፡ ካሳ ፡ መስጠት ፡ የለበትም ፤ ብሎ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀሉን ፡ ክስ ፡ ማስናበትና ፡ የካሳ ፡ ገንዘብ ፡ ማስከፈል ፡ የለበትም ። ሕጉ ፡ በየትም ፡ ቦታ ፡ ቢሆን ፡ አንድ፡ ይግባኝ ፡ ያልተባለበት ፡ የፍትሕ ፡ ብሔር ፡ የካሳ ፡ ፍርድ ፡ ተከሳሹ ፡ ይግባኝ ፡ ብሎ ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ቢለቀቅ ፡ የካሳው ፡ ጉዳይም ፡ ይሰናበታል ፡ የሚል ፡ የለም ።

፷፱ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፩ ፡ የተመለከተው ፡ ደንብ ፡ በ፩ሺ፱፻፴ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ፡ኤ፡አ፡ በወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መግቢያ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፭ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ።

፸ ግን ፡ ከሳሹ ፡ ቢሞት ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፪(፪) ፡ መሠረት ፡ ከሞተ ፡ የመክሰሱ ፡ መብት ፡ ካልቆመ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፪(፩) ፡ መሠረት ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፡ ወራሾቹ ፡ ሊነጋገሩ ይችላሉ ።

(ለ) የይቅርታ ፡ ወይም ፡ የምሕረት ፡ ሕግ ፡ ከወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ክሱን ፡ ያቆመዋል ፤ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፵ (፪) ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በሞት ፡ ምክንያት ፡ እንደተሠራው ፡ ይሠራል ። ግን ፡ ምሕረት ፡ ክሱን ፡ ስለሚያስቀረውና ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፵(፪)) ክስ ፡ ቀርቦበት ፡ የነበረውንም ፡ የወንጀል ፡ ጥፋት ፡ እንዳልተሠራ ፡ ስለሚያስቆጥረው ፡ ከዚሁ ፡ የወንጀል ፡ ጥፋት ፡ የተነሣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ከወንጀሉ ፡ ጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። ስለዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፫ (፪) መሠረት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ክስ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተወሰነ ፡ የይርጋ ፡ ጊዜ ፡ የለውም ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ የይርጋ ፡ ጊዜ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ሺ፩፻፵፫ (፩) በተመለከተው ፡ የይርጋ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የተወሰነው ። ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፤ የተደረገ ፡ ምህረት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ የካሣ ፡ ገንዘብ ፡ ከመክፈል ፡ አያግድም ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፵፩) ።

የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ጣምራ ፡ ክስ ፡ የሚካሄድበት ፡ መንገድ ፡ እንደሌሎቹም ፡ አገሮች ፡ በኢትዮጵያም ፡ ታሪካዊ ፡ ምክንያት ፡ አለው ። ይህም ፡ መንገድ ፡ ወይም ፡ አሠራር ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ በወንጀል ፡ ሥራ ፡ ለተጐዱት ፡ ወገኖች ፡ ጠቃሚነት ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ የወንጀል ፡ መቅጫን ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተገቢ ፡ አንቀጽ ፡ እየተከተሉ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሳይ ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ «ከግል ፡ ጥቅም ፡ የጠቅላላ ፡ ጥቅም ፡ መቅደም ፡ አለበት» ያለውን ፡ ማስታወስ ፡ ይገባል ።

JOINDER OF CRIMINAL AND CIVIL PROCEEDINGS

by Philippe Graven
Ministry of Justice

Civil liability consists in one's duty to repair the material and/or moral damage suffered by another person in consequence of an event for which one is answerable (Art. 2028 Civil Code). This event may or may not be in the form of a criminal offence, but if it is in such a form, then a civil liability may be incurred together with a criminal liability. Indeed, the principle as stated in Art. 2035 Civil Code is that a person is civilly liable where he infringes a specific and explicit legal provision and thereby causes damage to another.

Both types of liability differ in nature and raise different questions which are normally settled by different courts, for the objects of criminal and civil proceedings are not identical nor are the justification, purposes and effects of criminal penalties and civil remedies. However, owing to the fact that both types of liability originate from one and the same unlawful behaviour, it may in some cases be expedient to allow a joinder of criminal and civil proceedings so that the criminal and civil aspects of the case be decided by one and the same court. A court trying a criminal offence may thus decide on the civil liability of the convicted person. But the reverse is not possible and a court trying a civil claim, such as a claim for maintenance, would have no jurisdiction to sentence the defendant to a criminal punishment even where it should consider that he has committed an offence contrary to Art. 625 Penal Code.

This joinder of proceedings, which is now expressly provided for by Art. 100 Penal Code and Arts. 154-159 Criminal Procedure Code, is not a novelty in Ethiopian law; it could occur under the 1930 Penal Code already, many provisions of which empowered the court trying a criminal case to order that the convicted person pay damages to the injured party (*e. g.* Arts. 273, 296-299). What is new, however, is the generality with which the principle of joinder is now formulated. Moreover, the conditions under which a claim for compensation may be heard by a criminal court and the effects of a joinder of criminal and civil proceedings are regulated today with greater precision than they were in the past.

I - CONDITION

Art. 100 Penal Code lays down that "where an offence has caused considerable damage . . ., [1] the injured party or the persons having rights from

1. The word "considerable" should have been omitted for it may lead one to think, wrongly, that a joinder of proceedings may not be allowed where an offence has caused little damage.

him shall be entitled to claim that the offender be ordered to make good the damage or to make restitution[2] or to pay damages by way of compensation . . . . For the purpose of establishing his or their claim, the injured person or the persons having rights from him may be joined as parties in the criminal proceedings. The conditions, form and manner of such joinder shall be governed by the provisions of the Criminal Procedure Code, which provisions are Arts. 154-159.

1. According to Art. 154 (3) Criminal Procedure Code, (3) an order for joinder may be made whether the prosecution in the proceedings is public or private. However, such an order may not be made by a criminal court of its own motion, and written application for joinder must always be submitted by the injured party at the opening of the hearing (Art. 154 (1))[4] in the court of first instance [5].

